የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት
JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

24ኛ ቮልዩም ቁ 1	በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የሚታተም	Vol. XXIV No. 1
ነሐሴ 2002 ዓ.ም	Published at least once annually	July, 2010

In This Issue:

Articles

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Published at least once a year by the School of Law,
Addis Ababa University
Founded in 1965
(To be cited as 24 J. Eth.L.No.1)

...

ADDIS ABABA UNIVERSITY
SCHOOL OF LAW

Faculty
2010/11 Academic Year

Aberra Degefa	-	LL.B, LL.M; Lecturer
Aman Assefa	-	LL.B, LL.M; Lecturer
Andreas Eshete	-	B.A, M.A, Ph.D.; Professor and President of A.A.U
Blen Asemire	-	LL.B; Assistant Lecturer
FikreMarkos Merso	-	LL.B,LL.M,Ph.D.;Assistant Professor & Dean
Gedion Timothewos	-	LL.B., LL.M; Assistant Lecturer
Getachew Assefa	-	LL.B, LL.M; Assistant Professor
Girmachew Alemu	-	LL.B, M.A, Ph.D., Assistant Professor
Mandefro Eshete	-	LL.B, LL.M, Dr. Iur.; Assistant Professor
Martha Belete	-	LL.B, LL.M; Lecturer & Assistant Dean
Mehari Redae	-	LL.B, LL.M; Assistant Professor
Mekete Bekele	-	LL.B, LL.M; Assistant Professor
Mohammed Habib	-	LL.B, LL.M; Assistant Professor
Molla Mengistu	-	LL.B, M.A, LL.M; Lecturer
Muradu Abdo	-	LL.B, LL.M; Assistant Professor
Seyoum Yohannes	-	LL.B, LL.M; Lecturer
Tadesse Lencho	-	LL.B, LL.M; Lecturer
Tilahun Teshome	-	LL.B; Professor
Tsehai Wada	-	LL.B, LL.M; Assistant Professor
Wondowssen Demissie	-	LL.B, LL.M; Lecturer
Yazachew Belew	-	LL.B, LL.M; Lecturer
Yonas Birmeta	-	LL.B, M.A; Lecturer
Zekarias Keneaa	-	LLB, LL.M; Assistant Professor

Part-Time Faculty

Abraham Ayalew	- LL.B, Mphil; Lecturer
Aschalew Ashagrie	- LL.B, LL.M; Lecturer
Assefa Fisseha	- LL.B, LL.M, Ph.D.; Associate Professor
Enemanachew Yemamu	- B.SC, M.A., LL.B; Lecturer
Getahun Kassa	- LL.B, LL.M; Lecturer
Gebereamlak Gebregiorgis	- LL.B, M.A, LL.M.; Assitant Professor
Imiru Tamrat	- LL.B, LL.M; Assistant Professor
Kalkidan Negash	- LL.B, LL.M.; Lecturer
Nuru Seid	- LL.B, LL.M; Lecturer
Solomon Emiru	- LL.B, LL.M ;Lecturer
Solomon Negus	- LL.B., LL.M., Ph.D. ; Assistant Professor
Tewodros Mihret	- LL.B, LL.M; Lecturer
Tsegaye Regassa	- LL.B.,LL.M. ; Assitant Professor
Yosef Aymero	- LL.B, Lecturer
Wondimagegn Tadesse	- LL.B, LL.M; Lecturer
Yared legesse	- LL.B, LL.M; Assitant Professor



JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

The Journal of Ethiopian Law invites the submission of unsolicited articles, essays, case comments, book reviews and comments on law/legislation. The Journal also invites letters in response to articles, essays, case and legislation comments, book reviews and notes appearing in the Journal within the last year. Correspondence should be brief (about 3 pages). Selected letters will be edited with the cooperation of the author and published.

Our Address is: The Editor – in – Chief
Journal of Ethiopian Law
School of Law, Addis Ababa University
P.O.Box 1176
Addis Ababa, Ethiopia
Tel., 0111239757

The Journal of Ethiopian Law is distributed by the Book Centre of Addis Ababa University. If you wish to subscribe, please address correspondence to:

The Book Centre, Addis Ababa University,
P.O.Box 1176, Addis Ababa, Ethiopia.

TABLE OF CONTENTS

ማ ው ጫ

የፍርድ ቤት ውሣኔዎችና ትችቶች
Case Reports, Comments and Book Reviews

Book Review

David Turton (ed.), Ethnic Federalism: The Ethiopian Experience in Comparative Perspective (Eastern African Studies, James Currey, Ohio University Press and Addis Ababa University Press 2006, 246 pages)

Reviewed by Wondemagegn Tadesse

Editorial

It is trite to explain the relevance and importance of scholarly publications in expanding the frontiers of knowledge. The Journal of Ethiopian Law strives to publish writings that contribute to the dissemination of knowledge and the enrichment of the debate on the different aspects of the Ethiopian laws and legal system. All along the Journal combines theoretical and practical approaches to publish research articles that explain principles as well as commentaries on court cases that scrutinize the practice.

The research articles in this volume cover such wide-ranging subjects as insurance, speedy trial, employment of disabled persons, access to genetic resources and benefit sharing, and the criminalization and punishment of inchoate conducts and criminal participation under the anti-terrorism law of Ethiopia. This volume also contains three commentaries on court cases that focus on land use and mortgage, a note on the Ethiopian Arbitration and Conciliation Center, case reports and a book review.

I am pleased to announce that Dr. Assefa Fiseha (Associate Professor, Institute of Federalism& Legal Studies, Ethiopian Civil Service College) has joined the Editorial Board of the Journal as of July 2010. I thank Dr. Assefa and all members of the Editorial Board, the Editors and the Secretary for their efforts in the preparation and publication of the current volume. I also thank the following people who were referees for the research articles submitted for publication in the current volume: Abera Degefa, Aman Assefa, Belete Geda, Getahun Kassa, Hailu Nigatu, Kalkidan Negash, Mekete Bekele, Nuru Saaid , Mehari Redae, Samuel Asfaw, Sisay Alemahu, Dr. Solomon Ayele, Taddesse Lencho, Tewordros Mehret, Yonas Birmeta, and Wondemagegn Tadesse.

Girmachew Alemu (Ph.D.)
Editor-in-Chief

ዘካርያስ ቀነዓ*

መግቢያ

መብትና ግዴታ በስፋትና በጠባቡ ሊታዩ የሚችሉ ፅንሰ ሓሳቦች ናቸዉ። በዚህ ጽሑፍ ዉስጥ ግን መብትና ግዴታ ከሕግና ከዉል ረገድ ካላቸው ጠባብ ቴክኒካዊ ትርጉም አንፃር እንደሚታዩ ለአንባቢ ግልጽ ሊደረግ ይገባል።

መብትና ግዴታ ሁለት አብረው የሚሄዱ /ኮሪሌቲቭ/ ፅንሰ ሓሳቦች ናቸዉ። መብት ሲባል አንድ ሰው ከአንድ የተለየ ሌላ ሰው ወይም ባጠቃላይ ከአንድ ማሕበረሰብ ወይም ከአንድ ሕብረተሰብ ሊያገኝ የሚገባው ገንዘብ፣ አገልግሎት ወዘተ ሲሆን ባንፃሩ ደግሞ ለባለመብቱ እንዲደርሰው የሚፈለገውን ገንዘብ ወይም አገልግሎት ወዘተ የመስጠት የማቅረብ ግዴታ በዚያ በተለየ አንድ ሰው ላይ ወይም ባጠቃላይ በማኅበረሰቡ ወይም በሕብረተሰቡ ላይ እንደሚወድቅ እናያለን።

መብትና ግዴታ የሚመነጩት ከሕግ ወይም ከውል እንደመሆኑ መጠን በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ ውስጥ በተቻለ መጠን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ውስጥ ለመድን ውል ተዋዋይ ወገኖች የተሰጣቸውን አንዳንድ መብቶችና በዚህ አንፃር የተጣለባቸውን ግዴታዎች በመድን ውሎች ውስጥ ሰፍረው ከምናገኛቸው ጋር በማነፃፀር ለመመልከት ሙከራ ይደረጋል።

መብትና ግዴታ ከሕግ ሳይሆን ከውል በሚመነጩበት ጊዜ የግድ አዛዥ የሕግ አንቀጾችን ሳይጥሱ ወይም ሳይቃረኑ መቋቋም እንዳለባቸው ግልጽ ቢሆንም ማስታወሱ ጠቃሚ ነዉ። በዚህ ረገድ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር (ከዚህ በኋላ የፍ.ብ.ሕ.ቁ.) 1731/2/ ተዋዋይ ወገኖች ከውላቸው እንዲመነጩ የሚፈልጉትን መብቶችና ግዴታዎች አዛዥ የሕግ አንቀጾችን ሳይጥሱ ወይም ሳይቃረኑ እንደፈለጉ ማቋቋም ወይም መመሥረት እንደሚችሉ ይደነግጋል።

የዚህ ጽሑፍ ርዕስ የመድን ውል ተዋዋዮችን መብትና ግዴታ የሚመለከት ቢሆንም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ውስጥ በዚህ ርዕስ ሥር ሊነሱ የሚችሉትን ጉዳዮች ሁሉ በእንደዚህ ዓይነቱ ውስን ጽሑፍ መዳሰስ አይቻልም። ስለሆነም ይህ ጽሑፍ የቃኛቸው በርዕሱ ውስጥ ሊጠቃለሉ ከሚችሉ ጉዳዮች ጥቂቶቹን ብቻ ያዉም በንግድ ሕጉ ዉስጥ በጠቅላላ ድንጋጌነት የሰፈሩትን መሆኑን አንባቢያን ከወዲሁ እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል።

ተዋዋይ ወገኖች እነማን ናቸው?

ከመድን ሕግና ውል አኳያ "ተዋዋይ ወገኖች" ሲባል በአንድ በኩል የመድን ሽፋን እንዲሰጠው ለመድን ሰጪው አመልክቶ ማመልከቻው ወይም ጥያቄው ተቀባይነት

*ተባባሪ ፕሮፌሰር እና ተ/ዳን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ሕግ ትምህርት ቤት

ያገኘ በሕግና በፖሊሲዎች ውስጥ መድን ተቀባይ ወይም መድን ገቢ የሚባለው ወገንና በሌላ በኩል የመድን ሽፋን ለመስጠት የተዋዋለው መድን ሰጪ ብቻ መስለው ሊታዩ የሚችሉ ቢሆንም በንግድ ሕጉ ውስጥ እንደተመለከተው "ወኪል" "ፈራሚ" "የመድን ውል የተላለፈለት ሰው" መድን የተገባለት ንብረት የተላለፈለት ሰው "ወራሽ" "ተጠቃሚ" ተብለው በተለያዩ ቁጥሮች ሥር በተለያየ አገላለጽ የተጠቀሱ ሌሎችም ምናልባት ከመብትና ግዴታ አንፃር ከመድን ገቢዎች ጋር የሚደመሩ ሰዎች መኖራቸውን እንመለከታለን። በዚሁ መሠረት በንግድ ሕጉ የመድን ድንጋጌዎች ባብዛኞቹ ላይና በፖሊሲዎች ላይ መድን ገቢ፣ ተጠቃሚ፣ የመድኑ ውል ባለቤት ወዘተ በሚል አጠራር የተመለከቱት የሚናገሩት ያው ስለመድን ገቢ መሆኑን መረዳት ጥሩ ነው።[1]

የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ ከውሉ ምሥረታ ጋር በተያያዘ

የመድን ውልን ምሥረታ በሚመለከት ምንም እንኳን የመድን ውል ልዩ ውል ቢሆንምና የንግድ ሕግ ቁጥሮች 654-712 በልዩነታቸው በቅድሚያ ተፈፃሚ ቢሆኑም በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1676/1/ እና /2/ መሠረት የመድን ውሎችም ጠቅላላ ውሎችን በሚመለከቱ የፍትሕብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ይገዛሉ። በመሆኑም የውል አቀራረብና አቀባበልን የሚመለከቱ የፍትሕብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም የተዋዋይ ወገኖች የችሎታ፣ በውል ለመገደድ ፈቃዳቸውን በነፃ የመስጠት፣ የውሉ ጉዳይ ማለትም የተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎች ጥርት ባለ ሁኔታ መመልከት፣ የተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎች የሚቻሉ፣ ሕጋዊና ከንብረተቡ የሞራል ሕግ ጋር የማይጋጩ፣ እንደዚሁም ውሉ ሕግ በሚያዘው ፎርም[2] መሠረት የተቋቋሙ መሆን እንዳለባቸዉ ስናስተውል፣ ከነኚህ በሕግ ፊት የፀና ውል እንዲቋቋም አስፈላጊ ናቸው ተብለው ከሚወሰዱት ነገሮች ያንደኛው አለመሟላት አንድን የመድን ውል በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1808 እና ተከታታዮቹ ቁጥሮች መሠረት ፍርስ ወይም ፈራሽ ሊያደርገው ይችላል።

በንግድ ሕግ ቁጥር (ከዚህ በኋላ ን.ሕ.ቁ.) 654/1/ እንደተመለከተው የመድን ውል ማለት፣

- ኢንሹራንስ /መድን/ ሰጪ የሚባለው /ወገን/፣

---

[1] ከሕይወት መድን አኳያ "ተጠቃሚ" የሚለው ቃል "beneficiary" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ትርጉም ሆኖ በጠባቡ መወሰዱን መገንዘብ ያስፈልጋል።

[2] በን.ሕ.ቁ.657/1/ መሠረት አንድ የመድን ውል የመድን ውል ፖሊሲ በሚል ጽሑፍ መደገፍ አለበት። የን.ሕ.ቁ.657/2/ እንደሚደነግገዉ አንድ የመድን ውል ፖሊሲ ሊሻሽልም እንደዚሁ "ተጨማሪ ጽሑፍ" /endorsement/ በሚባል ጽሑፍ መሆን አለበት። ተጨማሪ ጽሑፍ እስከሚፈረም ድረስ መድን ሰጪው ጊዜያዊ የመድን ሽፋን መስጠቱን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ ውልም ሊሰጥ እንደሚችል በን.ሕ.ቁ. 657/3/ ላይ ተመልክቷል። በን.ሕ.ቁ. 657/3/ የሚሠጠው ሰርቲፊኬት በሌሎች አገሮች "Cover note" የሚባለው መሆኑ ነው።

- በአንድ ጊዜ ወይም ስለአከፋፈሉ በተስማሙት መሠረት ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲከፈል የተመደበውን አረቦን /ፕሪሚዬም/ ተቀበሎ፣
- በውሉ የተመለከተው አደጋ ወይም ቀን፣ ወይም ኃላፊነት በደረሰ ጊዜ፣
- መድን ለገባው ሰው ወይም ለተጠቃሚው ወይም የመድን ውል መብት ለተላለፈለት ሰው በውሉ የተመለከተው የኃላፊነት ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ በደረሰው ጉዳት ልክ ካሣ ወይም በውሉ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ውል ሲሆን፣

የውሉን ጉዳይ (object of the contract) ለይተን ለማውጣት ብንሞክር በመድን ሰጪው በኩል ስምምነት የተደረገበትን አረቦን (premium) የማግኘት ጉዳይ ሲሆን በመድን ገቢው በኩል ደግሞ የተፈራው አደጋ ወይም ጊዜ ወይም ኃላፊነት ሲደርስ የመካስ ወይም የተመለከተውን ገንዘብ የማግኘት ፍላጐት ሆኖ እናገኘዋለን።

በዚሁ መሠረት መድን ሰጪው ዋስትና ሊሰጥበት እየተዋዋለ ያለውን የአደጋውን (risk) መጠንና ሁኔታ አመዛዝኖ በስሌት የደረሰበትን አረቦን የመቀበል መብት ሲኖረው፣ መድን ተቀባዩም ይህንኑ የመክፈል ግዴታ ይወድቅበታል።

ምንም እንኳን በን.ሕ.ቁ. 659/1/ መሠረት አንድ የመድን ውል ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ ውጤት መስጠት የሚጀምረው ፖሊሲው ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ ቢሆንም በዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር /2/ መሠረት የመድን ውል ተፈፃሚነቱ የሚጀምረው የመጀመሪያው መደብ አረቦን ሲከፈል ነው ብሎ መዋዋል እንደሚቻል ተመልክቷል። ይህ ሊሆን የሚችለው መድን ሰጪው እንዲከፈለው ያለሳው አረቦን ወይ ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲከፈል ማለትም ተቆራርጦ እንዲከፈል ስምምነት ሲደረግ ወይም ውሉ ፀንቶ ለሚቆይበት ለመጀመሪያው የስምምነት ጊዜ /ዕድሳትን ሳይጨምር/ የሚከፈል አረቦን ሲሆን ነው።

በን.ሕ.ቁ. 659/2/ መሠረት የተፈረመው የመድን ውል ፖሊሲ የመጀመሪያው መደብ አረቦን እስኪከፈል ተፈፃሚነቱን ለማዘግየት መዋዋል አንዳንድ አስራካሪ ውጤቶችን ሊያስከትል እንደሚችል ይገመታል። ይኸውም በአንድ በኩል የመድኑ ውል ፖሊሲ ተጽፎ ከተፈረመ በኋላ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ መድን ገቢው መካስ ይገባኛል ብሎ መጠየቅ ይችል ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ሲያስነሳ በሌላ በኩል ደግሞ የመድኑ ውል ፖሊሲ ቢፈረምም ተዋዋዮቹ ተፈፃሚነቱ የሚጀመረው የመጀመሪያ መደብ አረቦን ሲከፈል ነው ብለው በመስማማት የመድን ፖሊሲውን ተፈፃሚነት አግደውታልና አረቦኑ ተከፍሎ እገዳው እስከሚነሳ ድረስ ውሉ ቢመሠረትም በተዋዋይ ወገኖች ላይ ውጤት አይኖረውም ማለት ይቻላል።

በሕግ ረገድ ይህ ዓይነት ስምምነት በሁኔታ መስማማት ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1871 ላይ እንደተመለከተው አንድ ውል የማቆያ ሁኔታ ተጨምሮበት የተመሠረተ እንደሆነ የውሉ ተዋዋይ ወገኖች ሌላ ተቃራኒ

ሃሳብ ካልገለፀ ውሉ ውጤት ማግኘት የሚጀምረው ማቆያ ሁኔታው ከሚፈፀምበት ቀን ጀምሮ እንደሚሆን ተደንግጓል። በን.ሕ.ቁ. 659/2/ ሥር ሠፍሮ የሚገኘውም አባባል የማቆያ ሁኔታን የሚመለከት ሆኖ መድን ሰጪውና መድን ተቀባዩ የርሱን ዓይነት ሁኔታ አስገብተው ከተዋዋሉ ውላቸው ሁኔታው እስከሚፈፀም ድረስ ውጤት መስጠት እንደማይጀምር መገንዘብ ቀላል ነው።[3]

በውሉ ምሥረታ ጊዜ በፖሊሲው ላይ ወይም በን.ሕ.ቁ. 657/3/ መሠረት በተሠጠ በጊዜያዊ የመድን ሽፋን ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ የመድን ሰጪው ግዴታ ቢጠቀስም የርሱ ግዴታ ተፈፃሚ የሚሆነው በውሰታው ላይ የተመለከተው አደጋ፣ ኃላፊነት ወይም ጊዜ ሲደርስ ብቻ ነው። የመድንን ውል ልዩ ከሚያደርጉት ጠባዮች አንዱ ውሉ በመድን ተቀባዩ ላይ ከአረቦን ክፍያ አኳያ ወዲያውኑ ተፈፃሚ የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን ለመድን ሰጪው ግን ተፈፃሚነቱ የመድን ሰጪውን ኃላፊነት የሚያስቀሩለት ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው በውሉ ላይ የተመለከተው አደጋ ወይም ኃላፊነት ወይም ጊዜ ሲደርስ ብቻ ነው።[4]

ስለዚህ በመድን ሰጪው በኩል በውሉ ምሥረታ ጊዜ የሚፈለግበት ግዴታ ባጠቃላይ አነጋገር የተፈራው አደጋ ሲደርስ ወይም በውሉ የተነገረው ጊዜ ሲሞላ ወይም ኃላፊነት ሲመጣ እክስሃለሁ ብሎ ቃል መግባት ነው ለማለት ሲቻል[5] መድን ገቢው ግን ሌሎች በውሉ ምሥረታ ጊዜ ወይም እንደሁኔታው ከምሥረታው በፊት የሚወድቅበትን ግዴታዎች ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

የመድን ሰጪውን የአደጋ አስተያየት የሚለውጡበትን ሁኔታዎች /ፍሬ ነገሮች/ መረጃዎች ስለማስታወቅ

ከመድን ውል ልዩ ጠባዮች መካከል አንደኛውና ምናልባትም ዋነኛው ተብሎ ሊጠቀስ የሚገባው ስለፍፁም ቅን ልቡና ጉዳይ ነው። የመድን ውል በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ቅን ልቦና ላይ በተለይም ደግሞ በመድን ገቢው ፍፁም ቅን ልቦና ላይ የሚመሠረት ውል ነው።

---

[3] አንድን የመድን ውል በን.ሕ.ቁ. 659/1/ ሥር በተዓፈው ዓይነት የማቆያ ሁኔታ አድርጐ መዋዋሉ ግን በተግባር ላይ አንዳንድ ችግሮችን ሊያስነሣ ይችላል። ጎላ ብሎ የሚታየው የመድን ውል ፖሊሲ ዛሬ ተፈርሞ ውጤት መስጠት የሚጀምረው ግን የመጀመሪያ መደብ አረቦን ሲከፈል ከሆነ የአረቦኑ መከፈል ውሉን ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ ውጤት እንዲሰጥ ያደርገዋል? ወይንስ አረቦኑ ከተከፈለበት ጀምሮ ወደፊት? የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል።

[4] Henry vance, Handbook of the Law of Insurance, በተሰኘዉ መጽሐፉ West Publishing Co. (1951) pp. 94-95 የሚከተለዉን አስቀምጧል: "A contract of insurance is executory and conditional. It is executory on the part of insured and conditional as regards the insurer."

[5] ይህን ስንል ግን መድን ሰጪው ከሥራው ተግባር የተነሳ ስለተፈራው አደጋ የደረሰው መረጃ ካለ ለመድን ገቢው የማሳወቅ ግዴታ የለበትም ማለት አይደለም። እ.ኤ.አ. በ1987 ላይና ከዚያም ወዲህ የፍጹም ቅን ልቡና ግዴታ በሁለቱም የመድን ውል ተዋዋዮች ላይ ተፈጻሚ መሆኑ ተረጋግጧል።

የመድን ኢንዱስትሪ እጅግ በጣም በዳበረበት በእንግሊዝ አገር ከጥንት ጀምሮ ማለትም እ.ኤ.አ. ከ1766[6] ጀምሮ የመድን ውል የቅን ልቡና ውል መሆኑ የታወቀ ሲሆን በየዘመናቱ ይኸው አስተሳሰብ ሲጠናከር የቆየበት አገር ነው ። አንዱ ታዋቂ የመድን ሕግ ምሁር እንዲህ ይላሉ፦

> The Law Relating to contracts of insurance is part of the general law of contracts. Contracts of insurance are, however, a species of that speeial class of contract, contracts of utmost good faith. Special rules therefore apply in insurance law relating to non-disclosure and misrepresentation which differ from the rules applicable to contracts generally. Otherwise there is no principle in insurance law which is repugnant to the ordinary principles of the Law of contracts.[7]

/የመድንን ውል የሚመለከተው ሕግ የጠቅላላ ውል ሕግ አንዱ ክፍል ነው። ሆኖም ግን የመድን ውሎች ልዩ ከሚባሉት የውል ዝርያዎች አንዱ ሆነው "የፍፁም ቅን ልቡና ውሎች" ከሚባለው ክፍል የሚመደቡ ናቸው። በመሆኑም የመድን ውሎችን በሚመለከት ከሌሎች ውሎች በተለየ አኳኋን ተፈፃሚ የሚሆኑ መደበቅን (መሸሸግን) እና ሐሰተኛ መግለጫን የሚመለከቱ ደንቦች አሉ። በተረፈ በመድን ሕግ ውስጥ ከሌሎች ከማናቸውም ተራ የውል መርሆችና ደንቦች ጋር የማይጣጣም መርህ የለም።/

ትርጉም የፀሐፊው/ ነው።

ሌላ በመድን ሕግ ላይ የጻፉ እንግሊዛዊ ምሁር የሚከተለዉን ያስረዳሉ፦

A Contract of insurance is the primary example of the class of contracts <u>*uberrimae fidei*</u> that is of the utmost good faith. As a result, the parties to it are bound to volunteer to each other before the contract is concluded information which is material to the risk.[8]

/የመድን ውሉ የፍፁም ቅን ልቡና ተብለው ከሚመደቡት መካከል ዋነኛው ምሣሌ ነው። ከዚህም የተነሣ የውሉ ተዋዋይ ወገኖች ውሉ ከመመሥረቱ በፊት አንዱ ለሌላኛው ሰለተፈራው አደጋ መረጃ ለመሰጠት ይገደዳል

/ትርጉም የፀሐፊው/ ሲሉ ሌሎችም በርካታ ፀሐፊዎች ስለመድን ውል የፍፁም ቅን ልቡና ውልነት በሰፊው አትተዋል።[9]

---

[6] Carter V Boehm (1766) 3 Burr. 1905.

[7] Raoul Collinvaux, <u>the Law of Insurance 5th</u> ed ,Sweet & Maxwell, London, 1984 p.11

[8] John Birds, <u>Modern Insurance Law</u>, Sweet & Maxwell, London, 1982,p.83

[9] ለምሣሌ፦ E.R. Hardy Ivamy, <u>Principles of Modern Insurance Law 4th</u> ed., Butterworths & Co., (Publishers) Ltd., London, 1986 p. 119 et seq., Merkin and McGee, <u>Insurance Contract Law</u>, Kluwer, London, 1988. (et.passim).

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ የመድን ሕግ መምህር የነበሩት ብሩን ኦቶ ብሪዴም ባጠቃላይ የንግድ ሕጉ ከፍትሕብሔር ሕጉ ጋር ተዛምዶ መታየትና መነበብ እንዳለበት ካወሱ በኋላ ለምሳሌ ያህል ስለመድን ውል ምሥረታ ብለው በመቀጠል የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1678 በሁሉም ውሎች ላይ ተፈፃሚ ነው። ለሁሉም ውሎች አስፈላጊ ተብለው በዚህ ቁጥር ሥር ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ የችሎታ ጥያቄ የሚዳኘው በፍትሐብሔር ሕግ ነው፣ የፈቃድ ጉዳይም ከሞላ ጐደል እንደዚሁ ሲሆን፣ ነገር ግን የን. ሕ. ቁ. 667 እና 668 ከፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌ የበለጡ ተንኮልንና ስሕተትን የሚመለከቱ ደንቦችን ያስቀምጣሉ በማለት ያስረዳሉ።[10]

የን.ሕ.ቁ. 667 በኢትዮጵያ የመድን ሕግ ውስጥ የቅን ልቡናን ግዴታ በመድን ገቢው ላይ ሲጥል ከዚህም አኳያ ውሉን በሚዋዋልበት ጊዜ ኢንሹራንስ ሰጪው ኃላፊነት የሚወስድባቸውን አደጋዎች ለመመዘን የሚያስችሉትን ማናቸውንም ሁኔታዎች በትክክል መግለጥ አለበት ሲል ይደነግጋል።

ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው ለማለት ባያስደፍርም[11] በመድን ሥራ ሠፊ ልምድ ባላቸው አገሮች እንደሚታመነው በን.ሕ.ቁ. 667 ሥር የተፃፈው ግዴታ መሠረቱ የሚከተለዉ አስተሳሰብ ነዉ፦

> The underwriter knows nothing and the man who comes to him to ask him to insure knows everything, it is the duty of the assured, the man who desires to have a policy, to make a full disclosure to the underwriter without being asked of all the material circumstances, because the underwriter knows nothing and the assured knows everything. That is expressed by saying that it is a contract of utmost good faith *uberrimae fides*[12]

/መድን ሰጪው የሚያውቀው ምንም ነገር የለም። መድን እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚመጣው ሰውዬ ግን ሁሉን ነገር ያውቃል፣ በመሆኑም ይህ መድን እንዲሰጠው የሚፈልገው መድን ገቢ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑትን ሁኔታዎችና መረጃዎች ሳይጠየቅ ለመድን ሰጪው በሙሉ የመግለጽ ግዴታ አለበት። ምክንያቱም መድን ገቢው ሁሉን ነገር ያውቃል፣ መድን ሰጪው ግን የሚያውቀው ምንም ነገር የለም። ይህም የመድን ውል የፍጹም ቅን ልቡና ውል ነው። ፍጹም ቅን ልቡና በሚል አገላለጽ ይጠቃለላል። /ትርጉም የፀሐፊው/

---

[10] Brun Otto Bryde. Insurance Law, unpublished, Faculty of Law, Haile Selassie I University, (1983), p.104.

[11] መድን ገቢው የሚያውቃቸውን ወይም ማወቅ ይገባዋል ሊባሉ የሚችሉትን ፍሬነገሮች /facts/ መድን ሰጪውም ሊያውቃቸው ይችላል። በተለይም ከመድን ሰጪው ሙያ አንፃር ሊያውቃቸው ይገባል የሚባሉት ፍሬነገሮች ቁጥራቸው በርካታ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። እንደዚሁም ማንም ሰው የሚያውቀውን ፍሬነገር መድን ገቢው አልገለፀም ተብሎ ክርክር ሊቀርብበት አይገባም።

[12] Rozan V Bowen (1982) 32 LIL Rep. 98 at 102

እንግዲህ በን.ሕ.ቁ. 667 ሥር የሠፈረው አባባልም የመጣው መድን ስለሚገባለት ንብረት፣ ሰው ወይም አደጋ የሚያውቀው መድን ጠያቂው ነው ከሚል እምነት ነው ቢባል ስሕተት አይመስለኝም።

በን.ሕ.ቁ. 667 መሠረት መድን ገቢው መግለጽ የሚገባው ሁሉንም መድን የሚጠየቅለትን ንብረት፣ ወይም ሰው፣ ወይም አደጋ የሚመለከቱትንና እርሱ የሚያውቃቸውን ፍሬነገሮች ቢመስልም ነገር ግን መወሰድ ያለበት በመድን ጠያቂው በኩል መገለጽ ያለባቸው ፍሬነገሮች መድን ሰጪው ኃላፊነት እንዲወስድባቸው የሚፈለጉትን አደጋዎች ለመመዘን የሚያስችሉትን ማናቸውንም ፍሬነገሮችን[13] ነው እንጂ ሁሉንም መድን ገቢው የሚያውቃቸውን ፍሬነገሮች አይደለም።

እንደ ኤዉሮፓ አቆጣጠር በ1906 ዓ.ም. በወጣዉ የእንግሊዝ ማሪን ኢንሹራንስ አክት በአንቀጽ 18(2) እና 20(2) መሠረት የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ማለት፦ "Any fact which would influence the judgment of a prudent insurer in fixing the premium or determining whether he will take the risk"[14] ነዉ። ይህ በግርድፉ "ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ማለት ማንኛዉም አንድ አመዛዛኝ መድን ሰጪ የሚያስከፍለዉን አረቦን ወይም መድን ሽፋን በመስጠት ሓላፊነትን የሚወስድበትን አደጋ የሚመለከት ፍሬነገር ማለት ነዉ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

በኢትዮጵያ የመድን ሕግ ውስጥ የትኞቹ ፍሬ ነገሮች አስፈላጊና ዋነኛ የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች (material facts) ሊባሉ እንደሚችሉ በግልጽ የተሰጠ ትርጓሜ ወይም ማብራሪያ የለም። የንግድ ሕጉ ሲረቀቅ በነጊህ በን.ሕ. ቁ. 667 እና 668 በስተጀርባ የነበረዉን አስተሳሰብ ፒተር ዊንሺፕ ጠቅለል አድርገዉ እንደሚከተለዉ ይገልጹታል፦

> On the question of facts concealed and false statements, I have included the more nuanced sanctions found in the French law rather than the solutions set out in the Maritime Code, which are perhaps too rigorous.[15]

---

[13] በመሠረቱ አንድ መድን ገቢ መግለጽ የሚጠበቅበት ፍሬነገሮችን (facts material, material facts)እንጂ የመድን ገቢዉን የግል አስተያየት(opinion)አለመሆኑን አንባቢ ልብ ሊል ይገባል። ለአንዳንድ የመድን ዉሎች ምናልባት የመድን ገቢዉ አስተያየት ሊጠየቅ ወይም ሊፈለግ ይችል ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ መድን ገቢዉ በሚሞላዉ ፎርም መጨረሻ ላይ የማዉቀዉንና የማምነዉን ያህል በፎርሙ ላይ የሰጠሁት መረጃ ትክክል ነዉ ከማለት በስተቀር ለሰጣቸዉ መረጃዎች ትክክለኝነት ማረጋገጫ ወይም ዋስትና ሊሰጥ አይችልም። በተጨማሪም አንባቢ ከዚህ በታች በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 7 ላይ የተጠቀሰዉን መጽሃፍ ከገጽ 98-101 እንደዚሁም ገጽ 104 እና 140ን ይመልከት።

[14] Sections 18(2) and 20(2) of the English Marine Insurance Act of 1906

[15] Peter Winship, (editor and translator) Background Documents of the Ethiopian Commercial Code of 1960, Faculty of Law , Haile Selassie I University, Addis Ababa, 1974 p. 83

የተሸሸጉ እና በትክክል ያልተገለጹ ፍሬነገሮችን ጥያቄ በተመለከተ በባሕር ሕግ ዉስጥ የተካተቱትን ጠበቅ ያሉ መፍትሔዎችን ከመዉሰድ ይልቅ በፈረንሳይ ሕግ ዉስጥ የሚታዩትን ረቀቅ ብለዉ ላላ ያሉትን የማስገደጃ ስልቶችን አካትቻለሁ (ትርጉም የፀሓፊዉ)።

በኢትዮጵያ የባሕር ሕግ ቁጥር 300 ላይ "ስላለመግለጽና አለተኛ መግለጫ ስለመስጠት" በሚል ረዕስ የሚከተለዉ ተደንግጓል፦

(1) ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ ሳይገልጽ መቅረቱ ወይም አለተኛ የሆነ መግለጫ መስጠቱ ምንም እንኳ በማታለል መንፈስ የተደረገ ባይሆን ለመድረስ በሚያስጉ አደጋዎች (ሪስክ) ላይ ኢንሹራንስ አድራጊዉ ያለዉን አስተያየት የሚቀንሱ ከሆኑ የኢንሹራንሱን ዉል የሚያፈርሱ ናቸዉ።
(2) ሳይገለጽ መቅረቱ ወይም በሃሰት የተሰጠዉ መግለጫ ኢንሹራንስ በተደረገለት ዕቃ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ወይም መጥፋት ምክንያት ሆኖ ባይገኝም እንኳ የኢንሹራንሱን ዉል ፈራሽ ነዉ።
(3) ኢንሹራንስ የተደረገለት ሰዉ የማታለል ሃሳብ አሳይቶ እንደ ሆነ በኢንሹራንስ የተከፈለዉ ዋጋ (ፕሪሚየም) በሞላዉ የማታለል መንፈስ የሌለ እንደሆነ በግማሽ የኢንሹራንስ አድራጊዉ ገንዘብ እንደሆነ ይቀራል።

በእርግጥም በባሕር ሕጉ ላይ የተደነገገዉ ጠበቅ ያለ መመዘኛ ነዉ። መመዘኛዉ ለመድን ሰጪዎች ጥሩ ሊሆን ሲችል ለመድን ገቢዎች ግን ከበድ ያለ ዉጤት ይኖረዋል። የባሕር ሕጉ ድንጋጌ ጠበቅ ያለ ስለመሆኑ በተለይም በእንግሊዝኛ ቅጂ ላይ በግልጽ ይታያል።[16]

ወደ ንግድ ሕጉ ስንመለስ በቁ. 667 ሥር የተመለከተውና "መድን ሰጪው ዋስትና እንዲሰጥባቸው የሚፈለጉትን አደጋዎች ለመመዘን የሚያስችሉትን ማናቸውንም ፍሬነገሮች" የተሰኘው አባባል በኢትዮጵያ ሕግ የማቴሪያሊቲ (ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች) መለኪያ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

በን.ሕ.ቁ. 668 /1/ ሥር "እውነተኛው ነገር ተገልጾለት ቢሆን ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው ይህን ውል አይዋዋልም ወይም ተጠቃሚው ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍል የሚያደርግበት ውል ይዋዋል ነበር እስከሚያስኝ ድረስ እነኚህ የተሸሸጉ ነገሮች ወይም በሐሰት የተሰጡ መግለጫዎች የመድን ሰጪውን አስተያየት ለውጠውበት እንደሆነ ነው ..." ተበሎ የገባውም አባባል እንደ ማቴሪያሊቲ መመዘኛ ሊወሰድ ይችላል።

---

[16] Sub-article (1) of Art. 300 of the 1960 Maritime Code of Ethiopia provides: "Any concealment or misrepresentation on the part of the assured, by which the risk insured has been underestimated, shall result in the cancellation of the policy, even in the absence of fraud"

ይህንንም ለማለት የሚያስችለው ተደበቀ ወይም በሐሰት ተገለፀ የሚባለው ፍሬነገር ማንኛውንም መድን ገቢው የመድን ሽፋን እየጠየቀለት ስላለው አደጋ ወይም ሰው ወይም ንብረት የሚያውቀውን ፍሬነገር ሳይሆን የመድን ሰጪውን ያደጋ አስተያየት ሊለውጥበት ይችል የነበረውና የተደበቀው ቢታወቅ ኖሮ ወይም ትክክለኛው ፍሬነገር ቢገለጽ ኖሮ ወይ ለተፈራው አደጋ ዋስትናውን ከመስጠት ይቆጠብ ነበር ወይም ዋስትናውን ለመስጠት ፈቃደኛ እንኳን ቢሆን አስከፍሎ ከተዋዋለው ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው አረቦን የበለጠ ያስከፍል ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ሲሆን ነው።

ሌላው መነሣት የሚያስፈልገው ነጥብ በኢትዮጵያ የመድን ሕግ አንድ ፍሬነገር የአደጋ አስተያየት ሊያስለውጥ የሚችል /ማቴሪያል ፋክት/ ነው አይደለም ብሎ ለመወሰን ሕጉ ሥልጣን /መብት/ የሰጠው የመድን ሽፋን እንዲሰጥ ጥያቄ እየቀረበለት ላለው ለዚያው መድን ሰጪ ይመስላል።[17] በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ የመድን ሕግ አንድን የተሸሸገን ወይም በትክክል ያልተገለፀን ፍሬነገር ያደጋ መመዘኛ አስፈላጊ ፍሬነገር ነው አይደለም ለማለት የሚችለው ያው ጥያቄ የቀረበለት መድን ሰጪ እራሱ ነው እንጂ አንድ መድን ሰጪ ተደበቀ የተባለውን ወይም በትክክል አልተገለፀም የተባለውን ፍሬነገር እንደአስፈላጊ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ይወሰደዋል ወይንስ አይወሰደውም? በሚል አብጀክቲቭ መለኪያ እንደማይሄድ ነው ይህንንም የሚያስብለዉ የን.ሕ. ቁ. 667 ድንጋጌ ራሱ ሲሆን የሚለዉም "ዉሉን በሚዋዋልበት ጊዜ ኢንሹራንስ ገቢዉ የሚያዉቃቸዉን ማናቸዉንም ሁኔታዎችና ኢንሹራንስ ሰጪዉ ኃላፊነት የሚወስድባቸዉን አደጋዎች ለማመዛዘን የሚያስችሉትን ማናቸዉንም ሁኔታዎች በትክክል መግለጥ አለበት" ነዉ። ፍ/ቤቶች አብጀክቲቭ መለኪያ እንጠቀማለን ቢሉ እንኳ ይህን ማድረጉ የማይቻልበት ወቅት ነበረ።[18]

ፕሮፌሰር አይቫሚ በእንግሊዝ አገር በሥራ ላይ ያለውን መለኪያ እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> The test which is usually adopted is whether the non-disclosure of the facts would influence a "prudent" insurer

---

[17] In a note published in Michigan Law Review, Vol.25 (1927) p. 469, it was stated: "The Insured's non-disclosure (misrepresentation) being material will be assumed to have influenced the insurer to assume the risk, to have induced him to enter into a contract which he would otherwise have declined or to take a less premium then he would otherwise have demanded."

[18] ከ 1967 እስከ 1983 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ መድን ሰጪ ብቻ (የኢትዮጵያ መድን ድርጅት) በነበረበት ሁናቴ ፍርድ ቤቶች አንድ reasonable insurer ተደበቀ የተባለውን ወይም በትክክል አልተገለፀም የተባለውን ፍሬነገር እንደአስፈላጊ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ያየዋል አያየውም? የሚለውን ለማጣራት /theoretically and fictitiously/ ካልሆነ በስተቀር ይችሉ እንዳልነበረ ግለጽ ነው። ከዚህም ሌላ በተቻለ መጠን ፍርድ ቤቶች አብጀክቲብ መለኪያ ወደመጠቀም ቢያዘነብሉ የተሻለ ነው የሚል ግምት አለ።

(though in some cases the term "reasonable" has been substituted for "prudent") Another test is whether a "reasonable" assured would consider them material…In no case is it relevant to consider whether the non- disclosure would influence the particular insured concerned or whether the assured himself sought that the facts were material. [19]

ምንም እንኳን አንዳንዴ "አመዛዛኝ" የሚለውን ቃል ቢጠቀሙበትም ብዙ ጊዜ የሚወሰደው መለኪያ /መመዘኛ/ መደበቁ የአንድን "ጠንቃቃ" መድን ሰጪ ያደጋ አስተያየት ይነካ ወይም ያሰቀይር እንደሆነ ነው። ሌላኛው መለኪያ ደግሞ አንድ "አመዛዛኝ" መድን ገቢ የተደበቁትን ፍሬነገሮች እንደ ማቴሪያል ይወስዳቸው እንደሆነ ሲሆን ... መቸውንም ቢሆን የተደበቀው ፍሬነገር የመድን ሽፋን እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበለት የተለየውን መድን ሰጪ ውሳኔ ይነካል ወይም ያስቀይረዋል ብሎ መውሰድ አግባብነት የለውም። መድን ገቢውም ራሱ በግሉ የተደበቁት ፍሬነገሮች ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች ናቸው ወይስ አይደሉም ይበል ተብሎም አይወሰድም/ ትርጉም የፀሐፊው ነው።

ሌላው በኛ ሕግ ውስጥ በግልጽ ያልተመለከተው በን.ሕ.ቁ. 667 ሥር የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ያለበት መድን ገቢ የትኞቹ ፍሬነገሮች ያደጋ መመዘኛ ናቸው ብሎ ማለት ያለበት እርሱ ነው ወይንስ መድን ሰጪው ወይንስ ሁለቱም ናቸው የሚለው ጥያቄ ሲሆን ይህም አከራካሪ ሲሆን እንደሚችል መገንዘቡ መልካም ነው።

መድን ገቢው በን.ሕ.ቁ. 667 ላይ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ ሲቀር ምን ውጤት እንደሚከተል በን.ሕ.ቁ. 668 ላይ ተመልክቶአል። በዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ተጽፎ እንደምናነበው መድን ገቢው "ሆነ ብሎ"[20] የመድን ሰጪውን የአደጋ አስተያየት ሊለውጥበት የሚችል ፍሬነገር /ማቴሪያል ፋክት/ ደብቆ ከተገኘና የተደበቀው ፍሬነገር ቢገለጽ ኖሮ ወይም በትክክል ተገልጾ ቢሆን ኖሮ መድን ሰጪው ወይ የመድን ዋስትናውን የመስጠት ግዴታ ውስጥ አይገባም ነበር ወይም ዋስትናውን ለመስጠት ፈቃደኛ እንኳን ቢሆን አስከፍሎ ከተዋዋለው አረቦን በላይ ያስከፍል ነበር ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው በላይ ለማስከፈል ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ከሆነ ውሉ ፍርስ እንደሚሆንና መድን ሰጪውም የተቀበለውን አረቦን እንደሚያስቀር ተደንግጓል።

---

[19] Ivamy፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ ገጽ 126 ።

[20] ሕጉ "እያወቀ" ነው የሚለው። ይህ አባባል ግን በሕጉ ላይ ከተመለከተው ውጤት አኳያ ሲታይ ብዙም ትክክል አይመስልም። ሆነ ብሎ የሚያውቁትን ነገር መደበቅ ወይም በሐሰት መግለጽ ግን fraud /ተንኮል/ ያለበት መሆኑን ያመለክታል።

በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 637/81 በይግባኝ ባይ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና በመልስ ሰጭ በወ/ሮ አዳነሽ አድማሱ (የእነ መሠረት ከተማ ሞግዚት) መካከል በተደረገዉ ክርክር ሟች የመልስ ሰጭ ባለቤት አቶ ከተማ ገ/መስቀል ለሞት የሕይወት መድን ዋስትና ሲገዙ በሞሉት መግለጫ ላይ የጉበት በሽታ የለብኝም ብለዉ ሞልተዉ በጉበት ሕመም ሕወታቸዉ ካለፈ በኋላ መድን ሰጪዉ ሟቹ የጉበት ሕመም እንዳለባቸዉ እያወቁና ለዚህ ህመም ህክምና እየተደረገላቸዉ መሆኑን እያወቁ በሞሉት መግለጫ ላይ የጉበት በሽታ የለብኝም ማለታቸዉ የመድን ሰጪዉን የአደጋ አስተያየት ሊያስለዉጥ የሚችል እዉነት መደበቅ ስለሆነ ከሃላፊነት ነጻ እንደሚያደርገዉ ተከራክሮ ረትቶበታል። በዚህ መዝገብ ላይ በዋናነት ክርክር የተካሄደዉ መድን ሰጪዉ ዉሉ ፍርስ ስለሆነ ሓላፊነት የለብኝም የሚለዉን ክርክር ሟች መድን ገቢ በሕይወት እያሉ ሊያነሳ ይችል እንደሆን እንጂ የመድን ገቢ ሕይወት ካለፈ በኋላ ማንሳት አይችልም የሚል ክርክር እንደነበረ አንባቢያን ማወቃቸዉ መልካም ነዉ።[21] በተመሳሳይ መልኩ በ1994 ዓ.ም. በከሳሽ በአቶ አዲሱ ተመስገን እና በተጠሪ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት መካከል በግልግል ዳኝነት ጉባዔ ፊት ተካሂዶ በነበረዉ ክርክር ይሸዉ ሀሰተኛ መግለጫ የመስጠት ጭብጥ ተነስቶ የግልግል ዳኝነት ጉባዔዉ ጉዳዩን በአምስት ፓራግራፎች እንደሚከተለዉ ገልጾታል፦[22]

> አንድ መድን ገቢ የመድን ዉል በሚዋዋልበት ጊዜ የፍጹም ቅን ልቦናን (utmost good faith) መሠረት በማድረግ ዋስትና እንዲገባለት ለተጠየቀዉ ንብረት የሚያዉቀዉን ሁሉ ተጠይቆም አስጠይቆም መግለጽ እንደሚጠበቅበት የንግድ ሕግ ቁጥር 667 ይደነግጋል።
>
> በንግድ ሕግ ቁጥር 668(1) መሠረት የመድን ዉል የገባዉ ሰዉ እያወቀ እዉነተኛውን ነገር የሸሸገ ወይም የሃሰት መግለጫ የሰጠ እንደሆነ እዉነተኛው ነገር ተገልጾለት ቢሆን ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው ይህን ዉል አይዋዋልም ወይም ከፍ ያለ አረቦን አስከፍሎ ይዋዋል ነበር እስከሚያስኝ ድረስ እነዚህ የተሸሸጉ ነገሮች ወይም በሃሰት የተሰጡ መግለጫዎች የኢንሹራንስ ሰጪውን የአደጋ አሰተያየት ለዉጠዉበት እንደሆነ ዉሉ ፍርስ ነዉ። እንደ እንግሊዝኛው ቅጂ "the policy shall be of no effect" ኢንሹራንስ ሰጪውም ተከፈለዉን አረቦን ያስቀራል።
>
> ከሳሽ ዋስትና ለተገባላቸዉ ማሽኖች መግዣ የተሰጠ ብድር በሰጣቸዉ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ አማካይነት እ.አ.አ 01/05/93 እና እ.አ.አ 13/2/96 በተጻፈ የመድን መግቢያ መጠየቂያ ቅጽ ላይ የማሽኖች ዋጋ ብር

---

[21] በ1989 ዓ.ም በ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥናት ምርምርና ሕትመት መምሪያ ታትሞ ወጥቶ የነበረዉን የፍርዶች መጽሐፍ ቮልዩም አንድ ከገጽ 49-51 ይመልከቱ።

[22] የኢትዮጵያ አርቢትሬሽን ኤንድ ኮንሲሊዬሽን ሴንተር <u>የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዎች</u>፤ ፭ኛ መጽሐፍ፣ገጽ 195 እና 196።ከላይ ከተመለከቱት ሁለት ዉሳኔዎች በተጨማሪ አንባቢያን የአዲስ አበባ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 84/89፤02188 የሰጣቸዉን ዉሳኔዎች እንደዚሁም ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ድሬደዋ ምድብ ችሎት በፍ/መ/ቁ 01798 የሰጠዉን ዉሳኔ መመልከት ይችላሉ

92,820 (ዘጠና ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ብር) እና ብር 282,705 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አምስት ብር) መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ በኋላ በአደጋ ወቅትም ቢሆን ማሽኖቹ አዲስ የተገዙ ናቸዉ በማለት ከሃግቤስና ጀኔራል መርካንታይል ከተባሉ ኩባንያዎች ደረሰኞች አቅርበዋል። ከነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳዉ ከሳሹ ዋስትና እንዲገባላቸዉ የጠየቁላቸዉ ማሽኖች አዲስ ናቸዉ በማለት የመድን መግቢያ ጥያቄ ማቅረባቸዉን ነዉ። ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነዉ አደጋ ከደረሰ በኋላ ተከሳሽ ድርጅት ጉዳቱን አስመልክቶ ተገቢዉን ምርመራ (ሰርቬይ) ለማድረግ በቦታዉ የተገኘ ሲሆን በምርመራዉ ወቅት የተገኘዉ ሪፖርት እንደሚያመለክተዉ ማሽኖቹ በፍጹም አዲስ አይደሉም። ይህም ሁኔታ አጠራጥሮት ከሳሹ ድርጅት ደረሰኝ ካቀረበባቸዉ ከሃግቤስና ጀኔራል መርካንታይል ኩባንያዎች ዕቃዎቹን አስመልክቶ ለሺያጩ መረጃ ሲጠይቅ ሁለቱም ኩባንያዎች ያረጋገጡት ማሽኖቹ ለከሳሹ አለመሸጣቸዉንናቀረቡ የተባሉት ደረሰኞችም በነርሱ በኩል ያልተዘጋጁ መሆናቸዉን ነዉ። ስለሆነም ከሳሹ አሮጌዎችን አዲስ የተገዙ በማስመሰል ዋስትና ገብተዋል። በዚህ ሁኔታ መድን ሰጪዉን የአደጋዉን ግምት አሳስተዉበታል። ይህም ድርጊታቸዉ ከላይ በጠቀስነዉ የንግድ ሕግ ቁጥር 667 መሠረት የሚጠበቅባቸዉን የፍጹም ቅን ልቦና ተጻራሪ ነዉ። ይህ ከላይ የተገለጸዉ የፍጹም ቅን ልቦና መርህ በመድን ገቢዎች ተጥሶ እዉነተኛዉ ነገር የተሸሸገ ወይም ሃሰት መግለጫ የተሰጠ እንደሆነ መድን ሰጪዉም እዉነቱን ቢያዉቅ ኖሮ አይዋዋልም ወይም ከፍ ያለ አረቦን ሊያስከፍል ይችላል የሚያስብል በመሆኑና ከሳሹ የሰጡት መግለጫ የመድን ሰጪዉን የአደጋ አስተያየት የለወጠበት በመሆኑ ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር አለኝ የሚሉት የመድን ዉል በንግድ ሕግ ቁጥር 668 ንኡስ ቁጥር 1 መሠረት ፍርስ ነዉ። በመሆኑም ተከሳሽ ለደረሰዉ አደጋ በመድን ሕግ መሠረት ኃላፊነት የለበትም።

በመሆኑም በንግድ ሕግ ቁጥር 668(1) መሠረት የመድን ዉሉ ፍርስ (of no effect) ስለሆነና እንዲህ ዓይነት ዉሎች በተለየ ሁኔታ ከመጀመሪያዉ (ከመመስረታቸዉ) ጀምሮ ዉጤት የሌላቸዉ ወይም እንዳልተቋቋሙ የሚቆተሩ ናቸዉ። ስለዚህ የመድን ዉሉ ፍርስ ስለሆነ ከሳሽ የሚጠይቁት ካሳ የለም።

የን.ሕ.ቁ. 668/1/ የእንግሊዝ ቅጂ "It shall be of no effect" ነው የሚለው ይህ አባባል ደግሞ "ፍርስ ነው" ከሚለው የበለጠ ጠበቅ ያለ ይመስላል። በእንግሊዝኛው ቅጂ ከተሄደ የተደበቀ ወይም በሐሰት የተገለጸ ፍሬነገር ኖሮ ሁኔታው በን.ሕ.ቁ. 668/1/ እንደሚሸፈን ከተረጋገጠ በመድን ገቢውና በመድን ሰጪው መካከል

የተመሠረተው ውል ምንም ውጤት እንደሌለው ነው የሚናገረው::[23] በቁጥር 668/1/ የአማርኛው ቅጂ አባባል ከተሄደ ውሉ ይፈርሳል:: /"ፍርስ ነው" የሚለው አባባል "ይፈርሳል" ከሚለው የተለየ ትርጉም ይሰጣል ካልተባለ/ ውሉ የሚፈርስ ከሆነ ደግሞ ተዋዋይ ወገኖች በተቻለ መጠን ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ የመመለሳቸውን ውጤት ያስከትላል::[24] ምናልባት "It shall be of no effect" የሚለው አባባል "Void ab initio"ከሚለው የላቲን አባባል ጋር ይመሳሰል ይሆናል::ይህ ከሆነ ደግሞ ውሉ በሕግ ፊት ጨርሶ እንዳልኖረ፣ እንዳልተመሠረተ ይቆጠራል ያሰኛል::

በሌላ በኩል ግን "ፍርስ ነው" ቢባል ወይም "ይፈርሳል" ወይም "ፈራሽ" ነው ቢባል ምንም ልዩነት አያመጣም ሊባል ይቻል ይሆናል:: ውጤቱ ዞሮ ዞሮ በተቻለ መጠን ተዋዋይ ወገኖችን ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ የመመለስ ሲሆን ከውሉ ሊመነጩ ይችሉ የነበሩት ግዴታና መብቶች አይመነጩም ማለት ነው ተብሎ ሊወሰድም ይቻላል::[25] ሆኖም ግን በን.ሕ.ቁ 668/1/ ሥር የተመለከተውን ልዩ የሚያደርገው ሌላው ሁኔታ መደበቁ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መሰጠቱ ሆን ተብሎ መደረጉ ሲረጋገጥና ከዚህም የተነሣ ውሉ ፍርስ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖች በተቻለ መጠን ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ መመለሳቸው መቅረትና መድን ሰጪውም የተቀበለውን አረቦን ማስቀረቱ ነው::[26]
የመድን ሰጪው የተቀበለውን አረቦን ማስቀረት ራሱ ተዋዋይ ወገኖች ዉሉ ፍርስ ነዉ ሲባል ከዉሉ ምስረታ በፊት ወደ ነበሩበት ያለመመለሳቸዉን ያሳያል::

ምናልባት አረቦኑ እንዳይመለስ የተከለከለው መድን ገቢው ከፈጸመው ማታለል የተነሳ በመድን ሰጪው ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለማካካስ ሊሆን ይችላል:: በዚያውም አታላዩን በገንዘብ ለመቅጣትም ሳይሆን አይቀርም:: ይህ ድርጊት

---

[23] በአማርኛ የፍትሐብሔር እና የንግድ ህጎቻችን ዉስጥ አገልግሎት ላይ ዉሰዉ የምናነባቸዉ አንዳንድ ቃላት በህጎቹ የእንግሊዝኛ ቅጂ ዉስጥ ከሚሰጡት መልዕክት የተለዩ መሆናቸዉን አንባቢያን ልብ ሊሉ ይገባል:: ለምሳሌ በእንግሊዝኛዉ ቅጂዎች "void" "voidable" ተብለዉ ልዩነት ባለዉ መልኩ ሲቀመጡ በአማርኛ ቅጂዎች ላይ ግን ልዩነቶቹ ብዙም ግልጽ አይደሉም:: እንደዚሁ በእንግሊዝኛዉ ቅጂዎች ዉስጥ "invalidation" እና "cancellation" ተለይተዉ ሲቀመጡ በአማርኛ ቅጂዎች ላይ ግን በሁለቱ መካከል ልዩነት እንደሌለ ተደርጎ ተጽፏል:: ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችም ሊኖሩ ይችላሉ::

[24] የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1815::

[25] በሕግ ፊት እንዳልተመሠረቱ እንዳልኖሩ የሚቆጠሩ 'Void ab initio" የተሰኙ ውሎች ምናልባት unenforceable ስለሆኑ በፍርድ ቤት እንዲፈርሱና ተዋዋይ ወገኖች በተቻለ መጠን ከውሉ በፊት ወደ ነበረበት ቦታ ይመለሱ ለማለትም አይቻልም ይሆናል::

[26] በዚህ ጹሑፍ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 ላይ እንደተገለፀው አንድ የመድን ውል በመድን ገቢው ላይ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ሲሆን በመድን ሰጪው ላይ ውጤት የሚኖረው ግን የተፈራው አደጋ ወይም ጊዜ ሲደርስ ወዘተ ስለሆነ በውሉ ምሥረታ ጊዜ ወይም ከዚያ ቦኋላ ለመድን ገቢው ተሰጥቶት መድን ገቢው ውሉ በመፍረሱ ምክንያት የሚመልሰው ነገር የለውም::

በወንጀልም ያስቀጣል።[27] መድን ሰጪው አረቦን ማስቀረት ብቻ ሳይሆን በን.ሕ. ቁ. 668 ሥር የሰፈረዉ ሁኔታ ሲያጋጥም በወንጀልም ሊያስቀጣ ይችላል።

የመድን ገቢው ሆን ብሎ ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት ወይም መሸሸግ መድን የተገባለት አደጋ ከመድረሱ በፊት ወይም በኋላ ቢታወቅ የተለያየ ውጤት ስለማስከተሉ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ላይ የተመለከተ ነገር የለም። ሕጉ በዚህ ረገድ ፀጥ ቢልም ሆን ብሎ መሸሸጉ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መሰጠቱ መድን የተገባለት አደጋ ከደረሰ በኋላ ቢታወቅ በቁ. 668/1/ የተመለከተውን ውጤት አያስከትልም ብሎ መገመቱ በአንድ በኩል የዋህነት ሲሆን በሌላ በኩል ሕጉ ሊጠብቀው የፈለገውን (public policy) ዝቅ ማድረግ ነዉ። ስለሆነም ያንድ መድን ገቢ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ሆን ብሎ ደብቆ መገኘት ወይም ሆን ብሎ በሐሰት መግለጽ የተደረሰበት ተፈርቶ መድን የተገባለት አደጋ ከመድረሱ በፊት ይሁን በኋላ ምንም ለውጥ አያመጣም። ውጤቱም ያው በን.ሕ.ቁ.668/1/ ሥር የተጻፈውና ከዚህ በላይ ያየነው ይሆናል።

መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ሊሆኑ የሚችሉትን ፍሬነገሮች የደበቀው ወይም በሐሰት የገለጸው ሆነ ብሎ በተንኮል መድን ሰጪውን ለማሳሳት ካልሆነ ውጤቱ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር ከተመለከተው የተለየ ነው። ውጤቶቹ በን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተጻፉት ይሆኑና በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ከተመለከተው ለዘብ ያሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። የንዑስ ቁጥር /2/ አነጋገር ራሱ ቁልጭ አድርጎ እንደሚያመለክተው ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን መሸሸጉ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መስጠቱ ሆን ተብሎ ያልተደረገ ከሆነና መድን ሰጪውም ሆን ተብሎ መደረጉን ማስረዳት ካልቻለ ውሉ አይፈርስም።

የን.ሕ.ቁ. 668/2/ አነጋገር ሁለት ዋና ዋና ነጥቦችን ይዟል። 1ኛ/ለውሉ ፍርስ መሆን ወይም አለመሆን መለኪያው መሸሸጉ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መሰጠቱ ሆን ተብሎ መደረጉ ወይም አለመደረጉ መሆኑን፤እና 2ኛ/መደበቁ ወይም በሐሰት መገለጹ ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን ማስረዳት ያለበት መድን ሰጪው መሆኑን ነው።

---

[27] ሆን ተብሎ በራስ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ከመድን ውል ነገር በተያያዘ የማጭበርበርና የተንኮል ሥራ በ1949 ዓ.ም. ሥራ ላይ በነበረዉ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 659 መሠረት ያስቀጣ ነበር። በ19977ዓ.ም. በወጣዉ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 698(1) ላይ ደግሞ **እንሹራንስ በሚመለከት የሚፈፀም የአታላይነት ድርጊት** በሚል ርዕስ እንደሚከተለዉ ተደንግጓል። " ማንም ሰዉ የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ፦

ሀ/ኢንሹራንስ የተገባበት አደጋ በመፍጠር፣ ወይም

ለ/በዉሉ ዉስጥ በተገለፀዉ ጥቅም ላይ ተጽዕኖ በሚያደርግ አኳኋን ኢንሹራንሱን ገንዘብ ልክ የዉሉን ዘመን ወይም የኢንሹራንስ ተጠቃሚዎችን በሚመለከት ፍሬነገር በመደበቅ፣ በማሳሳት፣በማረጋገጥ፣ወይም ይህንኑ በሚመለከት ሀሰተኛ መግለጫ በመስጠት አንድ የኢንሹራንስ ማሕበርን ያታለለ እንደሆነ.....በቀላል እሥራት ወይም ሁኔታዎቹ በይበልጥ ከባድ ሲሆኑ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ሃምሳ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል....።

ለውሉ "ፍርስ" መሆን ወይም አለመሆን የተሰኘውን አባባል ትንሽ ማየት ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፣ ምክንያቱም የን.ሕ.ቁ.668 ንዑስ ቁጥር/2/ "ውሉ አይፈርስም" የሚል አነጋገር ነው የተጠቀመው። በሌላ በኩል በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ያለው አባባል ግን "ፍርስ ነው" የሚል ነው። በቁ. 668 ንዑስ ቁጥር /2/ የተመለከተዉ በሕግ ጣልቃ ገብነት ዉሉ "ፍርስ" ወይም "of no effect" አለመሆኑን ለማመልከት ይመስላል። በመሆኑም "ውሉ አይፈርስም" ከሚለው አነጋገር የበለጠ የሕግ አውጪውን ፍላጐት ሊገልጽ ይችል የነበረው "ውሉ ፍርስ አይሆንም" የሚለውን አባባል ቢጠቀምበት ኖሮ ነበር ቢባል ስሕተት አይመስለኝም።

የን.ሕ.ቁ. 668/2/ "ውሉ አይፈርስም" ወይም በእንግሊዝኛው አነጋገር "ውሉ ፀንቶ ይቆያል" ይበል እንጂ ውሉ ሊቋረጥ እንደሚችል በዚሁ ንዑስ ቁጥር ሥር በ/ሀ/ ላይ ተመልክቶአል። ይህም የሚያሳየው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል እስከሚቋረጥበት ጊዜ ድረስ በሕግ ፊት የፀና ውል እንደኖረ የሚያስረዳ ሆኖ ሐሰተኛ መግለጫ መሰጠቱ ወይም የተደበቀ የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር መኖሩ ተደርሶበት ውሉን መድን ሰጪው ለማቋረጥ ወስኖ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ ውለታው ውጤት እንደሚኖረው ነው። ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ተሽከርካሪውን ለግጭት አደጋ በ 2002 ዓ.ም. መጀመሪያ በመስከረም ወር ላይ ለብር 120.000 ለአንድ ዓመት መድን ቢያስገባና በጎዳር ወር በዚያው ዓመት በተሽከርካሪው ላይ ትንሽ የግጭት ጉዳት ደርሶበት መድን ሰጪው 5000 ብር ያህል ቢከፍለውና በሚያዝያ ወር 2002 ዓ.ም. ውስጥ ሆን ተብሎ ሳይሆን በስሕተት የተሸሸገ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር እንደነበር ቢደረስበትና መድን ሰጪው ከዚህ የተነሳ ውሉን ለማቋረጥ ወስኖ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ቢያቋርጥ የውሉ መቋረጥ የሁለቱን የወደፊት ግንኙነት ከፍጻሜ ያደርሰዋል እንጂ ወደኋላ ተመልሶ <u>በጎዳር ወር</u> 2002 ዓ.ም. የተከፈለውን የ5000 ብር ካሣ አይነካም። በዚህ ምሣሌ ሥር የተነሳው የመሸሸግ ጉዳይ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር የሚወድቅ ቢሆን ኖሮ ግን ውሉ ራሱ ፍርስ ስለሆነና በሕግ በፊት እንዳልተደረገ ወይም እንደውጤት አልባ ውል ስለሚቆጠር መድን ሰጪው በጎዳር ወር 2002 ውስጥ የከፈለውን ብር 5000 መልሶ መጠየቅ እንደሚችል ይገመታል።

ሌላኛው በን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ሀ/ ሥር የተጠቀሰው ነጥብ መድን ሰጪው በውለታው መቀጠል ከፈለገ ማለትም ማቋረጡን ካልፈለገ ሆን ተብሎ ሳይሆን በስሕተት የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የተገለጸው የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ባይደበቅ ኖሮ ወይም በትክክል ቢገለጽ ኖሮ ያስከፍል ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል የነበረውን አረቦን አስልቶ ከዚሁ ላይ መድን ገቢው የከፈለውን ወይም ሊከፍል የተዋዋለውን ቀንሶ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት አስከፍሎ ምናልባትም ኪሣራውን ጨምሮ በማስከፈል ውሉን ሊቀጥል እንደሚችል ነው።

በን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ለ/ ሥር እንደተመለከተው ሆን ተብሎ ሳይሆን በስሕተት የተደበቀው ወይም በሐሰት የተገለፀው የአደጋ መመዘኛ ፍሬ ነገር መኖሩ የታወቀው መድን የተገባለት አደጋ ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ ውጤቱ ለመድን

ገቢው መጥፎ አይደለም። በሌላ ሌላ ምክንያት መድን ሰጪው ከሃላፊነት ይድን እንደሆነ እንጂ በዚህ ንዑስ ቁጥር ሥር በሚወድቅ መሸሸግ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መሰጠት መድን ሰጪው ከመካስ ሃላፊነት ነፃ እንደማይሆን ስለተደነገገ መደረግ ያለበት የተደበቀው ቢታወቅ ኖሮ ወይም በሐሰት የተገለጸው በትክክል ቢገለጽ ኖሮ መድን ሰጪው ለአደጋው ሽፋን ያስከፍል ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል በነበረውና ባስከፈለው ወይም ሊያስከፍል በተዋዋለው መካከል ያለውን ልዩነት መድን ሰጪው ለመድን ገቢው ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ይቀንሰዋል።

ከዚህ በላይ ስለመደበቅና ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት ሕግ የሚለውን ለማየት ተሞክራል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በኢትዮጵያ አንጋፋዉ፣ ዋናዉና ትልቁ መድን ሰጪ የሆነዉ ኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች አንፃር መሸሸግና ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት እንዴት ይታያል? የሚለውን ጥያቄ ባጭሩ እናያለን። የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች ከእንግሊዝ አገር መድን ሰጪዎች እንደተወሰዱ ሁሉ ሌሎች በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉት መድን ሰጪ ኩባንያዎች የሚጠቀሙባቸውን ፖሊሲዎች የወሰዱት ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነዉ። በመሆኑም በዚህ ጽሁፍ ዉስጥ የተካተቱት አንጋፋዉ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸውን ፖሊሲዎች የሚመለከቱ አስተያተቶች ሌሎች መድን ኩባንያዎች ለተመሳሳይ አደጋዎች ሰሚጠቀሙባቸዉ ፖሊሲዎች ያገለግላሉ።

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሚጠቀምበትና አሁን በሥራ ላይ ባለው የሠራተኞች የካሳ ፖሊሲ /workmen's compensation policy/ ላይ 'ሁኔታዎች' "conditions" በሚለው ክፍል ሥር በ10ኛው ቁጥር ላይ ማንኛውም የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ቢደበቅ ወይም በሐሰት ቢገለጽ በደፈናው ፖሊሲው ውድቅ እንደሚሆን ከመጸፉ በስተቀር በን.ሕ.ቁ. 668 ላይ እንደተመለከተው ሆን ተብሎ ሲደረግና በስሕተት ወይም ባለማወቅ ሲደረግ የተለያዩ ውጤቶች እንደሚያስከትል አልተገለፀም።

በቤቶችና በሌሎች ነገሮች በኃይል ሠብሮ የመግባት ፖሊሲ (Burglary & Housebreaking policy) ላይ አሁንም ሁኔታዎች (conditions) በሚለው ክፍል ሥር በ2ኛው ቁጥር ላይ የመድን ገቢው በማመልከቻ ላይ የሞላቸው መግለጫዎች እውነት መሆን መድን ሰጪው በፖሊሲው መሠረት በኃላፊነት ለመጠየቅ እንደቅድመ ሁኔታ ተደርጎ እንደሚወሰድና መድን ገቢው በማመልከቻው ውስጥ ካሠፈራቸው መግለጫዎች ሐሰተኛ የሆነ ካለ ወይም ሳይገለጽ የቀረ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር /ማቴሪያል ፋክት/ ከተገኘ ፖሊሲው ውድቅ ይሆናል ይላል። ይህም አባባል በንግድ ሕጉ በን.ሕ.ቁ. 668 ሥር ከሠፈረው የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ምናልባት በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር ከተመለከተው ጋር ሊመሳሰል ይቃጣው ይሆናል። ነገር ግን በቁ. 668/1/ ሥር የተመለከተው ጠንከር ያለ ውጤት እንዲመጣ መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን የደበቀው ወይም በሐሰት የገለፀው ሆን ብሎ መሆን እንዳለበት ስንመለከት በዚህ በያዝነው በቤቶችና በኃይል ሰብሮ የመግባት ፖሊሲ /Burglary and Housebreaking policy / ላይ ግን ሆን ተብሎ ይሆን በቸልተኝነት ይሁን

ወይም በስሕተት ሳይለይ በደፈናው ብቻ መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ሳይገልጽ መቅረቱ ወይም በሐሰት መግለጹ ፖሊሲውን ውድቅ እንደሚያደርገው መጻፉን እንረዳለን።

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለእሳትና ለመብረቅ አደጋ መድን በሚጠቀምበት ፖሊሲ /Fire and Lightning policy/ ውስጥም 'ሁኔታዎች' conditions በሚለው ክፍል በአንደኛው ቁጥር ላይ ያደጋ መመዘኛ መረጃዎችን ያለመግለጽ ወይም በሐሰት መግለጽ በደፈናው የመድን ሰጪውን በፖሊሲው መሠረት ለመካስ መጠየቅን እንደሚያስቀርለት ሲያመለክት በግል ተሽከርካሪ ለ3ኛ ወገን ኃላፊነት ፖሊሲ /Private Vehicle third party policy/ ላይም አሁንም 'ሁኔታዎች' conditions በሚለው ክፍል በመጀመሪያ ቁጥር ላይ የመግለጫዎች እውነትነት ለመድን ሰጪው በፖሊሲው መጠየቅ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ተመልክቷል። በንግድ ተሽከርካሪዎች ፖሊሲም ላይ ይኸው ሠፍሮ ይገኛል።

በፊደሊቲ ጋራንቲ /Fidelity Guarantee/ ፖሊሲ ላይ ደግሞ በመድን ገቢው የተሰጡት መግለጫዎች ውሉ የቆመበት ዋነኛ መሠረት basis of the contract ተብለው እንደሚወሰዱ ሲነበብ በአካል ጉዳት መድን ፖሊሲ ላይም ያልተገለፀ ወይም በሐሰት የተሠጠ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ካለ በደፈናው ፖሊሲው ውድቅ እንደሚሆን ተጽፎ ይገኛል።

አሁን በሥራ ላይ ካሉት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች መካከል ወደ ን.ሕ.ቁ. 668 ቀረብ ተደርገው የተቀረጹት፡- የሕይወት መድን ፖሊሲ፣ የሁሉም ዓይነት አደጋ ፖሊሲ /all risks policy/ እና የገንዘብ ፖሊሲ /Money policy/ የሚባሉት ብቻ ናቸው ቢባል ስሕተት አይመስለኝም። ይህንንም ያልኩበት ዋናው ምክንያት በነዚህ ሶስት ፖሊሲዎች ላይ በተመለከተው መሠረት ውሉ ውድቅ የሚሆነው መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ሆን ብሎ ካልገለፀ ወይም ሆን ብሎ ሐሰተኛ መግለጫዎችን ከሰጠ ብቻ ነው ስለሚል ነው።

ባጠቃላይ ሕጉና አብዛኞቹ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች ከመደበቅና በሐሰት ከመግለጽ አኳያ ብዙም ተጣጥመው አናገኛቸውም። አብዛኛዎቹ ፖሊሲዎች የመድን ገቢውን መብት የሚያጣበቡ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምናልባት ይህ ችግር የመጣው በኮንቲኔንታል የሕግ ሲስተም (Continental Legal System) ለተቀረፀ የመድን ሕግ የኮመንሎው (Common Law) ፖሊስዎችን ከመጠቀም ሳይሆን አይቀርም። የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች የእንግሊዝ መድን ሰጪዎች የሚጠቀሙባቸው ፖሊሲዎች ሳይሆኑ አልቀሩም።

በመጨረሻም በ የኮመንሎው ሲስተም (Common Law System) አገሮች ማለትም በሁለቱ የዚህ ሲስተም ተጠቃሽ አገሮች በዩናትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካና በእንግሊዝ አገር ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች ሆን ተብሎ ቢደበቁ ወይም በሐሰት ቢገለፁ ወይም በስሕተት ቢደበቁ ውጤቱ አንድ ነው። መድን ሰጪው ፖሊሲውን

ውድቅ ነው ሊል ይችላል። በአሜሪካ አገር ባንዳንድ አካባቢዎች የሚከተለዉ አስተሳሰብ ይንፀባረቃል፦

> The material representation must be fraudulently made in order to avoid the policy. The defendant must show not only that the representation was material and false in fact, but that it was willfully and knowingly made form a fraudulent or corrupt motive or with intent to deceive.[28]

/ፖሊሲውን ውድቅ ነው ለማለኘት ያደጋ መመዘኛው ሐሰተኛ መግለጫ በተንኮል የተደረገ መሆን አለበት። ይህም በመሆኑ ተከሳሹ ማረጋገጥ ያለበት የተሰጠው ፍሬነገር ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር መሆኑንና ይኸውም በሐሰት የተሰጠ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የተሰጠው ሐሰተኛ መግለጫ መሆኑ እየታወቀ ሆን ተብሎ በተንኮልና በማሳሳት ፍላጐት የተሰጠ መሆኑም ጭምር መሆን ይኖርበታል/ ትርጉም የፀሐፊው። ከላይ የተመለከተዉ አስተሳሰብ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሜሪካ አገር በሠፊው ሥራ ላይ ያለውና ሥር የሰደደው ሕግ የሚከተለዉ ነዉ፦

> ... That a false representation if it be a fact material to the risk avoids the policy irrespective of the good faith of the one who makes it. A false statement or declaration of fact material to the risk and upon which the policy is based, will avoid the policy, whether that misrepresentation be the result of intention or mistake not so made.[29]

/ያደጋ መመዘኛ የሆነ ሐሰተኛ መግለጫ፣ መግለጫ ሰጪው በቅን ልቡና ይሰጥ አይሰጥ ፖሊሲውን ውድቅ ያደርገዋል። እንደፖሊሲው መሠረት ተደርጐ በሚወሰድ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ላይ የተደረገ ሐሰተኛ መግለጫ ለመሰጠቱ መንስኤው ስሕተት ይሁን ወይም በቅን ልቡና የተደረገ ይሁን ወይም ሆነ ተብሎ መደረጉ እግምት ውስጥ ሳይገባ ፖሊሲውን ውድቅ ያደርገዋል/። /ትርጉም የፀሐፊው ነው/ የተሰኘው ነው።

በእንግሊዝ አገር እንኳንስ ሆን ተብሎ ታስቦ መድን ሰጪውን ለማሳሳት የተደረገ መሸሸግ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ ቀርቶ An innocent misrepresentation affords the party misled a ground for avoiding the policy, a rule which also applies in the case of non-disclosure.[30] *በቅን ልቡና የተሰጠ ሐሰተኛ መግለጫ በመግለጫው ምክንያት ለተሳሳተው ወገን ፖሊሲውን ውድቅ ማድረጊያ ምክንያት ይሰጠዋል። ይህ ደንብ በመሸሸግም ላይ ተፈጻሚ ነው።* ተብሎ ተወስዷል።

---

[28] Michigan Law Review , supra note 17, p.468

[29] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.28 የተመለከተዉ።

[30] Raoul Collinvaux, ግርጌ ማስታወሻ ቁ.7 ገጽ 99

አደጋ እየከበደ መሄዱን ስለመግለጽ

ይህ ንዑስ ርዕስ ከዚህ በታች ባለዉ ክፍል ዉስጥ ሊታይ የሚችል ሲሆን እዚህ እንዲመጣ የተደረገዉ ከመሸሸግ እና ሃሰተኛ መግለጫ ከመስጠት ጋር ስለሚያያዝ መሆኑን ለአንባቢያን መግለጽ እወዳለሁ።

አደጋ እየከበደ መሄዱን ወደማስታወቅ ግዴታ ስንመለስ በን.ሕ.ቁ.667 ላይ ውሉ ሲመሠረት ወይም ከውሉ ምሥረታ በፊት መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን መግለጽ እንዳለበት ግዴታ ሲጥል ውል ከተመሠረተ በኋላ ደግሞ አደጋው እየከበደ ስለመሄዱ የመግለጽ ግዴታን በን.ሕ.ቁ. 669 ሥር ተመልክቶ እናገኛለን።

የን.ሕ.ቁ. 669 ከርሱ በፊት ከተጻፉት ከቁጥር 667 እና 668 ተከታይ ሆኖ ከውለታው ምሥረታ በኋላም ቢሆን የፍጹም ቅን ልቡና አስፈላጊነት የጎላ መሆኑን የሚያሳውቅ ቁጥር ሆኖ እናገኘዋለን።

ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች በትክክልና ሳይደበቁ ተገልጸው መድን ሰጪው ኃላፊነት ስለሚወስድበት አደጋ በትክክልና በሚገባ ተረድቶ ተገቢውን አረቦን በማስከፈል ወይም ለማስከፈል በመዋዋል አንድ የካሳ መድን ፖሊሲ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረ በኋላ መድን የተገባለት ንብረት ውሉ ሲመሠረት ለተፈራው አደጋ ተጋልጦ ከነበረው የበለጠ ቢጋለጥ የተፈራውና መድን የተገባለት አደጋ እየከበደ መሄዱን እንገነዘባለን። ይህም ተፈርቶ መድን የተገባለት አደጋ የመድረሱን ዕድል probability እየጨመረው መሄዱን ይጠቁምና ውሉ ሲመሠረት ወይም ከመመሥረቱ ቀደም ብሎ መድን ሰጭው እግምት ውስጥ ያላስገባቸው አዳዲስ ክስተቶች መኖራቸውን ያሳያል። ሕጉም በዚህ ረገድ መድን ገቢው አዳዲስ የተከሠቱትን የመድን ሰጪውን የአደጋ አሰተያየት ሊለውጡበት የሚችሉትን ፍሬነገሮች ለመድን ሰጪው ማስታወቅ እንዳለበት ይደነግጋል።

በን.ሕ.ቁ.669 ሥር ሕጉ ማንኛውም ዓይነት መድን የተገባለት አደጋ እየከበደ መሄዱን የሚያሳዩ ሁኔታዎች እንዲገለጹ ግዴታ አልጣለም። ይልቁንም ሕጉ መድን ገቢው እንዲገልፀው የፈለገው ያደጋው እየከበደ መሄድ ደረጃውና መጠኑ መድን ሰጪው ላደጋው ሽፋን ለመስጠት ውል ሲያደርግ እንዲህ እየከበደ መሄዱን ቢያውቅ ኖሮ ያደጋውን ኃላፊነት ለመቀበል አይዋዋልም ነበር ወይም ቢዋዋልም እንኳን ካስከፈለው ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው አረቦን የበለጠ አስከፍሎ ይዋዋል ነበር ሊያሰኝ ነው።

በሌላ አነጋገር ከውሉ ምሥረታ በኋላ የተከሠተውን የአደጋ ክብደት ወደኋላ መልሶ ይህ በኋላ የተፈጠረውና የታወቀው ማክበጃ ሁኔታ ውሉ ሲመሠረት ቢታወቅ ኖሮ መድን ሰጪው ወይ ጨርሶ አልዋዋልም ይል ነበር ወይም ለመዋዋል ፈቃደኛ እንኳን ቢሆን በምንም ዓይነት አስከፍሎ የተዋዋለውን ወይም

ሊያስከፍል ለተዋዋለው አነስተኛ አረቦን አይዋዋልም ነበር ሊያስኝ ነው ማለት ነው።

በን.ሕ.ቁ. 669 ሥር እንደተደነገገዉ በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጵያ የባህር ሕግ ቁ. 301 "ይደርሳል ተብሎ የሚያሰጋዉ አደጋ ስለ መክበዱ" በሚል ርዕስ የሚከተለዉ ተደንግጓል፦

(1) የኢንሹራንስ ዉል በሚፀናበት ጊዜ ይደርሳል ተብሎ የሚያሰጋዉ አደጋ የከበደ እንደሆነ ይህንኑ ሁኔታ እንዳወቀ ለኢንሹራንስ አድራጊዉ ካላስታወቀ የኢንሹራንስ ዉሉ ፈራሽ ይሆናል።

(2) ይህ የአደጋዉ መክበድ ለኢንሹራንስ አድራጊ የተነገረዉ እንደሆነና ይህም የአደጋ መክበድ የደረሰዉ ኢንሹራንስ በገባዉ ሰዉ ምክንያት የሆነ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ገንዘብ ለርሱ ቀሪ ሆኖ ወዲያዉኑ ዉሉን መሻር ወይም የኢንሹራንሱ ገንዘብ እንዲጨመር ለማስገደድ ይችላል። አደጋዉ የከበደዉ በሌላ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ግን ገንዘቡን በመጨመር ኢንሹራንሱ ይቀጥላል።[31]

ባንዳሩ በእንግሊዝ አገር ያደጋ እየከበደ መሄድ ለተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተተወ ጉዳይ ነዉ። ተዋዋይ ወገኖች በዉለታቸዉ ዉስጥ መድን ገቢዉ ያደጋዉን እየከበደ መሄድ ለመድን ሰጪዉ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት ካላስገቡ በስተቀር መድን ሰጪዉ ኃላፊነት የወሰደበት አደጋ እየከበደም እንኳ ቢሄድ መድን ገቢዉ ሁኔታዉን ማሳወቅ አይጠበቅበትም።

በእንግሊዝ አገር ባጠቃላይ አነጋገር ያደጋ መመዘኛ ፍሬ ነገሮችን የማሳወቅ ግዴታ ከቅድመ ዉል ምስረታ ጋር እና ከዉል እድሳት ጋር የተያያዘ ነዉ። ይህንንም ጆን በርድስ እና ኖርማ ሄርድ እንደሚከተለዉ ያስቀምጡታል፦

> The duty to disclose material facts is cast upon the proposer or insured before the contract or a renewal is concluded. At common law, there is no general duty to disclose material facts that occur when they occur during the period of insurance.[32]

ሆኖም በእንግሊዝ አገር ግዴታዉ በህግ በመድን ገቢዎች ላይ የተጣለ አይሁን እንጂ በዉሎች ዉስጥ ግዴታዉን አስገብቶ መዋዋል ግን አልተከለከለም። በአንዳንድ የመድን ዉሎች በተለይም ለእሳት አደጋ ለሚገቡ የመድኖች ዉሎች የተፈቀደ ነዉ። ጆን በርድስ እና ኖርማ ሄርድ እንደሚከተለዉ ያብራራሉ፦

> Certain contracts of insurance, though most notably those of fire insurance do, in practice, impose a duty on the insured to disclose facts occurring during the insurance which materially increase the risk. The term that

---

[31] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የባሕር ሕግ ፣ነጋሪት ጋዜጣ ቁ. ፩፣ በ1952 ዓ.ም. በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ

[32] John Birds and Norma Hird, Modern Insurance Law , (5th ed.), Sweet & Maxwell, London, 2001, p.122.

imposes such a duty is usually, though not necessarily, a promissory warranty, since it provides that upon a failure to disclose, the insurer can avoid the policy.[33]

ጆን በርድስ እና ኖርማ ሄርድ እንደጻፉት በዉል የሚጣለዉ ያደጋን አየከበደ መሄድ የማሳወቅ ግዴታ መድን ገቢዉን የሚያስገድደዉ በቋሚነት ወይም በዘላቂነት የመድን ሰጪዉን ያደጋ ሃላፊነት የሚያከብዱ ፍሬ ነገሮችን በሚመለከት እንጂ ለጊዜዉ ብቻ ወይም አንዳንዴ የሚያከብዱትን አይደለም። መድን ገቢዉ ለጊዜዉ ብቻ ወይም አንዳንዴ የሚያከብዱትን እንዲገልጽ አይገደድም።[34]

ከመድን ውል ምሥረታ በኋላ አደጋው እየከበደ መሄዱን የማስታወቅ ግዴታ ብቻ ሳይሆን በን.ሕ.ቁ. 669/1/ ላይ የተጣለው የመክበዱ መንስዔ ዓይነትና መድን ገቢው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለበትም ተመልክቷል። በዚሁ መሠረት ለአደጋው እየከበ መሄድ ምክንያቱ ወይም መንስኤው የመድን ገቢው የራሱ ድርጊት ከሆነ ይህ አደጋ አክባጅ ድርጊት ወይም ሁኔታ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ መረጃው ለመድን ሰጪው መነገር አለበት። ለአደጋው እየከበደ መሄድ ምክንያቱ ወይም መንስኤው የመድን ገቢው ድርጊት ሳይሆን ሌላ ከሆነ መድን ገቢው የአደጋ አክባጅ ሁኔታ መከሰቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ አሥራ አምስት ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለመድን ሰጪው ማስታወቅ እንዳለበት ሕጉ ግዴታ ሲጥል ይህንን የ15 ቀናት የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ አርዝሞ መዋዋል በግልጽ ባይከለክልም ቀንሶ መዋዋልን ግን የን.ሕ.ቁ.669/1/ ይከለክላል።

በን.ሕ.ቁ. 669/1/ የተመለከተዉን የማስታወቅ ግዴታና የጊዜ ገደብ ሁኔታን በምሣሌ ለማየት ብንሞክር፣ ለምሣሌ አንድ ሰው ለውሃ ማመላለሻ የሚጠቀምበት ቡቴ መኪና ኖሮት መኪናውን ለእሳት አደጋ መድን አስገብቶ ሳለ የመኪናውን አገልግሎት ከውሃ ማመላለሻነት ወደ ነዳጅ ማመላለሻነት ቢቀይረው ጥሩ የአደጋ መክበድ ሁኔታ ስለሚሆንና መድን ሰጪው ውሉ ሲመሠረት ይህን ቢያውቅ ኖሮ አልዋዋልም እንኳን ባይል አስከፍሎ ከተዋዋለው ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው አረቦን የበለጠ ያስከፍል ነበር ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል ነበር ስለሚያሰኝ መድን ገቢው የውሀ ማመላለሻ ቡቴ መኪናውን ወደ ነዳጅ ማመላለሻነት ከቀየረበት ቀን አንስቶ በ15 ቀን ውስጥ ሁኔታውን ለመድን ሰጪው መግለጽ እንዳለበት እንረዳለን። በሌላ በኩል ግን ይኸው መድን የተገባለት መኪና በውሃ አመላላሽነት ወደ ጦር ግምባር ተልኮ ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ መድን ገቢው ለአደጋው እየከበደ መሄድ መንስዔ ወይም ምክንያት ባለመሆኑ /ፊትኑ የመኪናው ወደ ጦር ግምባር መላክ የአደጋ መክበድ ሆኖ የሚቆጠር ከሆነና ይህንኑ አስታውቆ ከሆነ/ መድን ገቢው ስለአደጋው መክበድ ማስታወቅ

---

[33] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.32 የተመለከተዉ ከገጽ 122-123።

[34] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.32 የተመለከተዉ ገጽ 123።

የሚፈለግበት በውሃ አመላላሽነት ወደ ጦር ግምባር የተላከው ቦቴ መኪናው ወደ ነደጅ ማመላለሻነት መቀየሩን ካወቀበት ቀን ጀምሮ አሥራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

መድን የተገባለት አደጋ እየከበደ መሄዱን ማስታወቅና አለማስታወቅ ምን ምን ውጤት እንደሚያስከትል በን.ሕ.ቁ. 669/2/ እና /3/ ሥር ተጽፎአል። ሰለሆነም ውጤቶቹ ሶስት ናቸው እነርሱም 1ኛ/ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር በተባፊው ሁኔታ ውሉ ፍርስ ሊሆን እንደሚችል፣ 2ኛ/ በመድን ሰጪው ፍላጐትና ምርጫ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል፣እና 3ኛ/ እየቀጠለ የሄደውን አደጋ ገምግሞ መድን ሰጪው ተገቢውን ተጨማሪ አረቦን በማስከፈል ውሉን እንዲቀጥል ማድረግ እንደሚችል ነው።[35]

የአደጋን እየከበደ መሄድ መግለጽ የን.ሕ.ቁ 669/1/ የመድን ገቢው ግዴታ አድርጐ ያስቀምጠው እንጂ በፖሊሲዎች ላይ አልተመለከተም። ቀደም ሲል በጨረፍታ እንደጠቀስኩት ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች በቀጥታ የተወሰዱት ከእንግሊዝ አገር መድን ሰጪዎች ስለሆነ ሳይሆን እንደማይቀር ሲገመት በእንግሊዝ አገር እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ማለትም እ.ኤ.አ. እስከ 1985[36] ዓ.ም. ድረስ የፍጹም ቅን ልቡናን ግዴታ በውሉ ምሥረታ ጊዜ ብቻ መወጣት እንደሚያስፈልግና ከውሉ ምሥረታ በኋላ ስለአደጋው እየከበደ መሄድ መግለጽ አስፈላጊ እንዳልነበረ መገንዘቡ መልካም ነው።

በን.ሕ.ቁ. 669/4/ ሥር እንደተመለከተው የአደጋን እየከበደ መሄድ የማስታወቅ ግዴታና ውጤቶች በሕይወት መድን ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ተደንግጐአል። የሕይወት መድንን በሚመለከቱ የንግድ ሕጉ ቁጥሮች አካባቢም የተባለ ነገር የለም። በሌላ በኩል በሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ ጠቅላላ ግዴታዎች በሚለው ክፍል ሥር መድን የገባው ድርጅቱ በጽሑፍ ሳይፈቅድለት በወታደራዊ፣ በባሕር ኃይል ... ወይም ማናቸውንም ይበልጥ አደጋ የሚያስከትል ሥራ ቢይዝ ወይም ... ሥራ ላይ ቢሠማራና ከላይ በተጠቀሱት በማናቸውም ምክንያቶች ቢሞት በዚህ ውል መሠረት የድርጅቱ ግዴታ ይኸው ይበልጥ አደገኛ የሆነው ሥራ ታውቆ ቢሆን ኖሮ የተከፈለው አረቦን ሊገዛ የሚችለውን የዋስትና ገንዘብ መክፈል ይሆናል። ይኸውም ይበልጥ አደገኛ የሆነው ሥራ ዋስትና ሊሰጠው የማይችል ከሆነ የድርጅቱ ግዴታ ለውሉ የተከፈውን ጠቅላላ አረቦን /ተጨማሪ አረቦን ሳይጨምር/ መመለስ ይሆናል ይላል።

---

[35] በን.ሕ.ቁ. 669/1/ሥር የተጣለው ግዴታ የሚያስከትለውን ዝርዝር ውጤት አንባቢው ከዚህ በላይ ከገጽ 7 እስከ 26 ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ስላለመግለጽ ወይም በሐሰት ስለመግለጽና የሚያስከትለውን ውጤት በሚመለከት የተፃፈውን እንዲመለከቱ ፀሐፊው ይጠቁማል።

[36] The Litsion Pride (1985) 1 LLoyd's Rep. 437

ውሉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ /መድን የተገባለት አደጋ ከመድረሱ በፊት ወይም በውሉ የተመለከተው ጊዜ ከመሙላት በፊት/ የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ

የአረቦን አከፋፈል[37]

በዚሁ ጽሁፍ ዉስጥ ቀደም ሲል ለማመልከት እንደተሞከረው ምንም እንኳን የኢንሹራንስ /የመድን/ መግቢያ ገንዘብ /አረቦን/ አከፋፈል በተዋዋይ ወገኖች ውል የሚወሰን ቢሆንም አንድ የመድን ውል ፖሊሲ ተፈርሞም ፖሊሲው ዉጤት መስጠት የሚጀምረው ግን የመጀመሪያው መደብ ኘሪሚዬም ሲከፈል ነው ብሎ መዋዋል እንደሚቻል በን.ሕ.ቁ. 659/2/ ተደንግጓል። ይህ የን.ሕ.ቁ. 659/2/ ድንጋጌ ለተወሰነ ጊዜ ፖሊሲውን የሚያስኬደው አረቦን ተከፍሎ ከዚያ ያ የተወሰነው ጊዜ ካለቀ በኋላ ማደሻ ኘሪሚዬም ስለማስከፈል ይሁን ወይም ለተወሰነ ጊዜ የተገባ ፖሊሲ ኖሮ ለዚያ ለተወሰነ ጊዜ ከሚከፈለው ኘሪሚዬም ላይ የሆነ ያህል እንደ መጀመሪያው መደብ የሚቆጠር ካልከፈሉ ፖሊሲው ውጤት መስጠት እንደማይጀምር ይናገር ተለይቶ አልታወቀም።

ስለ አረቦን አከፋፈል መድን ድርጅት በሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች ላይ ምን እንደተባለ ከዚህ በታች ባጭሩ ለማየት እንሞክራለን።

በሠራተኞች የካሣ መድን ፖሊሲ /workmen's compensation policy/ ላይ 'ሁኔታዎች' conditions በሚለው ክፍል በ6ኛው ቁጥር ላይ "የመጀመሪያው መደብ" አረቦንና "ማሳደሻ አረቦን" የሚሉ ሐረጎች እናገኛለን። "የመጀመሪያው መደብ" ማለት ውሉ ለአንድ ዓመት ተገብቶ ከሆነ ለዚያ ለአንድ ዓመት የሚውል ሙሉ አረቦን የሚል ስሜት ያለው ሲመስል አንድ ዓመት ሲያልቅ የሚከፈለው አረቦን ደግሞ "ማሳደሻ" አረቦን ይሆናል።

በሁሉም አደጋ መድን ፖሊሲ /All risks Policy/ ላይም እንደተመለከተው "የመጀመሪያ መደብ" አረቦን "first premium" የተሰኘው አባባል ውሉ ፀንቶ ለሚቆይበት ጊዜ የሚከፈለውን አረቦን እንደሚመለከት ስንረዳ ከሕይወት መድን አኳያ ስንመለከት ግን ለአንድ ዓመት የሚከፈለው አረቦን ተከፋፍሎ በ Installment ሊከፈል ስለሚችል "first premium" የመጀመሪያው መደብ አረቦን ማለትም ፖሊሲው ለአንድ ዓመት ተገብቶ ከሆነ ለዚያ ዓመት የሚከፈለው ሙሉ አረቦን ላይሆን ይችላል። "የመጀመሪያው አረቦን" በዚህ ረገድ የመጀመሪያው Installment ተደርጐ ሊወሰድ እንደሚችልና በን.ሕ.ቁ. 659/2/ መሠረትም ምንም እንኳን ፖሊሲው ቢፈረምም ይኸው የመጀመሪያው Installment ኘሪሚየም ካልተከፈለ

---

[37] ይህ ፀሃፊ በኢትዮጵያ ጠበቆች የሕግ መጽሔት በመጋቢ 1ቁ.1 ላይ ያሳተመዉን ይመልከቱ፣ እንደዚሁም በጥጋቡ አንበርበር እና በኢትዮጵያ መድን ድርጅት መካከል ስለ አረቦን መክፈልና ስለመድን ዉል መታደስ በነበረዉ ክርክር ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በፍ/ቤቱ የፍርዶች መጽሃፍ ቅጽ ፩ ከገጽ 121-126 ይመልከቱ

ፖሊሲው ዉጤት መስጠት አይጀምርም የሚል ስምምነት ማድረግ እንደሚቻል እንገነዘባለን።

መድን ድርጅት በሚጠቀምባቸው ሌሎች ፖሊሲዎች ላይ ሠፍሮ የሚገኘው መድን ሰጪው ለመስጠት እየተዋዋለ ስላለው የመድን ሽፋን መድን ገቢው አረቦን ለመክፈል መስማማቱን የሚገልጽ ሲሆን ውሉ ሲመሠረት መድን ገቢው አረቦኑን ውሉ ፀንቶ ለሚቆየበት ጊዜ ባንዴ ይክፈል ወይም ከፋፍሎ ይክፈል ባያመለክትም ባንዴ ከፍሎ እንደሚዋዋል ይገመታል። ቢሆንም ግን ተዋዋይ ወገኖች የአረቦኑን አከፋፈል በሚመለከት እንደፈለጉ ሊዋዋሉ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም።

ዋነኛው በዚህ በያዝነው "የአረቦን አከፋፈል" በተሰኘው ንዑስ ርዕስ ሥር ለማንሳት የፈለግሁት በን.ሕ.ቁ.666 እና 709 ላይ የተመለከተዉ አረቦን በጊዜ ካልተከፈለ ምን ውጤት እንደሚያስከትል የተደነገጉትንና በፖሊሲዎች ላይ ስለአረቦን ክፍያ የሠፈሩትን በሚመለከት አንዳንድ ሐሳቦችን ነው።

ምንም አንኳን በን.ሕ.ቁ.666/1/ መሠረት መድን ገቢው ለኢንሹራንስ መግቢያ የሚከፈለውን ገንዘብ በውሉ ላይ በተወሰነው ቀን መክፈል ግዴታው መሆኑ ቢደነገግም መድን ገቢው አረቦኑን በውሉ በተወሰነው ጊዜ ባለመክፈሉ ብቻ ውሉን ማፍረስ እንደማይቻል በን.ሕ.ቁ. 666/2/ ላይ ተመልክቷል። የንዑስ ቁጥር /2/ ክልከላ ተፈጻሚነቱ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ባይኖርም ሲሆን የዚህን ንዑስ ቁጥር ድንጋጌ ዋና መልዕክት አረቦን በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ካልተከፈለ ውሉ ፈራሽ ነው በሚል ሰበብ ስምምነቱን ወደጉን ማድረግ እንደማይቻል ነው። የንግድ ሕጉ ሲረቀቅ በዚህ በንግድ በን.ሕ.ቁ. 666 በስተጀርባ የነበረዉን አስተሳሰብ ፒተር ዊንሺፕ እንደሚከተለዉ ይገልጹታል፦

> As for the payment of the premium, in order to spare the insured from the sudden unforeseen rupture of the contract, I have included a provision, as has been done in the French law, requiring a mandatory waiting period of one month during which the insurance is only suspended. The provision is a matter of public policy and cannot be varied by the parties.[38]

የአረቦን አከፋፈልን በተመለከተ መድን ገቢዉ ለድንገተኛ የዉል መቋረጥ እንዳይጋለጥ ለመከላከል በፈረንሳይ ሕግ ዉስጥ እንዳለዉ ዓይነት ለአንድ ወር ጊዜ ዉሉ ታግዶ የሚቆይበትን በግዴታ የመጠበቂያ ጊዜን የሚመለከት ድንጋጌ አስገብቻለሁ(ትርጉሙ የፀሃፊዉ)

አረቦኑ በፖሊሲው ላይ በተመለከተው ጊዜ ካልተከፈለ ውሉ ለተገባበት ጊዜ ሙሉውን ፀንቶ ይቆያል ማለት አይደለም። የን.ሕ.ቁ.666/2/ አባባል ግልጽ እንደሚያደርገው መድን ሰጪው አረቦኑ በፖሊሲው ላይ በተመለከተው የመክፈያ

---

[38] Peter Winship, (editor and translator) Background Documents of the Ethiopian Commercial Code of 1960, Faculty of Law , Haile Selassie I University, Addis Ababa, 1974 p. 82

ጊዜ ባለመከፈሉ ውሉ በዚሁ ምክንያት ብቻ ወዲያውኑ /automatically/ ፈራሽ ነው ሊል አይችልም። በን.ሕ.ቁ. 666/3/ እና /4/ እንደዚሁ በራሱ በንዑስ ቁጥር /2/ መሠረት መድን ሰጪው ያልተከፈለው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ እንዳለበትና እንዲከፈለው በጠየቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከተከፈለው ውለታው ይቀጥላል ካልተከፈለው ግን በን.ሕ.ቁ. 666/2/ ሥር የተጻፈው"... ባለመከፈሉ ብቻ ውሉን ለማፍረስ አይቻልም" የሚለው አባባል የተወዘፈው አረቦን ባይከፈልም ውሉ ተዋዋይ ወገኖች ፀንቶ እንዲቆይ ለተዋዋሉት ጊዜ ይፀናል ማለት አለመሆኑን ማጤን ያስፈልጋል።

በን.ሕ.ቁ.666/3/ ላይ በቁጥር የአንድ ወር ጊዜ ተለጠ እንጂ ሃሳቡ በፍትሐብሔሩ ሕግ የጠቅላላ ውል ሕግ ክፍል ውስጥ በቁጥር 1772 ላይ የተመለከተውን ማስጠንቀቅን ወይም ደግሞ በቁጥር 1770 ሥር የተጻፈውን የችሮታ ጊዜን[39] የሚመለከት ነው ለማለት ይቻላል። ልዩነቱ ማስጠንቀቂያ ተባለ የችሮታ ጊዜ በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር የመለከተውን የሰጠው ሕግ ነው እንጂ ተዋዋዩ መድን ሰጪ አለመሆኑ ነው።

ወደ ን.ሕ.ቁ. 666/3/ አባባል ስንመለስ መድን ሰጪው አረቦን እንዲከፈለው ከጠየቀበት ቀን አንሥቶ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ካልተከፈለው ውሉ አንደሚታገድ እናነባለን። የውሉ መታገድ ምን እንደሆነ፣ ምን ውጤት እንደሚያስከትል በሕጉ ላይ የተሰጠ ምንም ዐይነት ማብራሪያ ባይኖርም በዚህ ንዑስ ቁጥር ሥር "ውሉ ይታገዳል" የሚለው አባባል ምን እንደሆነና ምንስ ውጤት እንደሚያስከትል ባጭሩም ቢሆን ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል።

ስለውሉ መታገድና ስለውጤቱ ከማውሳታችን በፊት መድን ሰጪው የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ካደረገበት[40] ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ጊዜ ድረስ ውሉ እንደፀና እንደሚቆይ መገንዘቡ መልካም ነዉ። የአረቦን ክፍያ ጥያቄ በመድን ሰጪው ከተደረገበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ መድን ሰጪው የመካስ ግዴታ እንደሚወድቅበትም መረዳቱ አስፈላጊ ነው። የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ መድን ሰጪው መክፈል ይገባ የነበረውን አረቦን ከካሣው ላይ ቀንሶ ለመድን ገቢው መስጠት እንደሚችል ይገመታል። ምናልባትም ኪሣራም ሊጠይቅ ይችል ይሆናል።

---

[39] የኢትዬጵያ መድን ድርጅት "የፋታ ጊዜ" ይለዋል።

[40] በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ላይ ያለው የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የመድን ሰጪው የውዝፍ አረቦን ክፍያ ጥያቄ ከተላከበት ቀን /ጊዜ/ ጀምሮ ነው? ወይንስ ጥያቄው ለመድን ገቢው ከደረሰበት ጊዜ /ቀን/ ጀምሮ ነው? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። ከውል ድርድር ማለትም hoffer እና acceptance አንፃር እንደሚታወቀው Dispatch theory እና Reception theory የሚባሉ ነድፈ ሐሳቦች አሉ። የን.ሕ.ቁ. 666/3/ አባባልም ከነኚህ ባንዱ ሥር መሸፈን አለበት ሊባል ይቻላል።

በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር አርባ ላይ እንደተመለከተው ያንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የመድን ሰጪው የዉዝፍ አረቦን ጥያቄ ከተላከበት ቀን አንስቶ ይሁን ወይም ጥያቄው ለመድን ገቢው ከደረሰበት ቀን አንስቶ የሚለው አከራካሪ ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ መድን ሰጪው ጥያቄ ካቀረበ ከአንድ ወር በኋላ ውሉ እንደሚታገድ በን.ሕ.ቁ. 666(3) ተደንግጉአል። "ይታገዳል" የሚለው ቃል ውሉ "ይፈርሳል" እንዳልሆነ በን.ሕ.ቁ. 666 ንዑስ ቁጥር (4) ሥር ከተጻፈው መረዳት ይቻላል። "ይታገዳል" ማለት "ይፈርሳል" ካልሆነ ሊኖረው የሚችለው ትርጉም ለጊዜው ተፈጻሚነቱ ይቆማል ማለት ነው። በተለይም የእንግሊዝኛውን ቅጂ ስናይ "suspended" ስለሚልና ይህ ማለት ደግሞ "ለጊዜው የመቆም"፣ "ለጊዜው የመታገድን" "ለጊዜው የመወገድን" ሰሜት ስለሚሰጥ የን.ሕ.ቁ. 666/3/ ትርጉም በመድን ሰጪውና በመድን ገቢው መካከል የተደረገው ውለታ ሳይፈርስ ወይም ሳይቋረጥ ለጊዜው ውሉ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነቱ ወይም ውጤታማነቱ ይቆማል ወይም ይቆያል ማለት ነው። ባጭሩ በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር ሕግ አውጪው ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት መድን ሰጪው አረቦኑ እንዲከፈለው ከጠየቀበት ቀን አንስቶ ሳይከፈለው አንድ ወር ካለፈ ከዚያ በኋላ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ ማለትም የእገዳው ጊዜ ከተጀመረ በኋላ ለሚደርሰው አደጋ መድን ሰጪው ሊክስ እንደማይገደድ ነው።

ከላይ እንደተመለከተው በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር የተጻፈው የእገዳ ጊዜ ውሉን ለጊዜው ተፈጻሚነቱን ያቆመዋል እንጂ አያቋርጠውም ወይም አያፈርሰውም። በመሆኑም ከእገዳው በኋላም ቢሆን መድን ገቢው በመድን ሰጪው ጥያቄ ይሁን በራሱ አነሣሽነት አረቦኑን ቢከፍል ከከፈለበት ቀን አንስቶ ውሉ ተፈጻሚነቱን ሊቀጥል እንደሚችል በዚሁ የን.ሕ.ቁ. 666 ንዑስ ቁጥር /5/ ሥር ተጽፎ እናነባለን።

መድን ሰጪው የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ከጠየቀበት ቀን አንስቶ የአንድ ወር ጊዜ ሲያልፍ ማለትም የእገዳው ተፈጻሚነት ከጀመረ በኋላ በን.ሕ.ቁ. 666 /4/ ሥር ሁለት አማራጮች ተሰጥተውታል። 1ኛ/ከላይ እንደተባለው በድጋሚ የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።[41] 2ኛ/ አንደኛውን አማራጭ ካልፈለገ ደግሞ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ ይችላል።[42]

---

[41] ይህ መቼም ተግባራዊ መሆኑ አጠራጣሪ ይመስላል፣ ነገር ግን መድን ሰጪው የረዥም ጊዜ ደምበኝነትንና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በድጋሚ ጥያቄ ለማቅረብ ይፈልግ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ የን.ሕ.ቁ.. 666/4/ የእንግሊዝኛ ቅጂ "claim" ስለሚል በፍርድ ቤት ወይም በግልግል ዳኝነት መድረክ ላይ እንዲከፈለው ክስ ያቀርባል ማለት ነው ሊባል ይችላል። በዚህ አጋጣሚ ከሕይወት መድን አንፃር መድን ሰጪው አረቦን ስላልተከፈለው ክስ ማቅረብ እንደማይችል ተጽፎ ስለምናይ የን.ሕ.ቁ.. 666/4/ ን ክስ ወደማቅረብ ልናጠቃልለው የምንችል ይመስላል።

[42] ይህ ሁሉ ሆኖ ሕጉ መድን ሰጪው ውሉን እራሱ እንዲያፈርስ ወይም ፈርሷል ብሎ እንዲል መብት የከለከለው ይመስላል። ተዋዋዮች በልዩነት ካልተስማሙ ወይም ሕግ ካልፈቀደ ውል እንዲፈርስ መጠየቅ በፍርድ ቤት በኩል እንደሚሆን በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1784 ተመልክቷል።

መድን ሰጪው በመጀመሪያው አማራጭ በመጠቀም የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ ከተከፈለው ውሉ እገዳው ተነስቶለት ውጤት መስጠት እንደሚጀምር ከን.ሕ.ቁ. 666 /5/ አባባል ስንገነዘብ፣ በሁለተኛው አማራጭ ሊጠቀም የፈለገ መድን ሰጪ ግን ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት[43] አማካኝነት ውሉን ሲያስፈርስ የውሉ መፍረስ የሚያስከትለውን ውጤት የንግድ ሕጉ አይናገርም። ምናልባት ያው በፍ.ብ.ሕ.ቁ 1815 መሠረት በተቻለ መጠን ተዋዋይ ወገኖች ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ ይመለሳሉ ለማለት ይቻል ይሆናል፣ ሆኖም በን.ሕ.ቁ. 666/4/ መሠረት አንድ የመድን ውል ሲፈርስ ሁለቱንም ተዋዋይ ወገኖች በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1815 መሠረት ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት መመለስ አይቻልም። ቀደም ሲል እንደተገለፀው መድን ሰጪው ለውሉ ግዴታ ተጠያቂ የሚሆነው የተፈራው አደጋ ሲደርስ ወይም ጊዜ ሲሚላ ወዘተ ስለሚሆን ከርሱ ወደ መድን ገቢው የሚሄድ ነገር የለም። የን.ሕ.ቁ. 666 ተፈጻሚነት ራሱ የሚነሣው መድን ገቢው በገባበት ግዴታ መሠረት አረቦን ለመክፈል ሲዘገይ ስለሆነ መድን ገቢው ከሰጪው በተመሳሳኝነት የሚጠይቀው ነገር አይኖርም።

ይልቅ አክራካሪ ሊሆን የሚችለው አረቦኑ መከፈል ይገባው ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ውሉታው በሕግ ማለትም በን.ሕ.ቁ. 666/3/ መሠረት እስከታገደበት ጊዜ ድረስ መድን ሰጪው ላደጋው ኃላፊነት ሰለነበረበትና He was on risk ለዚያ ጊዜ ደግሞ ሽፋን እንደሰጠ ስለሚቆጠር ለዚያ ጊዜ አረቦኑ ተሠልቶ መድን ገቢው እንዲከፍል ሊገደድ የሚችል ይመስላል። ይህን ገንዘብ መድን ሰጪው ባልተከፈለ አረቦንነቱ እንኳን ባያገኘው በኪሣራ መልክ ሊሰጠው የሚገባ ይመስላል። በነገራችን ላይ በን.ሕ.ቁ. 666 ሥር በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቅጂዎች በተጻፉት ድንጋጌዎች መካከል ልዩነት አለ። በተለይም በእንግሊዝኛዉ ቅጂ በን.ቁ. (2) እና (4) ላይ "terminate" እና "termination" በአማርኛዉ ቅጂ ደግሞ "ለማፍረስ" እና "እንዲፈርስ" በተሰኙት ቃላት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ። በእንግሊዝኛዉ ቅጂ ላይ የተጻፉቱ ቃላት በአማርኛ በትክክል ቢተረጎሙ ኖሮ "ማቋረጥ" "መቋረጥ" የሚል ትርጉም ሲኖራቸዉ በአማርኛዉ ቅጂ ላይ የተጻፉቱ ግን "ማፍረስ" "መፍረስ" የሚሉ ናቸዉ። በሌላ በኩል በ "መፍረስ" እና በ "መቋረጥ" መካከል ትልቅ የዉጤት ልዩነት አለ። በዉል ህግ ቋንቋ "መቋረጥ" ወይም "ማቋረጥ" የወደፊት ዉጤት ብቻ ሲኖረዉ ማለትም ዉሉ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ የተፈፀሙትን ግዴታዎች የማይነካ የተዋዋዮቹን የወደፊት ግዴታዎችን ብቻ የሚመለከት ሲሆን የዉል "መፍረስ" ግን ወደ ኋላ ሄዶ ዉሉን ከምስረታዉ ጀምሮ የሚነካዉ፣ በዉሉ መሠረት የተፈፀሙትን ግዴታዎች እንዳልተፈፀሙ በማስቆጠር ወደ ኋላ የሚመልሳቸዉ እንደዚሁም ደግሞ ከዉሉ መፍረስ የተነሳ ወደፊት ሊፈፀሙ ይችሉ የነበሩትን ግዴታዎችንም ጭምር የሚመለከት ነዉ። በ "መቋረጥ" እና በ "መፍረስ" መካከል ባሉት እነዚህ ልዩነቶች መነጽር በን.ሕ.ቁ. 666 የተቀመጠዉን

[43] የን.ሕ.ቁ. 666/4/ "ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ይችላል" ስለሚል መድን ሰጪው የግድ በፍ/ቤት በኩል መሄድ ይኖርበታል ማለት ሲቻል በሌላ በኩል ግን ውሉን ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ ሲያፈርስ /ፍርድ ቤት ሳይሄድ/ እንደሚቻል በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1774 1786 እና 1787 ተመልክቶአልና ከነኝህ ቁጥሮች ባንደኛው መጠቀም ከቻለ መድን ሰጪው በገዛ ራሱ ውሉ ፈርሷል ሊል እንደሚችል ይገመታል።

ስንመለከት መድን ሰጪው አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ካልተከፈለዉ ዉሉን የማቋረጥ መብት ነዉ ያለዉ ወይንስ የማፍረስ? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ የማይቀር ነዉ። አስገዳጅ በሆነዉ የአማርኛዉ ቅጂ መሠረት ከተሄደ መድን ሰጪው ዉሉን ከነዉጤቱ ማስፈረስ ሲችል በእንግሊዝኛዉ ቅጂ መሠረት ከተሄደ ደግሞ መድን ሰጪው ዉሉን በራሱ ሥልጣን በማቋረጥ በወደፊት ግዴታዎች ላይ ብቻ ዉጤት እንዲኖረዉ ማድረግ ይችላል።

ስለአረቦን ክፍያ የተጻፈው የን.ሕ.ቁ. 666 በሕይወት መድን ላይ ተፈጻሚ ያለመሆኑ በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር /6/ ሥር ተደንግጓል። ስለሕይወት መድን የተደነገጉትን የንግድ ሕግ ቁጥሮች ስንቃኝ ስላልተከፈለ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ በሚል ርዕስ ቁጥር 709 ስለዚሁ ጉዳይ የሚደነግግ መሆኑን እንረዳለን።

በን.ሕ.ቁ. 666 እና 709 መካከል ጉልቶ የሚታየው ልዩነት በቁጥር 666 ላይ የተጻፈው እንደተጠበቀ ሆኖ ውል የማፍረስና የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈል ጥያቄ ወይም ክስ የማቅረቡ መብት ሰፋ ተደርጐ ሰመድን ሰጪው ሲሰጥ በቁጥር 709 ላይ ግን 1ኛ/ ውዝፍ አረቦን እንዲከፈል ክስ ማቅረብ የተከለከለ መሆኑን፣ እና 2ኛ/ የአረቦኑ መወዘፍ በቁጥር 709/2/ ሥር በተመለከተው ሁኔታ ካልተሸፈነ ውሉን ማፍረስ እንደማይቻል እንገነዘባለን።

በን.ሕ.ቁ. 709/2/ ሥር እንደተመለከተው አንድ መጽናት ከጀመረ ገና ሶስት ዓመት ያልሞላው የሕይወት መድን ውል ተገብቶ በውሉ መሠረት በየዓመቱ መጀመሪያ ላይ መከፈል የሚገባው አረቦን ኖሮ ለምሳሌ በ3ኛው ዓመት መግቢያ ላይ መከፈል የነበረበት ሳይከፈል ቢቀር መድን ሰጪው እንዲከፈል ጥያቄ ያቀርብና ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለው ውሉን ሊያፈርስ እንደሚችል እናያለን።[44]

ይሁን እንጂ ፖሊሲው ውሉ መጽናት ከጀመረ አንስቶ እጅግ በጣም ሶስት ዓመታዊ የአረቦን ክፍያዎች የተከፈሉበት ከሆነና ለምሣሌ የአራተኛው ዓመት አረቦን በወቅቱ ካልተከፈለው መድን ሰጪው አንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችልና ጥያቄ ባቀረበ በ1ወር ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለው ውሉ ውድቅ መሆኑ ወይም መፍረሱ ቀርቶ መድን ሰጪው ከዚህ በታች ከተመለከቱት ሁለት አማራጮች አንዱን መፈጸም እንዳለበት በን.ሕ.ቁ. 709/3/ ሥር ተደንግጐአል።

አማራጮቹም፡-

1/ ለተከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ፖሊሲ መስጠት ወይም

2/ የተስማሙበትን ዋና ገንዘብ ወይም በሕይወት እስካለ ድረስ የሚከፈለውን ገንዘብ በን.ሕ.ቁ. 656 መሠረት በሚወጣው ደንብ መሠረት መቀነስ ናቸዉ።

---

[44] በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር የተመለከተው የእገዳ ጊዜ በቁጥር 709 ላይ አይታይም።

የመጀመሪያውን አማራጭ ለመከተል የፈለገ መድን ሰጪ አሁን ሥራ ላይ ባለውና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምበት የሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ "የአረቦን ክፍያ ሲቋረጥ" በሚለው ክፍል ሥር እንደተመለከተው የሚያደርገው "የአረቦን ክፍያው በተቋረጠበት ጊዜ ውሉ ባፈራው የጥሬ ገንዘብ ዋጋና መድን በገባው ሰው ዕድሜ ላይ የተመሠረተ የተቀነሰና በሙሉ የተከፈለበት የመድን ፖሊሲ መስጠት" ሲሆን ሁለተኛውን አማራጭ ለመከተል ከፈለገ ግን አሁንም በዚሁ በሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ እንደተመለከተው ማናቸውንም በመድን ገቢው ላይ የሚፈለገውን ዕዳ ቀንሶ ውሉ ያፈራውን የጥሬ ገንዘብ ዋጋ በጥሬ ገንዘብ ባንዱ ይከፍላል ወይም ደግሞ በተደረገው ቅናሽ መሠረት መድን ገቢው በሕይወት እስካለ ድረስ በየጊዜው የሚከፈለውን ገንዘብ ይሰጠዋል።

ከዚህ በላይ በን.ሕ.ቁ. 709/3/ ከተጠቀሱት ሁለት አማራጮች በተጨማሪ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምበት 3ኛ አማራጭ በሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ ይታያል። ይኸውም "የተራዘመ ተርም መድን" /ኤክሰተንድድ ተርም ኢንሹራንስ/ በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሲሆን ተግባራዊነቱም "ውሉ የሚኖረውን የተጣራ የጥሬ ገንዘብ ዋጋንና የመድን ገቢውን ዕድሜ እግምት ውስጥ በማስገባት ከመድን ገቢው ላይ የሚፈለገውን ማንኛውንም ዕዳ ቀንሶ መድን ገቢው በደረሰበት ዕድሜ የፖሊሲው የጥሬ ገንዘብ ዋጋ የሚገዛውን በማስላት ውሉ ለዚያን ያህል እንዲቀጥል ማድረግ ሲሆን" በእንግሊዝኛው የሕይወት መድን ፖሊሲ ቅጂ ላይ እንደተመለከተው የፖሊሲው የጥሬ ገንዘብ ዋጋ የመድን ገቢውን ዕድሜ ተንተርሶ የተራዘመ ተርም መድን ገዝቶ የሚተርፍ ከሆነ መድን ገቢው የተራዘመው ጊዜ ሲያልቅ በሕይወት ኖሮ ከተገኘ ተራፊው ገንዘብ እንደ አንድ ጊዜ አረቦን ተቆጥሮ ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚያስገኝለት ተመልክቷል።

ከተዋዋይ ወገኖች ያንደኛው መክሠር

የን.ሕ.ቁ 671-673 ድንጋጌዎች በተመለከተ ድንጋጌዎች ሲረቀቁ ምን ታሳቢ እንደተደረገ ፒተር ዊንሺፕ እንደሚከተለዉ ይገልጹታል፦

> The effects of bankruptcy, of death and of the assignment of the object insured are regulated so as to maintain the effects of the insurance as far as possible, while at the same time safeguarding the parties' freedom to terminate the contract.[45]

የተዋዋይ ወገኖችን ዉሉን የማቋረጥ ነፃነት ሳይነካ ከሥረት፣ሞትና መድን የተገባለት ንብረት መተላለፍ የሚያስከትሏቸዉን ዉጤቶች ለመቆጣጠር እንዲቻል በተቻለ መጠን ዉሎቹ ዉጤታማ ሆነዉ እንዲቀጥሉ ተደርጓል። (ትርጉም የፀሃፊዉ)

---

[45] Peter Winship, ቀደም ሲል በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 15 የተመለከተዉ ገጽ 83

ይህንኑ መሠረት አድርገን ድንጋጌዎቹን ከዚህ በታች እንመለከታቸዋለን።

በን.ሕ.ቁ. 671/1 ሥር ሠፍሮ እንደምናገኘው አንድ መድን ገቢ ከከሠረ የመድን ውሉ በዚሁ ምክንያት ብቻ አይፈርስም። የከሣሪው መድን ገቢ ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች በውሉ ተጠቃሚና ለመድን ሰጭው ለሚከፈለው አረቦን ተጠያቂ ባለዕዳ ሆነው የመድን ውሉ ፀንቶ ይቆያል።

በን.ሕ.ቁ. 671/1/ ሥር የሚታየው ድንጋጌ ሁሉንም መድን ገቢ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። የሚመለከተው የከሠረን መድን ገቢ ሲሆን ማንኛውም መድን ገቢ ደግሞ ከሠረ ሊባል እንደማይቻል መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ በያገኘው ንዑስ ርዕስ ምን ዓይነት መድን ገቢ "ከሠረ" ሊባል እንደሚቻልና "ክሥረት" ራሱ ምን እንደሆነ "ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች" ማለት እነማን እንደሆኑ በመጠኑም ቢሆን ለአንባብያን ማስተዋወቁ አስፈላጊ ይሆናል።

በመጀመሪያ "ከሠረ" የሚለው አባባል ተፈጻሚነቱ የሙያ ሥራው አድርጐ ጥቅም ለማግኘት ሲል በን.ሕ.ቁ. 5 ከተዘረዘሩት ሥራዎች መካከል አንዱን በሚሠራ በማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ላይና ከእሽሙር ማሕበር በስተቀር በመመሥረቻ ጹሑፍ መሠረት ወይም በተግባር በን.ሕ.ቁ. 5 ከተዘረዘሩት ሥራዎች አንዱን በሚሠራ የንግድ ማሕበር ላይ ብቻ መሆኑን መረዳቱ ጠቃሚ ነው።[32] በሌላም በኩል የንግድ ማሕበራትን በተመለከተ በን.ሕ.ቁ.10(2) መሠረት በኢትዮጵያ ዉስጥ ዕዉቅና የተሰጣቸዉ ሁለት ኩባንያዎች ማለትም የአክሲዮን ማህበራትና ሓላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት የተቋቋሙት በን.ሕ.ቁ. 5 ከተዘረዘሩት ሥራዎች አንዱን ለመሥራት ይሁን አይሁን ዓይነተኛ የንግድ ጠባይ ያላቸዉ ማህበራት መሆናቸዉ መዘንጋት የለበትም።[46] "ከሠሩ" ልንላቸው የምንችለው እነማንን መሆኑን ካወቅን "ክሥረት" ራሱ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ባጭሩ መልስ ለመስጠት ይሞከራል። አንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማሕበር እንደከሠረ የሚቆጠረው ይኸው ግለሰብ ነጋዴ ወይም ዓይነተኛ የንግድ ጠባይ ያለው የንግድ ማሕበር ማንኛውንም ከንግዱ ሥራ ጋራ የተያያዘውን ዕዳውን መክፈል ያቋረጠና መክሠሩ በፍርድ የተወሰነ ሲሆን መሆኑን የንግድ ሕጉ ይገልጻል።[47]

ያንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማሕበር መክሰር የሚታወቀው ነጋዴው ወይም የንግድ ማሕበሩ ከንግድ ሥራው ጋር የተያያዙትን ዕዳዎች ለመክፈል

---

[46] የንግድ ህጉ በአንድ በኩል የንግድ ማህበራትን ባብዛኛዉ በመመሥረቻ ጽሁፍ እንሠራለን ብለዉ በሚሉት ወይም በተግባር በሚሠሩት ላይ ተመሥርቶ ዓይነተኛ ንግድ ጠባይ ያላቸዉ እና የሌላቸዉ በማለት በዓላማቸዉ ላይ ተመሥርቶ በሁለት ጎራ ሊከፍላቸዉ፣ በሌላ በኩል ግን የንግድ ማህበራቱ የሚቋቋሙበት ፎርም ብቻዉን ከሁለቱ ባንደኛዉ ጎራ ዉስጥ እንዲደመሩ ያደርጋቸዋል፣ ከዚህ የተነሳ በህጉ ዕዉቅና የተሰጣቸዉ ሁለቱ ኩባንያዎች ዓላማቸዉ ምንም ይሁን ዓይነተኛ ንግድ ጠባይ ያላቸዉ ማህበራት ተብለዉ ተወስደዋል።

[47] የን.ሕ.ቁ. 5፣ ከቁጥር 10 እና ከቁጥር 968 ጋር ተዳምሮ ሲታይ

ያለመቻሉን ከሚገልጹ ከማንኛውም ድርጊቶች፣ፍሮነገሮች (facts) ወይም ሠነዶች[48] ቢሆንም ቅሉ ነጋዴው ወይም ማሕበሩ ማንኛውንም ዕዳ መክፈል በማቋረጡ ብቻ ከሠረ ሊያሰኘው እንደማይችልና አንድ ሰው ወይም ማሕበር ከሠረ ለማለት የግድ ከንግድ ሥራው ጋር የተያያዘውን ዕዳ መክፈል ማቋረጥና የፍርድ ቤት የክሥረት ውሣኔ መሠጠት እንዳለበት እንረዳለን::[49] ሆኖም የአንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማሕበር ዕዳውን መክፈል ማቋረጥ ለፍ/ቤት ቀርቦ የክሥረት ውሳኔ ባይሰጥም በመክሠር ላይ በሚደረግ የማጭበርበር ወይም ሌሎች የወንጀል ሥራዎች የወንጀል ፍ/ቤት የቅጣት ፍርድ ሊፈረድ ይችላል::[50]

የክሥረትን ሁኔታ ለማስታወቅ የሚሰጠው ፍርድ የኪሣራውን ሥራ የሚመረምር አንድ ዳኛና አንድ ወይም ቁጥራቸው ቢበዛ ከሶስት የማይበልጥ የከሠረው ሰው ወይም የንግድ ማሕበር ንብረት የሚያስተዳድሩ ንብረት ጠባቂዎች መምረጥ /መሾም/ እንዳለበት የንግድ ሕጉ ሲደነግግ[51] ዋናው የንብረት ጠባቂዎች ሥራ የከሠረው ሰው ወይም ንግድ ማሕበርን ማስተዳደርና የአስተዳደር ሥራንም ሲያከናውኑ ግለሰቡ ወይም ማሕበሩ ከንግድ መዝገብ እስከሚፋቅ የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ለመጠበቅ የሚጥሩ ባለአደራዎች ናቸው::

ወደ ን.ሕ.ቁ. 671 መለስ ስንል የመድን ገቢው መክሠር ፖሊሲውን ወዲያውኑ (automatically) እንደማያቋርጠውና ምንም አንኳን መድን ገቢው ቢከሠርም በፍርድ ቤት የተሾሙት ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች በዚሁ የንግድ ሕግ ቁጥር መሠረት ማለትም በሕግ የመድን ውሉ ተጠቃሚ ሆነው ውሉ እንደሚቀጥል እንገነዘባለን:: የን.ሕ.ቁ 671/2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥር 671/1/ መድን ገቢው በመክሠሩ ምክንያት ብቻ ውሉ አይፈርስም ብሎ ሲያስቀምጥ በፍርድ ቤት የተሾሙት የከሣሪውን መድን ገቢ ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎችን የመድን ውሉ ፀንቶ እስከቆየ ድረስ ለአረቦን ተጠያቂ ባለዕዳዎች አድርጓቸዋል:: እዚህ ላይ ግልጽ መደረግ ያለበት ነገር ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች በውሉ ተጠቃሚነታቸው ሆነ ለአረቦን ተጠያቂነታቸው በግላቸው እንዳልሆነ ነው:: ተጠቃሚነታቸው ዞሮ ዞሮ ለዚያው ለከሠረው ግለሰብ ወይም የንግድ ማሕበር ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች ከመሆናቸው አንፃር እንጂ በግላቸው የመድኑ ውል ፖሊሲ የሚያስገኘውን ገንዘብ እንዲያገኙ አለመሆኑን ነው:: ይህንን ስንል ምናልባት ከክሥረት ውሣኔ በኋላ የመድን ውሉ ፀንቶ እያለ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስና መድን ሰጪው ካሣ ቢከፍል ካሣውን ተቀብለው ከከሣሪው ግለሰብ ወይም የንግድ ማሕበር ንብረት ይደምሩለታል ማለት ሲሆን ለአረቦኑ ተጠያቂነታቸው ከዚያው ከከሠረው ሰው ወይም የንግድ ማሕበር ሀብት ነው እንጂ በግል ከኪሣቸው አይደለም:: ንብረት ጠባቂ በለአደራዎች በህግ የተሰጣቸዉ ስልጣን የከሠረዉን ሰዉ ንብረት

---

[48] የን.ሕ.ቁ. 971

[49] የን.ሕ.ቁ. 970

[50] የን.ሕ.ቁ. 970/2/ እና በ1997 ዓ.ም የወጣዉን <u>የወንጀል ህግ</u> ከአንቀጽ 725 እስከ 733 ያሉትን ይመልከቱ::

[51] የን.ሕ.ቁ. 981

በመርማሪዉ ዳኛ ጥበቃ ሥር ሆኖ ማስተዳደር እና ተራ ገንዘብ ጠያቂዎችን በሙሉ በሰስተኛ ወገኖች ፊት የመወከል ነዉ::[52]

በን.ሕ.ቁ. 671 ላይ መድን ገቢው በመክሠሩ ምክንያት ብቻ ውሉ አይፈርስም ቢልም የመድን ገቢው ክሥረት በፍ/ቤት ከተወሰነ ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ውሉን ወይ መድን ሰጪው ወይም ንብረት ጠባቂዎቹ ሊያፈርሱት እንደሚችሉ በን.ሕ.ቁ. 671/2/ ሥር ተደንግጐአል::

በአንድ በኩል በን.ሕ.ቁ. 671 "ተቃራኒ ውል ቢኖርም" የሚል አባባል ስለሌለ መድን ሰጪው በፖሊሲዎች ላይ "የመድን ገቢው ክስረት ውሉን ወዲያውኑ ከፍጻሜ ያደርስዋል" ብሎ ማስገባት የሚችል ቢመስልም በሌላ በኩል ግን ይህ ዓይነቱ ስምምነት ካጠቃላይ የን.ሕ.ቁ. 671/1/ ድንጋጌ መንፈስ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ አይመስልም::[53]

ለማነፃፀር ያህል በባህር ሕግ በቁጥር 299 ሥር የተደነገገዉን መመልከቱ መልካም ነዉ:: በእንግሊዝኛ የህጉ ቅጂ በንኡስ ቁጥር (1) "the underwriter may terminate policies in force in the event of the bankruptcy of the assured" ተብሎ ተደንግጐአል:: ይህ ድንጋጌ መድን ገቢዉ የከሠረ እንደሆነ ዉሉን የማቋረጥ መብትን ለመድን ሰጪዉ ሰጥቶ የንዑስ ቁጥሩ የአማርኛ ቅጂ ግን ዉሉን የማፍረስ መብት ነዉ የሚሰጠዉ::[54] ሎቹን የባህር ሕጉን የቁጥር 299 ድንጋጌዎች አንባቢዉ እንዲያዉቃቸዉ በግርጌ ማስታወሻነት ተዘርዝረዋል::[55]

---

[52] የን.ሕ.ቁ. 985(1)

[53] ሕጉ በተለያዩ ሁናቴዎች የመድን ውል ፖሊሲ ወደ ሌላ ተላልፎ እንዲቀጥል የሚያዝበት ዋነኛው ምክንያት የ"risk" ጥያቄ በውስጡ ስላለ ሰዎችን ድንገት ለአደጋ እንዳይጋለጡ መሸጋገሪያ ጊዜ ለመስጠት ሳይሆን አይቀርም::

[54] የባህር ሕግ ቁጥር 299(1) የአማርኛዉ ቅጂ የሚለዉ" ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ የከሠረ እንደሆነ ኢንሹራንስ አድራጊዉ የተጀመረዉን ኢንሹራንስ ሁሉ ማፍረስ ይችላል" ነዉ::

[55] ቁጥር 299(2) ለኢንሹራንሱ የሚከፈለዉ ገንዘብ በጊዜዉ ያልተከፈለና ኢንሹራንስ የተደረገለት ሰዉ በሃያ አራት ሰዓት ዉስጥ እንዲከፍለዉ ማስጠንቀቂያ ከላከለት በኋላ ይህ የማፍረስ ችሎታ ይኖረዋል::

(3) የዉሉ መፍረስና ግዴታዎች እንዲፈፀሙ የሚደረገዉ ማስጠንቀቂያ በሬኮማንዴ ደብዳቤ ወይም በቴሌግራም ሊደረጉ ይችላሉ::

(4) የሚከፈሉት የጉዳት ኪሳራዎች ሳይነኩ የዉሉ መፍረስ ይደርሳሉ ተብለዉ ለሚያሰጉት አደጋዎች (ሪስክ) ከተወሰኑት ጊዜዎች ባልደረሱት ጊዜዎች መጠን ለኢንሹራንስ ከተሰፈሰዉ ገንዘብ ላይ ተመላሽ ይደረጋል::

(5) ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ ያልከፈለዉን የኢንሹራንስ ዋጋ ሦስተኛ ወገን ከከፈለ ማንኛዉም አደጋ ከመድረሱና የዉሉ መፍረስ ማስታወቂያ ከመላኩ በፊት ኢንሹራንስ በተላለፈለት በቅን ልቡና ተጠቃሚ በሆነ ሦስተኛ ወገን ላይ የዉሉ መፍረስ ዉጤት አይኖረዉም::

(6) ኢንሹራንስ አድራጊዉ በከሠረ ጊዜ ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ እንደዚሁ ያሉ መብቶች ይኖሩታል::

የመድን ሰጪው መክሰር የግድ ውሉን ወደ ፍጻሜ እንደሚያመጣው በን.ሕ.ቁ. 671/3/ ላይ ተመልክቷል። የመድን ገቢው ክሥረት የግድ የውሉን መቀጠል ባያቆመውም የሰጪው ክስረት ግን የክስረቱ ውሣኔ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሉን እንዲያቋርጠው ሕግ ደንግጐአል። የመድን ሰጪው ክስረትና በዚህም ምክንያት የውሉ /ማለቅ/ ማቋረጥ ምን ውጤት እንደሚያስከትል ሕጉ ያለዉ ነገር ባይኖርም እስከ ክሥረቱ ውሣኔ ድረስ የመድን ፖሊሲዎቻቸው የበሰሉ መድን ገቢዎች የከሣሪው መድን ሰጪ ገንዘብ ጠያቂ /ክሬዲተርስ/ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲገመት ፖሊሲዎቻቸው ያልበሰሉ መድን ገቢዎች ከውሉ መቋረጥ ባሻገር ላለው ጊዜ የከፈሉትን አረቦን ከከሣሪው መድን ሰጪ መጠየቅ መገመት ይቻላል።

የን.ሕ.ቁ. 671 ድንጋጌ በካሣ መድኖች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ስለመሆኑ ለመረዳት በንግድ ሕጉ ውስጥ የሠፈሩትን የካሳ ያልሆኑ መድኖችን የሚመለከቱትን ድንጋጌዎች ማየቱ በቂ ነው ። ይህ ንዑስ ርዕስ ከማጠቃለሉ በፊት ሌላው መነሣት ያለበት ነጥብ የን.ሕ.ቁ. 671 እና ምናልባትም ተከታዮቹ የመድን ውል አስተላላፊ ድንጋጌዎች ናቸው ወይንስ የመድን ጥቅም? የሚለውን ጥያቄ የን.ሕ.ቁ. 673 ን ስንመለከት የምንመለስበት መሆኑን ነዉ።

የመድን ውል ተጠቃሚ መሞት

ስለመድን ፖሊሲ በሕግ መተላለፍ የሚያወሳው ሌላው ቁጥር የን.ሕ.ቁ. 672 ሲሆን በዚህ ቁጥር ንዑስ ቁጥር /1/ ላይ እንደተመለከተው አንድ የንብረት መድን ወይም የሃላፊነት መድን ሽፋን[56] የገዛ ሰው ቢሞት የመድኑ ውል መብት ወደ ወራሾቹ ተላልፎ እንደሚቀጥል እናነባለን። ይህ የቁጥር 672/1/ ድንጋጌ ተፈጻሚነቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚያደርጉት ተቃራኒ ስምምነት እንደማይገታ ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም እንኳ በሚለው የራሱ የሕጉ ሐረግ ስለተነገረ ማንኛውም በፖሊሲው ውስጥ ይህን የ 672/1/ን አባባል የሚቃረን ስምምነት ካለ ውድቅ ይሆናል። የመድን ገቢው መሞት ውሉን ወዲያውኑ (forthwith) አያቋርጠው እንጂ መድን ገቢው በሞተ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ወራሾቹ ወይም መድን ሰጪው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችሉ በንዑስ ቁጥር /2/ ሥር ተጽፎአል። ከፈለጉም ውሉን ከመቀጠል የሚያግዳቸው ምንም ነገር የለም።

---

[56] ለሞት ከተደረገ የሕይወት መድን አንፃር አንድ መድን ገቢ ቢሞት ፖሊሲው ገንዘብ ሊጠየቅበት የሚችል የበሰለ ፖሊሲ ይሆናል። ተጠቃሚውም ፖሊሲው የሚያስገኘው ገንዘብ እንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። ከውሉ ምሥረታ ቀን ጀምሮ ወደፊት ለዚህን ያህል ዓመት ወይም እስከ ተወሰነ ቀን /ዓመተ ምሕረት/ ወዘተ በሕይወት ኖሬ ከተገኘሁ የተወሰነ ገንዘብ ትከፍለኛለህ በሚል የተገዛ ፖሊሲ ከሆነ በውሉ መሠረት ገንዘብ ሊገኝ የሚችለው መድን ገቢው በውሉ ውስጥ በተመለከተው ቀን በሕይወት ኖሮ ሲገኝ ብቻ ነው። /የን.ሕ.ቁ. 702/

መድን የተገባለትን ንብረት ስለማስተላለፍ

ከመድን ሰጪው ፈቃድ ውጪ በሆነ ሁኔታ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ባይኖርም በን.ሕ.ቁ. 673 /1/ ላይ በግለጽ ተጽፎ እንደሚገኘው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ በሽያጭ ወይም በስጦታ[57] ሲተላለፍ የመድኑ ውልና መብት በሙሉ ንብረቱ ወደ ተላለፈለት ሰው ይተላለፋል። ሕጉ እንደዚህ ቁልጭ ባለ ሁኔታ ቢቀመጥም የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች አንዳንዶቹን[58] ስናይ መድን የተገባለት ንብረት በሽያጭ ወደ ሌላ ሲተላለፍ የመድን ውሉ ወዲያውኑ እንደሚቋረጥ ተመልክቷል።

ምናልባት በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58 ላይ ለምሣሌነት በተጠቀሱት ሁለት ፖሊሲዎች ውስጥ መድን ሰጪው ንብረቱ በሽያጭ ሲተላለፍ ከተሸጠበት ጊዜ ጀምሮ ፖሊሲው ይቋረጣል ብሎ ያሠፈረው በን.ሕ.ቁ. 673/2/ ሥር ሕግ ውሉን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለማቋረጥ ለርሱም ሆነ ንብረቱ ለተላላፈለት ሰው መብት ስለሚሰጥ ይሆናል ብሎ መጠራጠር ይቻል ይሆናል፣ ነገር ግን ይህ በንዑስ ቁጥር /2/ ለመድን ሰጪውና ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው የተሰጠው መብት በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር የተደነገገዉን በሚቃረን ሁኔታ ተዋዋዮቹን ማገልገል የለበትም።

የን.ሕ.ቁ 673/1/ ተፈጻሚነት መድን ሰጪው በሚጠቀምባቸው እንደ የግል ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ፖሊሲና የንግድ ተሽከርካሪ ፖሊሲዎች ላይ ተጽፎ የሚታየውን ዓይነት የውል ቃል ከግምት ውስጥ ሳያስገባ መሆኑ "ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም" በሚል ሐረግ ተመልክቷል። ከዚህ በላይ በን.ሐ.ቁ. 671 እና 672 ላይ የሠፈሩትን በተመለከተ በተብራራዉ መሠረት የቁጥር 673/1/ እና /2/ ጥምር መልዕክትም መድን የተገባለት ንብረት ከተላለፈ በኋላ ውሉ የግድ ንብረት በተላለፈለት ሰውና በመድን ሰጪው መካከል መቀጠል አለበት ሳይሆን ሕግ ሊከላከል የፈለገው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ በመተላለፉ የውሉን በዚሁ ምክንያት ብቻ ወዲያውኑ መቋረጥ ነው። ለምሳሌነት በተጠቀሱት ሁለት ፖሊሲዎች ላይ የሠፈረው ግን በቀጥታ በን.ሕ.ቁ. 673/1/ ሥር የተጻፈውን የሚቃረን ይመስላል። ሲሆን ንብረት ካስተላለፈው መድን ገቢና በመድን ሰጪው መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ፖሊሰው ለሶስት ወርና ከዚያ በላይ የሚቆይ ከሆነ ውለታው በአዲሱ ንብረት በተላለፈለት ሰውና በመድን ሰጪው መካከል እስከ ሶስት ወር ፀንቶ መቆየት እንዳለበት ሲገመትና ንብረት የተላለፈለትም ሰው ይህንን መከራከሪያ ሊያደርግ እንደሚችል ቢታይም መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ ከተላለፈ ጊዜ ጀምሮ 3 ወር ሳይሞላ ውሉን ከሁለት አንዳቸው ማቋረጥ እንደሚችሉ ግን አያከራክርም።

---

[57] በመያዣነት ወይም በአላባ ስምምነት ይዞታ ሲተላለፍ ጉዳዩ በን.ሕ.ቁ.673 ሥር ይሸፈን አይሸፈን ሊያከራክር ቢችልም ለጊዜው በግር ወይም በስጦታ ብቻ ስለሚተላለፍ ንብረት ማውሳቱ ብቻ በቂ ይሆናል።

[58] ለምሳሌ የግል ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ፖሊሲና የንግድ ተሽከርካሪ ፖሊሲን ይመልከቱ።

ምናልባት በን.ሕ.ቁ. 666፣ 668፣ 669፣ እና 671፣ ላይ የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ በተለይም ደግሞ በን.ሕ.ቁ. 666/3/ እና በቁ. 668/2/ /ሀ/ ሥር ሠፍሮ የሚገኘው መድን ሰጪው ውሉን ለማፍረስ አጅግ ቢያንስ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ መስጠት እንደሚያስፈልገው የሚናገሩት ድንጋጌዎች መድን ሰጪው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ መተላለፉን ካወቀ ጊዜ ጀምሮ ውሉን ለማፍረስ ከፈለገ ቢያንስ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ንብረት ለተላለፈለት ሰው መስጠት እንዳለበት ይጠቁማሉ ለማለት ይቻላል። መድን ሰጪው ውሉን በሶስት ወር ጊዜ የማፍረስ መብቱን ባግባቡ ሊጠቀምበት ከፈለገ ማድረግ የሚችለው ወይም የሚገባው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ መተላለፉን እንዲያስታውቅ ወይም በንብረት አስተላላፊው ላይ ወይም ሕግ የውሉ መብት ተጠቃሚ ባደረገው ንብረት በተላለፈለት ሰው ላይ የማስታወቅ ግዴታን መጣል እንጂ የሕጉን መንፈስ በሚቃረን ከዚህ በላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58 ላይ በተጠቀሱት ሁለት ፖሊሲዎች ላይ ተጽፎ እንደምናነበው ማድረግ የለበትም።

በርግጥ የመድን ሽፋን ያለው ንብረት ለሌላ ሲተላለፍ መድን ሰጪው ውሉ ወዲያውኑ እንዲቋረጥ አድርጐ እንዲያዘጋጅ የሚገፋፉት በርካታ አሳማኝ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉምና ከነዚህ ውስጥ ዋነኛው የንብረት መተላለፍ መድን የተገባለትን አደጋ ሊያከብድ የመቻሉ ጉዳይ ቢሆንም መድን ሰጪው ሕግ ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው የሚሰጠውን መብት ከሕጉ መንፈስ ውጪ ሊያጠበበት አይገባም፣ አይችልምም።

በጀርመን ፌደራል ሪፑብሊክ እ.ኤ.አቆጣጠር ከ1910 ጀምሮ[59] መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ ሲተላለፍ የመድኑ ውል መብትና ግዴታ በሙሉ ከአስተላላፊው መድን ገቢ ንብረቱ ወደ ተላለፈለት ሰው እንደሚሸጋገር ተደንግጐ ይገኛል።[60] ይህም ስለውሉ መተላለፍ ምንም ዓይነት ውለታ ማድረግ ሳያስፈልግ እንደሆነና የግድ መደረግ ያለበት ነገር ቢኖር መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ መተላለፉን ለመድን ሰጪው ማስታወቅ መሆኑን ስንረዳ[61] አለማስታወቅም መድን ሰጪውን ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርገው ማስታወቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ መድን የተገባለት አደጋ የደሰው የአንድ ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ ከሆነ ነው ተብሎ በዚሁ እ.ኤ.አ. ከ1910 ጀምሮ ሥራ ላይ በዋለው በጀርመን የግል መድን ሕግ በ71ኛው ሴክሽን ላይ ተጽፎ እናነባለን።[62] ከዚሁ በመነሳት ሚስተር ፖተርሰን በጀርመን የግል መድን ሕግ መድን የተገባለት ንብረት ሲተላለፍ የመድኑ ውሉ መብት ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው መሸጋገር ምንም እንደሚያከራክርና ይኸውም መብት ወዲያውኑ

---

[59] Edwin W. Patterson "The Transfer of Insured Property in German and American Law," Columbia Law Review, Vol. 29 (1929) pp.691 ff.

[60] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ ገጽ 693።

[61] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ።.

[62] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ።.

ንብረቱ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአንድ ወር መድን ሰጪውን ለመድኑ ዋስትና ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው ተገዳጅ እንደሚያደርገው ይናገራሉ።[63]

በአሜሪካና በእንግሊዝ አገር ባጠቃላይ አነጋገር ምናልባት በንብረቱ ማስተላለፊያ ውል ላይ ወይም በሌላ ተጨማሪ ውል የመድን ውልም ከንብረቱ ጋር አብሮ ተላልፎአል ካልተባለ በስተቀር የንብረቱ መተላለፍ ብቻውን የፖሊሲውን መተላለፍ እንደማያስከትል ይነገራል።[64]

በእንግሊዝ አገር መድንና ተያይዘው ያሉትን ጥቅማጥቅሞችን የማስተላለፉ ጉዳይ ከሶስት አቅጣጫ ነው የሚታየው። እነኚህም 1ኛ/ የተገባለትን ንበረት ከማስተላለፍ አኳያ 2ኛ/ አንድ የመድን ውል የሚያስገኘውን ጥቅም ከማስተላለፉ አኳያ እና 3ኛ/ የመድን ውል ከማስተላለፍ አኳያ ሲሆን በኢትዮጵያ ሕግ ግን የሕይወት መድን ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የንብረት መድንን በሚመለከት እነኚህ የተጠቀሱት ሶስት ሁኔታዎች ተለይተው የሚታዩ አይመስሉም። በን.ሕ.ቁ. 671፣ 672 እና 673 ላይ እንደተመለከተው ሁሉም የውሉን መተላለፍ የሚያስከትሉ ይመስላል።

በውሉ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ

ሀ. የመድን ገቢው ኃላፊነት

በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ላይ እንደተደነገገው አንድ መድን ገቢ ከአቅሙ በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ማሳወቅ ያልቻለ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር መድን ሰጪው ሽፋን የሰጠበት አደጋ መድረሱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ወይም እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ ለመድን ሰጪው ማስታወቅ አለበት።

ከዚህ በላይ በውሉ ምሥረታ ጊዜ እንደዚሁም ደግሞ ውሉ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተፈራው አደጋ መድረስ ባለው ጊዜ የተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታ ለመመልከት ተሞክሮአል። በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የምናየው ተፈርቶ መድን የተገባለት አደጋ ሲደርስ መድን ገቢው ምን ማድረግ እንዳለበት ሲሆን ቀጥሎ በመግቢያው ላይ እንደተመለከተው በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር የተጣለበትን ግዴታ እንመረምራለን።

በን.ሕ.ቁ 670/1/ የአማርኛው ቅጂ መሠረት መድን ገቢው ማስታወቅ የሚገደደው መድን ሰጪው ኃላፊነት የወሰደበትን አደጋ መድረስ እንጂ ሌላ አደጋ መድረሱን አይደለም። ለምሣሌ በን.ሕ.ቁ. 677 ሥር ተጽፎ እነደምናነበው መድን የተገባለት ንብረት ወይም ዕቃ በመድኑ ውል ውስጥ ባልተመለከተ አደጋ ቢወድም በዚሁ

---

[63] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ።.

[64] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 የተመለከተው ገጽ 138-142፤ እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ ቁ 56 ላይ የተመለከተው ገጽ 697 እና ተከታዮቹን ገጾች ይመልከቱ።

ቁጥር ሥር በተጻፈው መሠረት ውሉን ለማስፈረስ ስለአደጋው ያስታውቅ እንደሆነ ነው እንጂ በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር የተጻፈው ግዴታ ተፈጻሚ ሆኖበት አይደለም።

በን.ሕ.ቁ. 670/1/ የእንግሊዝኛው ቅጂ ከተሄደ "... the beneficiary shall inform the insurer of any occurrence likely to render the insuerr liable..." ሰለሚልና ከአማርኛው ቅጂ አነጋገር የሰፋ ስለሚሆን ማንኛውንም መድን ሰጪውን በውሉ የገባበትን ግዴታ ለመፈጸም ሃላፊ የሚያደርገው ሁኔታ መድረሱን ማስታወቅ እንደሚሆን እንረዳለን። በእንግሊዝኛው ቅጂ ከተሄደ በን.ሕ.ቁ 670/1/ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ በሕይወት ኖሬ ከተገኘሁ ይህን ያህል ብር ትከፍለኛለህ በሚል የሕይወት መድን ውል ላይና በኃላፊነት መድንም ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ሲገመት በአማርኛ ቅጂ ከተሄደ ግን የቁ. 670/1/ ተፈጻሚነት በንብረት መድንና ለሞት በሚገባ መድን ላይ ብቻ የተገደበ ይመስላል። የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች የእንግሊዝኛውን ቅጂ ይከተላሉ። በአማርኛውና እንግሊዝኛው የን.ሕ.ቁ 670/1/ አባባል መካከል ስላለው ልዩነት ይህን ያህል ካልን ወደዋናው በዚሁ በቁጥር 670 ሥር ስለተጻፈው ግዴታ እንመለሳለን።

የደረሰው አደጋ መድን ገቢው ራሱ የተሳተፈበት ለምሳሌ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ ሾፌር ሆኖ እየነዳ እያለ አደጋ ቢደርስ ወይም መኖሪያ ቤቱን ለእሳት ቃጠሎ መድን አስገብቶ የቃጠሎ አደጋ ሲደርስ ቤቱ ውስጥ ከነበረና ራሱ ግን ከመቃጠል ያመለጠ ከሆነ ወዘተ የአደጋውን መድረስ ማወቁ ምንም አጠራጣሪ ስላልሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ወይም አደጋው የደረሰው ከሥራ ሰዓት ውጭ ወይም በበአል ቀን[65] ካልሆነ የአደጋውን መድረስ ማስታወቅ ያለበት ወዲያውኑ[66] ነው። ምናልባት "ወይም እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ" የሚለው የን.ሕ.ቁ 670/1/ አባባል ከላይ ለማመልከት በተሞከረውና መድን ገቢው ራሱ በነበረበት የአደጋ ሁኔታ አሳሳች ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይገመታል። ሆኖም ግን አንድ መድን ገቢ አደጋው ሲከሰት ቢኖርም አደጋው በደረሰ እስከ አምስት ቀናት ውስጥ ቢያስታውቅ /ከዐቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ማጋጠም እንደተጠበቀ ሆኖ/ ከሕጉ ውጪ ስላልሆነ ሊከራከርበት ይችላል።

ሌላኛው በዚህ ርዕስ ሥር መነሳት ያለበት ነጥብ ለመድን ሰጪው አደጋ መድረሱን የማሳወቅ ሁኔታ መነሻው የመድን ገቢው የራሱ ያደጋውን መድረስ ማወቅ መሆኑን ነው። መድን ገቢው በቦታው ላይ በክስተቱ ጊዜ ኖሮ ያደጋውን መድረስ ካላወቀ ምናልባት አደጋ ደርሶ ለመድን ሰጪው ሳይነገረው ወራት ሊያልፉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። መድን ገቢው ያደጋውን መድረስ

---

[65] መድን ሰጪው ከሥራ ሰዓት ውጪና በበዓላት ቀናት የአደጋ ማስታወቂያን የሚቀበልበትን ሁኔታ አመቻችቶ ይህንኑ ለደምበኞቹ ካላሳወቀ በቀር

[66] "ወዲያውኑ" የሚለው አባባል ራሱ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። ምናልባት "ሊገኝ በሚችል ፈተሻለ ፈጣን መንገድ" ማለት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችል ይሆናል።

መረጃ እንደገኘ ወዲውኑ ወይም እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ /ከዐቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ/ ለመድን ሰጪው ማስታወቅ እንዳለበት ነው የምንረዳው። ይህንን የምንልበት ምክንያት በን.ሕ.ቁ 670/1/ አነጋገር አደጋው እንደደረሰ ወዲያውኑ ወይም አጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ ማስታወቅ አለበት የማይል መሆኑን ለማስገንዘብ ያህል ነው። በን.ሕ.ቁ. 670/2/ ሥር እንደተጻፈው በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር የተጻፈውንና ጊዜን የሚመለከተውን አነጋገር ማስረዘም ይቻል እንደሆነ እንጂ ማሳጠር እንደማይቻል መረዳቱ ቀላል ነው።

የአደጋን መድረስ የማስታወቅን ግዴታ ከአንዳንድ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች አንፅር ለማየት መሞከሩ በሕጉና በተግባር በሚሠራው መካከል ስምምነትም ይሁን ልዩነት መኖሩን ስለሚጠቁም ይህንኑ ከዚህ በታች ባጭሩ እንመለከታለን። በሠራተኞች የካሳ መድን /workmen's compensation policy/ ላይ እንደ 4ኛው ሁኔታ (condition) የሠፈረዉ በፖሊስው መሠረት ካሣ የሚያስጠይቅ ሁኔታ መድረሱን መድን ገቢው "በተቻለ ፍጥነት" ለመድን ሰጪው ማስታወቅ አለበት የሚል ሲሆን በኃይል ሠብሮ በመግባት ፖሊሲ፣ በእሳትና መብረቅ ፖሊሲ፣ እና በግልና ንግድ ተሸከርካሪዎች ፖሊሲዎች ላይ ደግሞ ካሣ የሚያስጠይቅ ሁኔታ እንደደረሰ "ወዲያውኑ" ማስታወቅ አለበት ተብሏል። የሁሉም ዓይነት አደጋ መድን ፖሊሲ /all risks policy/ በሚባለው ላይ ደግሞ መድን በተገባለት ንብረት ላይ አደጋ መድረሱን መድን ገቢው ከደረሰበት በኋላ "ተግባራዊ ሊሆን በሚችል በተቻለ ፍጥነት" /As soon as practicable/ ማስታወቅ እንዳለበት ተጽፎ እናነባለን።

በአካል ጉዳት መድን ፖሊሲ ላይ (As soon as possible after its occurrence) "አደጋው ከደረሰ በኋላ በተቻለ ፍጥነት" ተብሎ ሲጻፍ ለሞት በተደረገ የሕይወት መድን ግን ለሞቱ መንስዔ የሆነው አደጋ ከሆነ ወዲያውኑ ማስታወቅ እንደሚያስፈልግ ሲያመለክት መንስኤው አደጋ ላልሆነ ሞት ግን በሰላሣ ቀናት ውስጥ ማስታወቅ እንደሚቻል ተጽፎአል። ይሽኛው የኋለኛው ፖሊሲ ከዐቅም በላይ የሆነውን ሁኔታም ከግምት ውስጥ ሲያስገባ ሌሎቹ ፖሊሲዎች ግን በዝምታ አልፈውታል።

ከፖሊሲዎች አኳያ ዋናው መነሳት ያለበት ነጥብ በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር "እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ" ተብሎ የተጻፈው አባባል በማንኛውም ፖሊሲ ውስጥ ተጽፎ አለመገኘቱንና ይህ አለመጻፉ ደግሞ የመድን ገቢውን መብት በሕግ ከተሰጠው ማጥበብ መሆኑን ነው። አደጋን በስምምነቱ መሠረት ማስታወቅ ለመድን ሰጪው በኃላፊነት መጠየቅ እንደ ቅድመ ሁኔታ /Condition precedent/ የሚቆጠር መሆኑ ባብዛኞቹ ፖሊሲዎች ላይ ሲጠቀስ በአንዳንዶቹ ግን ቅድመ ሁኔታ መሆኑ አልተጠቀሰም።[67]

[67] ለምሣሌ Commercial Motor Policy (third party) እና Workmen's Compensation Policy.

የመድን አገልግሎት ኢንዱስትሪ በጣም ተስፋፍቶ ባለበት በእንግሊዝ አገር ሁኔታ (Condition) ወይ "ተራ" ወይም ደግሞ ቅድመ ሁኔታ /Condition precedent/ ተብሎ የሚከፈል ነዉ። በፖሊሲዎች ላይ እንደ ቅድመ ሁኔታ ያልተመለከቱት ነገሮች የመድን ሰጪውን ኃላፊነት ላያስቀሩ እንደሚችሉ ስንገነዘብ[68] በቅድመ ሁኔታነት የተጠቀሱት ጉዳዮች ያለመሟላት ግን መድን ሰጪው የካሣ ጥያቄ ከቀረበበት አደጋ አኳያ ብቻ ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርጉት ናቸው። [69]

ለ. የመድን ገቢው መብት

መድን ገቢው በውሉ የተመለከተው አደጋ መድረሱን ወይም ሌላ ማንኛውንም መድን ሰጪውን በኃላፊነት የሚያስጠይቀው ነገር መፈጸሙን የማስታወቅ ግዴታ እንዳለበት ሁሉ በውሉ መሠረት እንዲካስ ወይም ስምምነት የተደረገበት ገንዘብ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብትም አለው። መድን ገቢው የካሣ ጥያቄውን በምን ያህል ጊዜ ለመድን ሰጪው ማቅረብ እንዳለበት በሕጉ ላይ የተመለከተ ነገር ባይኖርም በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር አደጋ መድረሱን ሲያስታውቅ በዚያው የካሣ ጥያቄውንም ያቀርባል ተብሎ በውስጠ ታዋቂነት ተካትቷል ወይም የካሣ ጥያቄን ማቅረብ ለሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተተወ ጉዳይ ነው ማለት ይቻል ይሆናል።

በሕጉ ላይ የተባለ ነገር ባይኖርም በመድን ውሉ መሠረት ገንዘብ እንዲከፈለው ወይም እንዲካስ ጥያቄ የማቅረብ ሁኔታ ግን በሁሉም ፖሊሲዎች ላይ ተመልክቷል። በዚሁ መሠረት በአንዳንዶቹ ላይ የተጻፈውን ብንቃኝ በሠራተኞች የካሣ መድን ፖሊሲ ላይ መድን ገቢው እንዲክስ ጥያቄ እንደቀረበለት ወዲያውኑ ለመድን ሰጪው ጥያቄውን መላክ እንደለበት ሲጻፍ በኃይል ሠብሮ በመግባት ፖሊሲ ደግሞ በ5ኛው /መ/ ሁኔታ ሥር የመድን ሰጪውን ኃላፊነት የሚያስከትለው ማንኛውም ሁኔታ እንደተፈጸመ በተቻለ ፍጥነት ወይም ለማንኛውም ኃላፊነትን የሚያስከትለው ሁኔታ በደረሰ በ14 ቀናት ውስጥ የካሣውን ጥያቄ ከዝርዝር ሁኔታዎች ጋር ማቅረብ አለበት ሲል ጥያቄው በጽሑፍ ሰለመቅረቡ ግን አይናገርም። የእሳትና የመብረቅ መድን ፖሊሲ አደጋው ከደረሰ በኋላ በ15 ቀናት ውስጥ ወይም እንደሁኔታው መድን ሰጪው በጽሑፍ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የካሳ ጥያቄውን ማቅረብ አለበት ይልና ጥያቄውም በጽሑፍ መቅረብ እንዳለበት ያመለክታል።

የመድን ሰጪው ግዴታ

ከዚህ በፊት ለማመልከት እንደተሞከረው የመድን ውል በመድን ገቢ ላይ ከምሥረታው ጀምሮ ተፈጻሚ ሲሆን በመድን ሰጪው ላይ ተፈጻሚ የመሆኑ ጉዳይ ግን በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም ማለት መድን ሰጪው የውሉን

---

[68] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ላይ የተመለከተው ገጽ 126።

[69] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ላይ የተመለከተው ከገጽ 211-212።

ግዴታ እንዲወጣ የሚጠየቀው በውሉ የተመለከተው አደጋ ወይም ኃላፊነት ውሉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የደረሰ ከሆነ ብቻ ወይም ደግሞ ፖሊሲው መድን ገቢው እስከተወሰነ ቀን ድረስ በሕይወት ከኖረ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ከሆነ በዚያ በተባለው ቀን መድን ገቢው በሕይወት ኖሮ ከተገኘ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድ በን.ሕ.ቁ. 663/1/ ሥር በግልጽ እንደሠፈረው ሕጉም መድን ሰጪው በውሉ ለተመለከተው አደጋ መድን ለገባው ሰው መድን እንደሚሆን ሲደነግግ በዚሁ ሕግ በቁጥር 665/1/ ላይ ደግሞ በቁጥር 663/1/ ሥር ከተጠቀመበት ቋንቋ ሻል ባለ ሁኔታ "መድን ሰጪው በውሉ ውስጥ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ወይም በውሉ ውስጥ የተስማሙበት ቀን በደረሰ ጊዜ የተሰማውበትን ገንዘብ በውሉ በተወሰነ ቀን መክፈል ይገባዋል" ይላል።

ሕጉ መድን ሰጪው በፖሊሲው ላይ የተመለከተው አደጋ ሲደርስ ወይም ጊዜ ሲሞላ በውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ መክፈል አለበት ይበል እንጂ ሁል ጊዜም በውሉ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ወይም ጊዜ ከሞላ መካስ ወይም የተስማሙበትን ገንዘብ ለመድን ገቢው መክፈል አለበት ማለቱ ግን አይደለም። በን.ሕ.ቁ. 663/1/ እና 665/1/ ላይ የተቀመጡት ግዴታዎች የሚታዩት ከሌሎች የንግድ ሕግ ቁጥሮች ጋርና አዛኝ የሕግ አንቀጾችን ባልተቃረነ አኳኋን ተዋዋይ ወገኖች በተሰማሙበት መሠረት ሰለሆነ የን.ሕ.ቁ. 663/1/ እና 665/1/ በመድን ሰጪው ላይ የመጠየቅ ግዴታን ስለጣሉ ብቻ ይክሳል ማለት አይደለም።

ይህን በምሳሌ ለማስረዳት ብንሞክር ለአንድ መኖሪያ ቤት ለእሳት አደጋ መድን ተገብቶለት ኖሮ የመኖሪያ ቤቱ ከመድን ውሉ ምሥረታ በኋላ በእሳት አደጋ መውደሙ በማያከራክር ሁኔታ ቢረጋገጥ በአንድ በኩል የን.ሕ.ቁ. 663/1/ እና 665/1/ ሰብቻ ሲታዩ መድን ሰጪው ካሣ ለመክፈል መገደዱ ምንም የማያጠራጥር ሲሆን በሌላ በኩል ግን የደረሰው የቃጠሎ አደጋ መንስዔ በመድን ገቢው ሆን ተብሎ የተደረገ ጥፋት ምክንያት የመጣ ከሆነ ተቃራኒ ስምምነት እንኳን ቢኖር መድን ሰጪው በሃላፊነት እንደማይጠየቅ በን.ሕ.ቁ. 663/3/ ሥር ተመልክቶአል። በሌላ አነጋገር ምንም እንኳን በመድን ገቢው ላይ የደረሰው ጉዳት ተፈርቶ መድን በተገባለት አደጋ ቢሆንም መድን ገቢው የመድኑን ፖሊሲ ገንዘብ አገኛለሁ በሚል ቀቢፀ ተስፋ ተነሳስቶ ሆን ብሎና አስቦ መድን የተገባለት ጉዳት እንዲደርስ ቢያደርግ መድን ሰጪው የመካስ ግዴታው ይነሳለታል ማለት ሲሆን፣ ከሕይወት መድን አካያም ሲታይ መድን ገቢው ሆነ ብሎ ራሱን ቢገድል[70] ወይም ደግሞ አንድ የሕይወት መድን ተጠቃሚ መድን ገቢውን ሆን ብሎ ገድሎ ለዚህም በወንጀል ፍርድ ቤት ጥፋተኛነቱ ቢረጋገጥበት ውሉ ዋጋ እንደሌለው ሕጉ በግልጽ አስቀምጧል።[71]

---

[70] የን.ሕ.ቁ. 699

[71] የን.ሕ.ቁ. 700

የን.ሕ.ቁ. 663/3/ 699 እና 700 የሚያንፀባርቁት ሐሳብ "ex turpi causa non oritur actio" ከሚባል የላቲን አባባል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "no action can arise from a wrongful cause" ሆኖ በአማርኛ "ክስ የማቅረብ መብት ከወንጀል ድርጊት አይመነጭም" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ይህ ከዚህ በላይ የተነገረው የላቲን አባባል በተግባር ተፈጻሚ ሲሆን "ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆን የለበትም" በሚል የተወሰደ ሲሆን በእንግሊዝኛው "A man may not profit from his own wrong or crime" የሚል መርህ ሆኖ ይሠራበታል።[72] በሌላ አነጋገር የን.ሕ.ቁ. 663/3/፣ 699 እና 700 የፐብሊክ ፖሊስ ድንጋጌዎች ናቸው ለማለት ይቻላል።በዚህ ረገድ ጆን በርድስ እንዲህ ይላሉ። "... (He) (The insured) cannot recover if the loss was caused by his deliberate act. This may be simply the true construction of an insurance contract or it may alternatively be regarded as the application of public policy".[73]

ይሁን እንጂ በመድኑ ውል ፖሊሲ ውስጥ ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረ በስተቀር በን.ሕ.ቁ. 663/2/ መሠረት መድን የተገባለት አደጋ የደረሰው መድን በገባው ሰው ቸልተኝነት[74] ወይም ባልታሰበ አደጋ ከሆነ መድን ሰጪው በውሉ መሠረት የመካስ ግዴታ ይወድቅበታል። ከዚህ በላይ ለማመልከት እንደተሞከረው መድን ገቢው በገዛ ራሱ መሠሪ ድርጊት መድን የተገባለት አደጋ እንዲደርስ ቢያደርግ አይካስም ብሎ ሲል ሆን ብሎ ሳይሆን በመድን ገቢው ስሕተት ወይም ቸልተኝነት ለሚደርሰው አደጋ ግን መድን ሰጪው የመካስ ግዴታ እንደሚወድቅበት ሕጉ ደንግጐአል።[75] "ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረ" የሚለው በን.ሕ.ቁ. 663/2/ ሥር ሠፍሮ ያለው ሐረግ መድን ሰጪው በመድን ገቢው ቸልተኝነት ምክንያት የደረሰውን ጉዳት አልክሰም ብሎ በፖሊስዎች ውስጥ እንዲያስገባ ሰፊ ዕድል ሲሰጠው በመድን ገቢው ቸልተኝነት ለደረው ጉዳት አልጠየቅም የሚል የውል ቃል በፖሊሲዎች ላይ ከገባ ለመድን ሰጪው በኃላፊነት መጠየቅ የሚቀረው ጉዳት የደረሰው ባልታሰበ አደጋ "accident" ከሆነ ብቻ ነው። ይህ ማለትም የጉዳት ባልታሰበ አደጋ መድረስ ከቸልተኝነትም ሆን ተብለው ከሚደረጉትም ሁኔታዎች ውጪ መሆኑን ሲጠቁም "ባልታሰበ አደጋ" የሚለው ጉዳቱ የደረሰው ባልተጠበቀ

---

[72] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8፣ ገጽ 203።

[73] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8፣ ገጽ 203።

[74] አንድ መድን ገቢ ከአእምሮ ሕመም የተነሳ ወይም በቸልተኝነት ራሱን ቢገድል የመድን ውሉ ተጠቃሚ የፖሊሲውን ገንዘብ አያገኝም ለማለት አይቻልም። /የን.ሕ.ቁ.669/ ያንድ የሕይወት መድን ተጠቃሚም መድን ገቢውን ሆን ብሎ ሳይሆን በስሕተት ቢገድል የን.ሕ.ቁ. 700 ተፈጻሚ ሰለማይሆን የፖሊሲውን ገንዘብ ያገኛል።

[75] ምንም እንኳን በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1795 እና 1796 መሠረት ከውል ግንኙነት አኳያ የ "ጥፋት" ፅንሰ ሐሳብ ቢኖርም በዚሁ ሕግ ከውል ዉጪ ኃላፊነትን አስመልክቶ በቁጥር 2029 ላይ ጥፋት ሲባል ታስቦ በሚሠራ ወይም በቸልተኝነት በሚፈጸም ተግባር ሊደረግ እንደሚችል ተጽፎአል። ከወንጀል አኳያም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 57 ላይ እንደተመለከተው አንድ ሰው በወንጀል የሚጠየቀው ሆን ብሎ አስቦ ሲያጠፋ ወይም በቸልተኝነት ሲያጠፋ ብቻ ሲሆን ባልታሰበ ደጋ የሚፈፀም ሊያስቀጣ የሚችል ድርጊት በወንጀል እንደሚያስጠይቅም ተደንግጐአል።

ፍጹም ዳብዕዳ በሆነ ሁኔታ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በን.ሕ.ቁ. 663/2/ መሠረት "ባልታሰበ አደጋ" ለሚደርሱ ጉዳቶች መድን ሰጪው እንዳይጠየቅ በውል ግዴታውን ሊያስቀር እንደሚችል ተመልክቷል።

በን.ሕ.ቁ. 663/2/ ሥር "ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረ" የሚለው ሐረግ በቸልተኝነት ሽፋን ሰዎች ግዴለሽ ሆነው ለጉዳት መድረስ መንስዔ እንዳይሆኑ በውል ስምምነት ለመከላከል ካልሆነ በስተቀር ሚናው ባጠቃላይ በመድን ገቢው ቸልተኝነት የሚደርሱትን ጉዳቶች ከመድን ሰጪው ኃላፊነት ውጭ ለማድረግ ነው ተብሎ አይገመትም። ባልታሰበ አደጋ የሚደርሱትን ጉዳቶች በውል ከመድን ሰጪው ኃላፊነት ውጪ ማድረግም ጨርሶ መድንን ትርጉም የለሽ ወደ ማድረጉ ሰለሚያቀርበው መድን ሰጪው ይጠቀምበታል ብሎ መገመት አዳጋች ይሆናል።

መድን የተገባለት አደጋ የደረሰውና በዚሁ ምክንያት በመድን ገቢው ላይ ጉዳት ያስከተለው በራሱ መሠሪ ድርጊት ወይም በርሱ ቸልተኝነት ሲሆን ምን ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል በን.ሕ.ቁ. 663/2/ እና /3/ ላይ ሲደነገግ ራሱ መድን ገቢው ሳይሆን እርሱ ኃላፊ የሚሆንላቸው ሰዎች ባደረጉት ጥፋት ለሚደርስ ጉዳትም መድን ሰጪው በን.ሕ.ቁ. 664/1/ ሥር በተጻፈው መሠረት ኃላፊ ተደርጉአል።

እነኚህ መድን ገቢው ኃላፊ የሚሆንላቸው ሰዎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ በሕጉ ላይ በግልጽ የተመለከተ ነገር ባይኖርም ምናልባት በን.ሕ.ቁ. 683/3/ ሥር የተዘረዘሩት ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት አለ። የመድን ገቢዋ ባል ወይም የመድን ገቢው ሚስት በ.ን.ሕ.ቁ. 683/3/ ሥር ከተዘረዘሩት ሰዎች ውስጥ ሊደመር ወይም ልትደመር ስትችል በሌላ በኩል ግን ሚስትን ከመድን ገቢ ባል ወይም ባልን ከመድን ገቢዋ ሚስት ምን ለያት ወይም ለየው? በሚል ስሜት ተትቷል ወይም ተትታለች ብሎ ለማለት ይቻል ይሆናል።

- በን.ሕ.ቁ. 664/1/ ሥር መድን ገቢው ኃላፊ የሚሆንላቸው የተባሉት ሰዎች በፍ.ብ.ሕ.ቁ 2124 እና ተከታታዮቹ ሥር የተመለከቱት ሊሆኑ እንደሚችሉም ይገመታል። የመድን ሰጪው በን.ሕ.ቁ. 664 ተጠያቂ መሆን በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር የተመለከቱት ሰዎች ያደረጉት ጥፋት ዓይነትና ክብደት ሳይታይ ማለትም ጉዳት ያስከተለውን ጥፋት ያደረሱት ሆን ብለው ይሁን በቸልተኝነት እግምት ውስጥ ሳይገባ መድን ሰጪው ተጠያቂ ይሆናል። ሆኖም መድን ሰጪውን የመዳረግ መብት በተመለከተ የንግድ ሕጉ የሚለዉን ማጤኑ ጠቃሚ ይሆናል።[76]

[76] የን.ሕ.ቁ. 683/3/ን ይመልከቱ።

ሌላው ሁለቱን ተዋዋይ ወገኖች የሚመለከት ፀቢይ ጉዳይ የይርጋ ጉዳይ ነው። የይርጋን ጉዳይ ከመድን ሕግና ውል አኳያ ማየት ከመጀመራችን በፊት በፍትሕ ብሔር ሕግ የውል ጠቅላላ ሕጦች ክፍል ውስጥ ስለጉዳዩ በተጻፈው በቁጥር 1845 ብንጀምር "ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ውል እንዲፈጸም ወይም ካለመፈጸሙ የተነሣ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአሥር ዓመት ይርጋ" ይቀራል" ይላል። ምንም እንኳን ማንኛውንም ውል በተመለከተ የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 ተፈጻሚ ሊሆን ቢችልም በዚሁ ቁጥር "ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ" የሚለው ሐረግ አልፎ አልፎ ሕግ የሚያስቀምጠው አጠር ያለ ወይም ረዘም ያለ የይርጋ ዘመን ካለ ይኸው የተጠበቀ መሆኑን ለማመልከት ነው። በሌላ አነጋገር ልዩ ልዩ ሕጦች በተለይም ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሕግ አምስተኛ መጽሐፍ፣ በንግድ ሕግና በባሕር ሕግ ውስጥ ባሉት ልዩ ውሎች ውስጥ ሕግ ስለይርጋ በሌላ አኳኋን ወስኖ ቢገኝ በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 እና 1676/2/ መሠረት በልዩነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ማለት ነው።

በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 ሥር ከተደነገገው የይርጋ ዘመን ለየት ያለ ውሣኔ ከተሰጠባቸው ግንኙነቶች መካከል አንዱ ከመድን ውል[77] በሚመነጩ መብቶችና ግዴታዎች ላይ ሲሆን ሌሎችም በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 2143 ሥር ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከት እንዲሁም ከቼክ ጋር በተያያዘ ያለውን የይርጋ ዘመን በን.ሕ.ቁ.881 እና 882 ሥር የመለከቱት እንደምሣሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ከዚህ ጹሑፍ አኳያ ለማየት የሚፈለገው የመድን ውል ግንኙነት የሚፈጥራቸው መብትና ግዴታዎች በይርጋ የሚታገዱት እንዴት ነው የሚለውን ጥያቄ ስለሆነ ይህንኑ ከዚህ በታች ባጭሩ እንመለከታለን።

የመድንን ውል የሚመለከተው የይርጋ ሕግ የን.ሕ.ቁ. 674 የሚከተለዉን ይደነግጋል፦

> "በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የሚታገደው ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከተደረገበት ወይም በጉዳዩ ቅጥም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው"

የኢትዮጵያ የባሕር ሕግ ከንግድ ሕጉ ጋር ሲነጻፀር ስለ ይርጋ ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል። የባሕር ሕጉ የይርጋ ድንጋጌዎች ይርጋ የሚቋረጥባቸዉን ሁናቴዎች ጨምረዉ መያዛቸዉ አጽንኦት ሊሰጠዉ ይገባል። ከንግድ ህጉ በተለየና ግልጽ በሆነ ቋንቋ የኢትዮጵያ የባሕር ሕግ በቁ. 348 ላይ

---

[77] የን.ሕ.ቁ. 674

"ከኢንሹራንስ ዉል የሚመነጩ ክስ የማቅረብ መብቶች ሁሉ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳሉ" በማለት ይደነግጋል::[78]

የን.ሕ.ቁ. 674 ሌሎቹ ንዑስ ቁጥሮች የሚሉትን ወደጎላ ላይ ለማየት ትተናቸው በንዑስ ቁጥር /1/ ላይ ብናተኩር ሁለት ነጥቦችን እናያለን:: እነኚህም

1) ከመድን ውል በተነሣ የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የይርጋው ዘመን ሁለት ዓመት መሆኑ፣
2) ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው:-
   ሀ/ ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ወይም
   ለ/ በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ

መሆኑን ነው::

ከነኚህ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ሁለት ነጥቦች የሚያከራክር ሁኔታን የሚያስነሱት በሁለተኛው ነጥብ /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተነገሩትና የይርጋው ዘመን መቆጠር የሚጀምርባቸው ሁኔቴዎች ናቸው:: የአንድ መድን ገቢ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል ለማለት ምን ሲሆን ነዉ ቆጠራው የሚጀምረው "ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከደረሰበት" ነው የምንለዉ? ምን ሲሆን ቆጠራው የሚጀምረው በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ሰለአደጋው ካወቁበት ቀን ጀምሮ ነው የምንለዉ? ከዚህ በላይ በቁጥር 2 (ሀ) ላይ የተመለከተውን የይርጋው ዘመን መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ሕግ አውጪው ከራሱ ከመድን ገቢው አኳያ እንዲታይ ፈልጐ በ 2 (ለ) ላይ የተመለከተውን ደግሞ ከሌሎች በጉዳዩ ጥቅም ካላቸው ሰዎች ስለጉዳቱ ማወቅ አንፃር ብቻ እንዲታይ ፈልጐ ነው ለማለት ይቻል ይሆን?

የደረሰውን አደጋ /ጉዳት/ የማወቅ ጉዳይ ከሆነ መድን ገቢውም ቢሆን መድን የተገባለት አደጋ መድረሱን ካላወቀ በን.ሕ.ቁ. 670 ላይ ያለውን ግዴታውን እንኳን ሊወጣ አይችልም፣ የካሣ ጥያቄም ማቅረብ አይችልም:: ምናልባት ሕግ አውጪው ከዚህ በላይ በቁጥር 2 (ሀ) እና (ለ) ላይ ያስቀመጣቸው ሁለት የተለያዩ የሁለት ዓመት ይርጋ መቆጠር የሚጀምርባቸው ሁኔታዎችን ያሠፈረው ከ "ሀ" አንፃር የመድን ገቢው የአደጋን መድረስ ማወቅ ምንም መጠራጠር አያሰፈልግም /it should be taken for granted/ ከሚል የተነሳ ነው ሊባል ይችል ይሆናል:: ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ መቶ በመቶ ትክክል ነው ለማለት አያሰደፍርም:: ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁለተኛው ነጥብ "ለ" ላይ "በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ጀምሮ" የተሰኘው ምናልባት እነኚህ በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ሰዎች ሰለአደጋው ቆይተው ሊያውቁ ስለሚችሉ[79] መብታቸዉን ላለማጥበበ ይርጋው

---

[78] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት <u>የባሕር ሕግ</u> ፣ነጋሪት ጋዜጣ ቁ. ፩፣በ1952 ዓ.ም. በተሰይ የወጣ፣ አዲስ አበባ::

[79]ከመድን ውሉ ጋር በተያያዘ ጥቅም ያላቸው 3ኛ ወገኖች ያደጋውን መድረስ ሳያውቁ ሊቆዩ ይችላሉ:: በመሆኑም የነርሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል ሕግ አውጪው እነኚህን በተመለከተ የሁለቱ ዓመት ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው እነርሱ ያደጋውን መድረስ ካወቁበት እንጂ አደጋው ከደረሰበት ቀን አለመሆኑን ደንግጓል::

መቆጠር የሚጀምረው አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን እነርሱ ካወቁበት ቀን ጀምሮ ነው ብሎ ለማለት ፈልጎ ይሆናል ሕግ አውጪው መቼም በ "ለ" ላይ ያለውን ሁኔታ አስረድቶ በይርጋ ምክንያት ክሱ ይታገዳል ለማለኘት መድን ሰጪው ያለበትን ፍዳ መገመቱ ክባድ አይደለም፣ በተቃራኒዉ አደጋ የደረሰበትን ቀን ማስረዳቱ ቀላል ነው።

ሌላው በን.ሕ.ቁ. 674/1/ሥር አከራካሪ ሊሆን የሚችለው ነጥብ "ጉዳት" ለሚለው ቴክኒካዊ ቃል የሚሰጠው ትርጉም ነው። ከዚህም አኳያ ለመሆኑ "ጉዳት" የተባለው ቃል መድን ሰጪው በመድን ገቢው ላይ ለአረቦን ክፍያ የሚያቀርበውን ክስ በን.ሕ.ቁ. 674/1/ ሥር ከተመለከተው የይርጋ ዘመን ውጪ ያደርገው ይሆን? ሌሎችስ "ጉዳትን" የማይመለከቱትን መድኖች ይጠቀልል ይሆን? የሚሉትን ጥያቄዎች ሊያስከትል ይችላል። በአንድ በኩል የን.ሕ.ቁ. 674/1/ የእንግሊዝኛ ቅጂ "From the occurrence giving rise to the claim" ሲል አባባሉ ምናልባት ሰፋ ያለና ማንኛውም ከመድን ውል የሚነሣ ክስ ወደማለት ይወስዳል ሊባል ሲችል በሌላ በኩል "occurrence" የሚለው ቃል ዞሮ ዞሮ የአደጋን መድረስ /materialization of the risk insured/ የሚያመለክት በመሆኑ የእንግሊዝኛውም ቅጂ "ጉዳት" የሚለውን ቃል ከተጠቀመው ከአማርኛው ቅጂ አልራቀም ለማለት ይቻላል። የሆነ ሆኖ "occurrence" "ጉዳት" ከሚለው ቃል ሰፋ ማለቱ ብዙም አያከራክርም።

በን.ሕ.ቁ. 674/1/ "ጉዳት" የሚለው ቃል ከተወሰደ ለተወሰነ ጊዜ በሕይወት ኖሬ ከተገኘሁ ይህን ያህል ትከፍለኛለህ የሚል ስምምነት የሚደረግበትን የሕይወት መድን ዘርፍ እንደማይጨምር መከራከር ይቻላል። ከሁሉም ይበልጥ ግን መድን ሰጪው የተወዘፈ አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ በአንድ ወሩ የፋታ ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለው የሚያቀርበው ክስ በን.ሕ.ቁ. 674/1/ ይርጋ ይታገዳል? አይታገድም? የሚለው ጥያቄ ጉዳት ከሚለው ቃል አኳያ እንዴት ይታያል የሚል አከራካሪ ጥያቄ ያስነሳል።

የመድን ሰጪው ውዝፍ አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ ያለማግኘት እንደ "ጉዳት" ሊታይ ይችል ይሆን? በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት (is it an occurrence?) ተብሎ ሲጠየቅ "ጉዳት" የሚለው ያማርኛ ቃልና "Occurrence" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በጠባቡ ከተወሰዱ መልሱ አሉታዊ ሲሆን በሰፊው ከተወሰዱ ግን መልሱ አዎንታዊ ሊሆን ይችላል።

በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 አባባል ከተሄደ የመድን ሰጪው ውዝፍ አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያለማግኘት እንደ "ጉዳት" የማይታይበት ምንም ምክንያት የለም። በዚህ ረገድ "ጉዳት" የሚለው ቃል "occurrence" ወይም risk materialization ን የሚመለከት ሳይሆን "damage" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል

ስሜት ይዞ ነው።[80] በመሆኑም ወይ አረቦኑ መክፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ [81] በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መድን ሰጪው ክስ ካላቀረበ ይርጋ ያግድበታል ወይም ደግሞ በን.ሕ.ቁ. 663/3/ የተጻፈውን ከግምት ውስጥ በማስገባት አረቦን ከማስከፈል አንፃር ይርጋ መቆጠር መጀመር ያለበት የአንድ ወሩ የፋታ ጊዜ ካለቀ ጀምሮ መሆን አለበት ብሎ መከራከር የሚቻል ይመስላል።

በንግድ ህጉ ሊያከራክር እንደሚችል የተጠቆመዉ አረቦንን ስለሚመለከተዉ ይርጋ በባሕር ሕጉ በግልጽ ተቀምጧል። ቢያንስ ቢያንስ የባሕር ሕጉ የይርጋ ዘመኑ ከመቼ ጀምሮ መቆጠር እንዳለበት በመደንገግ ከንግድ ሕጉ ተሸሏል። በባሕር ሕጉ በቁ. 349 ላይ አረቦን ለማስከፈል የይርጋ ዘመን በዚሁ ህግ በቁ. 348 ሥር በተደነገገዉ እንደሚመራ ታሳቢ በማድረግ ይልቁንም አከራካሪ ሊሆን የሚችለዉንና አረቦንን ከማስከፈል አኳያ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረዉ ከመቼ ጀምሮ ነዉ? የሚለዉን ጥያቄ ይመልሳል።
የባሕር ሕጉ ይህን አከራካሪ ነጥብ በሚመለከት እንደሚከተለዉ ደንግጓል፦

> የኢንሹራንስ ገንዘብ (ፕሪሚየም) አከፋፈልን የሚመለከተዉ የክስ ማቅረብ መብት ይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረዉ የዉሉ ስምምነት ተቀባይነት ካገኘበት ቀን አንስቶ ነዉ።[82]

የማንኛውም ከመድን ውል በተነሣ ለፍርድ ቤትም ሆነ ለግልግል ዳኝነት መድረክ የሚቀርብ ክስ ከይርጋ አንፃር በ.ን.ሕ.ቁ. 674 መገዛት አለበት የሚለው ጠንካራ ክርክር መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል።

በን.ሕ.ቁ. 674/2/ ሥር ወደተጻፈው ስንመለስ የተሸሸገ ወይም በሐሰት የተሰጠ መግለጫ ካጋጠመ የሁለት ዓመቱ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው መድን ሰጪው ይህን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነው ይላል። በዚህ ንዑስ ቁጥር ሥር ያለው የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምርበት ሁኔታ ቀደም ብለን ባየነው የን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ሀ/ ሥር ከተጻፈው ጋር አብሮ መታየት ያለበት ይመስላል። በነገራችን ላይ የን.ሕ.ቁ. 674/2/ ተፈጻሚነቱ በመድን ሰጪው ላይ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ነው ሕጉ ያስቀመጠው። ነገር ግን ከመድን ውል ረገድ ተፈጻሚነቱ በሁለቱም

---

[80] ጉዳት ወይም በእንግሊዝኛው "damage" የሚለው ቃል በሰው ወይም በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚያመለክት ሲሆን ከሕግ አኳያ ትርጉሙ ግን ሰፋ ብሎ የገንዘብ ኪሣራንም የሚጨምር ስለሆነ ሊከፈለው ይገባ የነበረው አረቦን ሳይከፈለው ያደጋውን ሃላፊነት ላጭር ጊዜም ቢሆን የተሸከመው መድን ሰጪ አረቦኑን ባለማግኘቱ ኪሣራ (damage) ደርሶብኛል በማለት ሊጠይቅ ይችላል።

[81] አረቦን ሲል እዚህ ጋር የማሳደሻ ወይም የማስቀጠያ አረቦንን የሚመለከት ይመስላል። ስለሆነም ይርጋው መቆጠር የሚጀመረው ማሳደሻው ወይም ማስቀጠያው አረቦን ሊከፈል ይገባ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ነው ብሎ ማሰብ ይቻል ይሆናል። ነገር ግን ይህ ከን.ሕ.ቁ. 666/3/ አኳያ ሲታይ ብዙም ጠንካራ ክርክር አይመስልም።

[82] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት <u>የባሕር ሕግ</u> ፣ነጋሪት ጋዜጣ ቁ. ፩፣በ1952 ዓ.ም. በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ ቁ 349።

ተዋዋይ ወገኖች ላይ ነው::[83] በኢትዮጵያ የመድን ሕግ ውስጥ በግልጽ ባይቀመጥም የፍጹም ቅን ልቡና ጉዳይ በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ መሆኑን የሚጠቁሙ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አሉ::[84]

ከመድን ውል አንፃር የይርጋን ጉዳይ ከማጠቃለላችን በፊት በን.ሕ.ቁ. 674 የተመለከተው የይርጋ ዘመን በምን በምን ምክንያቶች እንደሚቋረጥ በንግድ ሕጉ ላይ የተባለ ነገር እንደሌለ መገንዘብ ያሻል:: የንግድ ሕጉ ከዚህ አኳያ ዝም ከማለቱ የተነሳ የካሣ ጥያቄውን ለመድን ሰጪው ያቀረበ አንድ መድን ገቢ መድን ሰጪው የካሣ ጥያቄውን ተቀብዬለሁ አልተቀበልኩም ብሎ ለማስታወቅ ቢዘገይም ይህ መዘግየት የይርጋ መቆጠሩን ያቋርጣል ካልተባለ በስተቀር የግድ በ.ን.ሕ.ቁ. 674/1/ መሠረት የሁለት ዓመቱ ጊዜ ከማለፉ በፊት መክሰስ እንደሚኖርበት እንረዳለን:: ይሁን እንጂ ደግሞ ሳቀረበው የካሣ ጥያቄ ከመድን ሰጪው የእምቢታም ይሆን የእሺታ መልስ ሳይገኝ ክስ ለማቅረብ መድን ገቢው በጣም እንደሚቸገር መገመቱ ቀላል ነው::

ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ በንግድ ሕጋችን ውስጥ የሚታዩትን መድንን የሚመለከቱአንዳንድ አከራካሪ ነጥቦችን ለመጠቆም ሙከራ ተደርጓል:: ከመድን ግንኙነት የተነሣ የሚከሰቱ ችግሮች ግን ሙሉ በሙሉ የተከሰቱት ወይም የሚከሰቱት ከሕጉ ድክመት የተነሣ ብቻ ባለመሆኑ ሌሎች ከግምት ውስጥ መግባት ስላለባቸው ችግሮች መጠቆሙ ወደፊት መፍትሔ ከመሻቱ ረገድ ጠቃሚና አስፈላጊ ይሆናል:: በዚሁ ስሜት አንዳንዶቹን ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል::

- በመሠረቱ የመድን ውል እኩል ባልሆኑና እኩል ናቸው ተብለው በማይገመቱ ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል ነዉ፣
- ከተዋዋይ ወገኖች እኩል ያለመሆን በተጨማሪ ደግሞ የመድን ውል በአንድ ወገን ማለትም በመድን ሰጪው የሚዘጋጅ በመሆኑና adhesive contracts ከሚባሉት ውሎች እንደ አንዱና ዋነኛው የሚቆጠር ነዉ፣
- ባንድ ወገን የሚዘጋጅን ውል አዘጋጁ ወገን ለራሱ በሚያመች ሁኔታ የሚያዘጋጀው ነዉ፣
- ቀደም ሲል በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ እንደተገለጸዉ በሀገራችን ውስጥ ያሉ መድን ሰጪዎች የሚጠቀሙባቸው የመድን ውሎች የተወሰዱት የኮመን ሎው የሕግ ሲስተም ከሚከተሉት አገሮች በተለይ ደግሞ ከእንግሊዝ አገር

---

[83] የመድን ውል የፍጹም ቅን ልቡና ውልነት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተፈፃሚነቱ በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ማለት በመድን ሰጪውና በመድን ገቢው ላይ ነው:: ምናልባት የ.ን.ሕ. ቁ. 674/2/ ከመድን ሰጪው አንፃር ብቻ እንደሚያገለግል ተደርጉ የተፃፈው ብዙም መድን ገቢው የሚጠቀምበት ስላልሆነና ባብዛኛው አታሎኛል ውሉ ፍርስ ነው ይባልልኝ ወይም ጨርሶ ያልተገለፀ ወይም በትክክል ያልተገለፀ ማቴሪያል ፋክት አሰና ውሉ ይፍረስልኝ ብሎ ጥያቄ የሚያቀርበው መድን ሰጪው ስለሆነ ይሆናል::

[84] ለምሣሌ የን.ሕ.ቁ. 680 በተለይም ንዑስ ቁጥር /1/ን ይመልከቱ::

መሆኑንና በአንዳንዱ የመድን ሕጋችን የተወሰደው ባብዛኛው የሲቪል ሎው ሲስተም ከሚከተሉት አገሮች በመሆኑ በሕጉና መድን ሰጪዎቹ በሚጠቀምባቸው ፖሊስዎች መካከል ያለመጣጣም አለ፣

- ስጊዜው ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በሥራ ላይ ካለው የሕይወት መድን ፖሊሲ በስተቀር ሌሎች ፖሊሲዎች የተዘጋጁት በእንግሊዝኛ ቋንቋ በመሆኑና በፖሊሲዎች ውስጥ ሰፍረው የምናገኛቸው ቴክኒካዊ ቃላትና ፅንሰ ሐሳቦች እንኳንስ ላልተማረ ለተማረ መድን ተቀባይ እንኳን በቀላሉ የማይገቡ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች ችግሮችን ለመቅረፍ የመድን ሰጪዎቹ የራሳቸዉ ሚና ቀላል እንደማይሆን ቢገመትም የመድንን ሥራ የሚቆጣጠረው መንግስታዊ አካልም ብዙ ይጠበቅበታል። ከዚህ በላይ ከተጠቀሙት ችግሮች አኳያ ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት ፍርድ ቤቶች መሆናቸዉን በተለይም ገዢ ሊሆኑ የሚችሉትን ዉሳኔዎች የሚሰጠዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ነዉ። ጉልቶ የሚታየውም ከመድን ውሎች አተረጓጎም አንፃር ሆኖ ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን አስተዳደራዊ ቁጥጥር በተጨማሪ በመድን ሥራ ዘርፍ ከፍተኛ የዳኝነት ቁጥጥር አስፈላጊ መሆኑ አከራካሪ አይደለም።

Timely Disposition of Criminal Cases in Ethiopia

Tsehai Wada*

Introduction

Timely disposition [85] of criminal cases is a concept close to the hearts of those who have come into conflict with the law[86]. As the old adage goes, justice delayed is justice denied. Timely disposition of cases, alias, the right to a speedy trial, though mainly discussed in light of a person who is accused of committing a crime, equally applies to litigants in civil cases. The main concern behind is litigating stale cases which may adversely affect the rights of parties in a dispute. If a legal case takes too much time to be disposed, one of the parties will be disadvantaged, for witnesses may die or disappear, physical evidences may deteriorate or get damaged partially or totally -and memory may fade. In criminal cases in particular, primarily, it is the accused that is denied the right, for unlike the prosecutor he does not have the freedom as well as the resource to collect evidences that may be submitted to court. The denial of the right to a speedy trial leaves the door open for the prosecution to dictate the length of a trial and will ultimately lead to unwarranted pretrial detention and abuse of prosecutorial power. Moreover it was explained that: [87]

> excessive delays in the administration of justice constitute an important danger, in particular for the respect of the rule of law...Celerity of proceedings responds to the need for legal

---

* Associate Professor, School of Law, Addis Ababa University.

[85] The term "Timely disposition" is no different from the well known term "speedy trial". This writer has, however, opted to use the former term, just for the sake of obviating the usual controversy that the latter refers to a person's right at trial only and does not cover any pretrial processes. It will be made clear hereunder that the right attaches to every process of the criminal justice system, starting from arrest or charging and ends at the end of trial.

[86] American Bar Association, Criminal Justice Standards on Speedy Trial, Sec. 12-1.1 a (2). Available at www.abanet.org. Moreover, the stakeholders of speedy trial or timely resolution of criminal cases are: an accused as well as the public, victims and witnesses. This is not to suggest that civil cases do not need celerity too. The European Convention for Human Rights for one, provides that "In the determination of his civil rights and obligations or of any criminal charge against him, everyone is entitled to a fair and public hearing within a reasonable time by an independent and impartial tribunal established by law" – Art.6 Sec.1. The scope of this article is, however, limited to the criminal aspect only.

[87] Venice Commission, Can Excessive Length of Proceedings be Remedied? Science and Technique of Democracy No.44, Council of Europe Publishing, (2007), pp. 15, 16.

> certainty, for both citizens and the state, and to the need to further, and restore as soon as possible, the peaceful coexistence of individuals...Indeed the economic life too suffers from contested situations which remain unsettled for too long. Long lasting disputes disturb such peaceful coexistence; judicial proceedings may not be pursued ad infinitum, not even when this prolongation may eventually lead to substantive justice. Decisions must at some foreseeable point become final.
>
> [Delayed justice] risks to affect the confidence which the general public places in the capacity of the State to dispense justice, to decide disputes, and very importantly, to punish crimes as well as to prevent and deter future crimes. This may cause or even incite the recourse by individuals to alternative means of dispute settlement or dispensation of punishment...

Since criminal cases are processed at public expense, any mechanism that can shorten the time required to process a criminal case also saves public spending. It should be noted that both a defendant and the society have interest in the implementation of the right to a speedy trial and that their interests are not conflicting. The defendant's interests are *inter alia*: reduction of anxiety and concern accompanying public accusation; interference with the right to liberty; disruption of employment; subjection to public obloquy; and avoiding undue and oppressive pretrial incarceration. The societal interests include effective prosecution of criminal cases without advantaging the prosecutor; penalizing official abuse of the criminal process and discouraging official lawlessness; preventing an accused who is not incarcerated from committing additional criminal acts while awaiting trial;[88] and reducing cost of pretrial incarceration for defendants who may ultimately be acquitted.[89]

---

[88] In the US, approximately three quarters of all defendants are released pending trial and a substantial percentage of crimes are committed by prior offenders. See, Mark L. Steinberg, Dismissal with or without Prejudice under the Speedy Trial Act: A Proposed Interpretation, The Journal of Criminal Law and Criminology, Vol.68, No.1, (1977).pp.10-12.

[89] Brian P. Brooks, A New Speedy Trial Standard for Barker v Wingo: Reviving a Constitutional Remedy in an Age of Statute, The University of Chicago Law Review, Vol. 61, No.2, (Spring 1994), p.587.

Despite this stark truth, the judicial process in many countries is slow, so much so that cases take years to be disposed to the disadvantage of everyone. One may mention so many reasons for such a slow process, but it suffices to mention just a few of them for the purpose of this article. The major causes of delay are, among others, caseloads at the different agencies of the criminal justice system, i.e. police, prosecution offices, and courts; unavailability of witnesses for whatever reason, flight of suspects with the intention to avoid arrest, pretrial motions and absence of a specific legal requirement that a case should be disposed within a given time as well as remedies when the legally fixed date expires.

The topic under discussion is an issue of universal concern, and a cursory look at the literatures that emanate from different jurisdictions[90] show that many countries have adopted different measures to lessen the effects of delayed justice, if not to do away with it *in toto*. Accordingly, some jurisdictions mandatorily require that there should be specific time limits to process a case at the different agencies and the sanction for failure to observe these limits may be, to dismiss the case with or without prejudice. A closely related solution to delayed justice is statute of limitation which will bring a definite end to such stale cases.

The right to a speedy trial is a constitutional right in Ethiopia. Moreover, subsidiary laws provide for some mechanisms to implement this right, though not to the expected level. Despite this, the right to a speedy trial is honored - in practice - more in the breach than in the observance. This article attempts to examine the state of the right in Ethiopia, compare and contrast the law with the practice and suggest some recommendations that may help ease the problem. With this in mind, the article is divided into three parts. The first part discusses the genesis and historical development of the right in the common law jurisdictions. The second section discusses the measures adopted by different countries with a view to lessen the effects of delayed justice. The third part deals with the position of Ethiopian laws on the right to a speedy trial to be followed by an overview of the practice. The article will end with conclusion and a few recommendations.

---

[90] Most of the materials accessible to this writer deal with the laws and practices of the US. Thus, the term 'jurisdictions' refers to, mainly this country. It should, however, be mentioned here, that the Venice Commission's report on the subject, Supra, Note 3, has canvassed all EU members and one can easily glean from the report that European nations have developed mechanisms which are similar to the US laws. www.legislationonine.org, which is a website with rich data on European laws, also evinces the same fact.

1. Origin and development of the right to a speedy trial

In the common law jurisdictions, writers trace the origin of the right to a speedy trial back to the 12th Century: [91]

> The right to a speedy trial is an ancient liberty. During the reign of Henry II (1154-1189), the English Crown promulgated the Assize of Clarendon, a legal code comprised of twenty-two articles, one of which promised speedy justice to all litigants[92]. In 1215 the Magna Charta prohibited the king from delaying justice to any person in the realm.

The pertinent part of the latter reads, *"To no one will we sell, to no one deny or delay the right of justice"*. As a follow up to this development, the English Parliament passed the Habeas Corpus Act in 1679. The Act required that persons accused of treason or a felony be released on bail if not indicted at the next term, unless the King's witness could not be produced, and further provided for complete discharge for those not indicted and tried by the next term.[93] In the US, the first colonial right was set forth in the Virginia Declaration of Rights of 1776, which was also the first colonial bill of rights.[94] The founding fathers intended the Speedy Trial Clause to serve two purposes: first, to prevent defendants from languishing in jail for an indefinite period before trial and ...second, to ensure a defendant's right to a fair trial. This is because the longer the commencement of trial is postponed, it is more likely that witnesses will disappear, memories will fade, and evidence will be lost or destroyed.[95] Thus, the right to a speedy

---

[91] Speedy Trial Encyclopedia, at www/lawencyclopedia.com. Accessed on July1, 2009

[92] The English Assize of Clarendon was enacted in 1166. See, Ostfeld, Greg, Speedy Justice and Timeless Delays: The Validity of Open ended "ends of justice" Continuance under the Speedy Trial Act, University_of Chicago Law Review, Vol.64, No.4 (summer, 1977), p.1057

[93] F.D.L. Jr., The Lagging Right to a Speedy Trial, Virginia Law Review, Vol.51, No.8, (Dec.1965), p.1595. It should also be noted that a number of American states, responding to the unfortunate effects of pretrial imprisonment, have patterned their statutes after parts of the English Habeas Corpus Act, .Ibid. at 1594 and 1595.

[94] Ostfeld, Supra, Note 7, at 1057.

[95] Speedy Trial Encyclopedia, Supra, Note 8 at 1594 and 1595.

trial is made a constitutional right under the Sixth Amendment, which states that, "in all criminal cases the accused shall enjoy the right to ...a speedy trial". Although this right is derived from the federal constitution, it has been made applicable to state criminal proceedings through the US Supreme Court's interpretation of the Due Process and Equal Protection of the Fourteenth Amendment [clauses].[96] Despite this clear constitutional guarantee, the US Supreme Court could not come up with a definite time limit within which a delay can be considered permissible or impermissible. What could be determined before 1974 was to make use of the "balancing test" in which the length of the delay is just one factor to be considered when evaluating the merits of a speedy trial claim.

Since the different mechanisms designed by the US Supreme Court's interpretation of the standards could not bring about the desired effects of reducing the backlogs of court cases, and lengthy pretrial delays, Congress enacted the Speedy Trial Act (18 U.S.C.A. Sec.3161 et. seq.) in 1974. This Act requires *inter alia*: that an information or indictment shall be filed within thirty days of a defendant's arrest; a prosecutor who knows an accused is incarcerated at the time of the indictment must take immediate steps to initiate prosecution; if a defendant enters a plea of not guilty, trial must commence within seventy days from the filing of the information or indictment, or seventy days from the accused's first appearance in court, whichever is later[97]. The Act thus, introduced definite time limits within which a criminal case may be dismissed with or without prejudice. Moreover, it provided nine specific exclusions to the time limits. Eight of the exclusions are specifically targeted at common sources of delay such as pretrial motions and joining of new codefendants...while the ninth confers discretion upon judges to grant a continuance when necessary to serve the "ends of justice".[98]

---

[96] Id.

[97] See generally, Speedy Trial Encyclopedia, and Ostfed, Supra, Notes 8 and 7 respectively.

[98] Osterfed, Supra, Note 7, at P.1037, 1039. The list of exclusions that exempt specific types of delay from the statute's time limit computations [are]: delay resulting from proceedings or examinations to determine the mental competency or physical capacity of the defendant; trial on other charges; interlocutory appeal; pretrial motions; transport of defendant from another district or to and from places of examination or hospitalization; consideration of proposed plea agreement; and unavailability of an essential witness.

The time limits as well as the sanctions have generated a number of issues with which the US courts are still grappling with and there appears to be a wide divergence in interpretation. This is so because in the words of one writer, 'the right is so amorphous, slippery and generally difficult to vindicate, [as a result of which] courts have not applied consistent legal standards in [such] cases'.[99] Notwithstanding the absence of a consensus, the practice evinces that some standards have developed to tackle the issue. The major ones are discussed below, *albeit* very briefly.

2. Major standards against which the right to a speedy trial should be measured and sanctions when legally set time limits are not observed.

2.1. The Barker test[100] – This test requires that courts should balance four factors, namely, the length of the delay, the reason for the delay, [the time] when the defendant asserted his right to speedy trial, and the prejudice suffered by the defendant as a result of the delay. A very brief explanation of each follows.

- Providing affordable and a speedy system of dispute resolution;
- Providing ADR services by making available a wide range of expertise to resolve commercial and non-commercial disputes;
- Providing professional ADR training for those who wish to qualify as arbitrators and mediators;

* Project Coordinator, the Ethiopian Arbitration and Conciliation Center, Addis Ababa, Ethiopia.

- Organizing and providing facilities for arbitrators, mediators and conciliators;
- Conducting research on ADR and disseminating the findings with the objective of introducing to the public the benefits of using ADR services; and
- Working together with the government in order to introduce new laws on ADR and to create better awareness on ADR.

The following sections explain the practical steps taken by the EACC in order to achieve its objectives enumerated above.

1. The provision of ADR services

1.1. ADR services at the EACC's head office

The EACC has actually provided cost effective ADR services that are speedy and conducted within a non adversarial atmosphere. The EACC provided mediation and arbitration services at its head office in Addis Ababa. Specifically the EACC has provided ADR services in relation to trade disputes, labor disputes, construction disputes and family disputes. The EACC employed voluntary arbitrators and mediators who bave been trained by the EACC and who are willing to provide free arbitration and mediation services at the EACC's head office. The EACC also has a roster of trained ADR professionals. The names, details and qualifications of these professionals is recorded in the roster and regularly updated. This roster is available not only for the EACC but also can be accessed by others who want to contact the mediators and arbitrators.

1.2. ADR services in sub-cities and kebeles in Addis Ababa

The EACC has now set up ADR centers in three sub cities. Prior to setting up sub city offices, EACC was providing ADR services from twelve kebeles across Addis Ababa. The Kebele services have now been phased out and replaced with the sub city offices.

1.3. Regional ADR services

The EACC has set up branch offices in seven regions and had been providing free ADR services using the expertise of those who it had trained as mediators and arbitrators. So far the EACC has set up ADR offices in Mekelle, Dire Dawa, Bahir Dar, Hawassa, Arba Minch, Adama and Harrar. The EACC has built its own ADR center at Arba Minch while it is in the process of building another one in Bahir Dar. The regional offices were set

up in cooperation with the respective regional Justice Bureaus, the regional City Councils and local kebeles. The regional offices are run by full time coordinators recruited by the EACC. The EACC has also provided training on ADR skills in the regions to, *inter alia*, community and religious elders, social court judges and professionals.

1.4. Court annexed mediation service

The EACC had been providing court annexed mediation service in Addis Ababa. The EACC provided mediation service for cases sent to it by the Civil Division of the Federal High Court on the basis of the agreement concluded between the Federal Supreme Court and the EACC. Moreover, the EACC entered into an agreement with the Federal First Instance Family Court to provide mediation service for cases that are referred to it by the latter.

1.5. Roster of ADR professionals

The EACC has compiled a roster of trained ADR experts which is regularly updated. The EACC refers to the roster when selecting suitable mediators and arbitrators to resolve disputes. The roster is an exhaustive list of ADR experts trained by EACC which is also accessible by all those who need information on mediators and arbitrators for different kinds of disputes.

2. Research and Law Reform

2.1. Draft Law

In its attempts to bring about law reform on ADR, the EACC commissioned a research with a view of proposing appropriate legislation on ADR in Ethiopia. In order to facilitate the process, the EACC organized and held two brain storming workshops. A number of professionals including members of parliament, prominent lawyers and university professors took part in these brainstorming workshops. The discussions during the workshops contributed towards the development of a draft law on ADR in Ethiopia.

The draft law was also sent overseas for consultations to an EACC's partner organization, STITT Feld Handy Group, an ADR Chamber in Canada. The draft law was eventually presented to the Ministry of Justice. The EACC hopes that the draft law will be adopted by the Parliament.

2.2. Rules of Arbitration and Mediation

The EACC hired the services of professional lawyers who are well versed in the area of ADR to prepare the 'Rules of Arbitration and Mediation'. The rules are meant to be used by mediators and arbitrators in resolving disputes at the EACC. Among other things, the rules provide guidance on the appointment of mediators and arbitrators, explain the roles of mediators and arbitrators in resolving disputes, and set out procedural matters.

2.3. Research on disputes resolved through ADR mechanisms

The EACC conducts research on disputes that have been resolved through ADR mechanisms. The EACC editorial team meets regularly to collect and edit cases resolved through ADR services of the EACC. The outcome of the research is published through on EACC journals of arbitral awards

3. Public Education

3.1. Training

A. Training on ADR mechanisms

In order to make ADR widely available, the EACC from time to time provides training on mediation and arbitration skills to individuals drawn from various sections of the society. Initially, the EACC training targeted various professionals including practicing lawyers, employees of the Ministry of Labor and Social Affairs, employees of Ethiopian Women Lawyers Association. members of the Confederation of Ethiopian Trade Unions, members of the Civil Engineers Association, members of Consulting Engineers and Architects Association and members of the Employers Federation.

Subsequently the EACC provided training on ADR to university students, law enforcement officers, judges, lawyers, prosecutors, and HIV desk representatives working in various kebeles. The EACC has also trained individuals from various areas in Addis Ababa including those involved in traditional dispute resolution such as religious leaders and community elders. In addition, EACC has trained numerous social court judges and registrars. Moreover, the EACC has trained persons drawn from various sections of the society in the regions. The EACC employs some of the trainees as ADR experts in its centers in Addis Ababa and the regions. The training is conducted by local and foreign ADR experts, and members of EACC's international partners.

B. Training of trainers course

The EACC conducts 'training of trainers' courses. The first such training was provided in March 2007 and targeted 30 trainees while in January 2009, the EACC held another similar training for 52 professionals. These trainings are designed to equip those who had already completed the training on ADR mechanisms with the capacity and skills to provide training on ADR mechanisms.

3.2. Awareness creation workshops

As part of its public education program, EACC organized and held a number of workshops in order to promote the notion of ADR. The workshops had different themes including the importance of ADR mechanisms, the strategy to be employed for a better application of ADR services, the role of lawyers and other professionals and institutions in promoting and providing ADR services and the relationship between customary methods of dispute resolution and modern ADR mechanisms. The participants of the workshops included academics, public officials, professionals, and religious and community leaders.

3.3. Publications

A. Journal

The EACC publishes journals on arbitral awards. The journals contain a number reports on selected cases resolved through ADR mechanisms. Each report contains:

- A short and precise list of all the legal questions raised in the case
- A brief summary of the plaintiff's pleading
- A brief summary of the respondent's reply
- A declaration as to which party prevailed
- The issues that the arbitrators raised
- Details of the arbitration proceedings
- The award passed by the arbitration panel
- The decree passed by the arbitration panel
- Dissenting opinion of an arbitrator, if any
- Decision of an Appellate Court, if the arbitral award was appealed to an ordinary court.

B. Newsletters and Brochures

The EACC publishes a quarterly newsletter to publicize its activities and popularize ADR mechanisms. The newsletter is distributed free of charge. The EACC also prepares brochures that contain information about its services in a manner that is accessible to the public.

C. National Arbitration Moot Court Competition

The EACC organizes national moot court competition in partnership with other institutions. In 2009 the EACC organized the firs national moot court competition in partnership with the American Bar Association-Rule of Law Initiative, the WTO-Accession Plus and the School of Law of Addis Ababa University. Twenty seven students and their advisors drawn from Addis Ababa University, Mekelle University, Jimma University, Hawassa University, Gonder University, Haramaya University and Bahir Dar University took part in the competition. The students and their advisors were given training on ADR mechanisms ahead of the competition.

EACC is now organizing its second round of the national arbitration moot competition and has already given ADR training to those university students selected to take part in the competition.

D. ADR Clubs

The EACC sets up ADR clubs in order to create awareness on ADR and its benefits. For instance the EACC has succeeded in setting up ADR clubs in eight colleges in Arba Minch. The EACC plans to do the same in other regions. Such clubs encourage students to resolve their disputes peacefully through mediation and help foster better relationships in educational institutions by assisting students to gain an insight into peaceful methods of dispute resolution. Students are also encouraged to pursue professional training on ADR.

E. Resource Center

The EACC maintains a resource center at its head office. The resource center is stocked with a books and documents on ADR and related topics. The resource center is open for professionals on ADR, academics and students who want to expand their knowledge on ADR.

F. Website

The EACC's website, www.eacc.com.et, is up and running and provides a detailed and up to date information for those who seek information on EACC's activities

የሰ/መ/ቁ 44800
ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሃይ ታደሰ
2. ሂሩት መለሰ
3. ታፈሰ ይርጋ
4. አልማው ወሌ
5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ ጠ/አስቻለው አሻግሬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፊጅ መንበረ አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የመያዣ ውል ይፍረስልን ጥያቄ ነው። አመልካች ለፌ/መ/ደረጀ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተጠሪ ላይ ለወሰደው ብድር አመልካች በአ/አበባ ከተማ ወረዳ 23 ቀበሌ 12 ውስጥ የሚገኘውን ቤት በመያዣ ያስመዘገቡ ሲሆን አቶ ሐሚድ ይስሐቅ የተባሉ ግለሰብም 2 ቤቶች በመያዣ ሰጥተዋል ተበዳሪው ብድሩን አጠናቆ ባለመክፈሉ ባንኩ በመያዣ የያዛቸውን ቤቶች በሃራጅ ለመሸጥ በመንቀሳቀሱ ባንኩ የአቶ ሐሚድ ይስሐቅ ቤቶች በሐራጅ ሽጦ እዳውን በሙሉ ከፍሎ አጠናቋል። እዳው ተከፍሎ ስለተጠናቀቀ በመያዣ የሰጠሁት ቤት ካርታ እንዲመለስልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም። የመያዣው ውሉ ከተፈረመ 10 አመት ያለፈው በመሆኑ ቀሪ ሆኗል። ስለዚህ ባንኩ ቤቴን በሐራጅ ለመሸጥ የጀመረውን እንቅስቃሴ እንዲያቆም የያዘው ካርታ እንዲመለስ ያልተከፈለ እዳ ካለ የሂሳብ መግለጫ እንዲያቀርብና ቀሪውን ገንዘብ ከፍዬ ቤቴ ከመያዣነት እንዲለቀቅልኝ በማለት ጠይቀዋል። ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተበዳሪው የወሰደው ብድር ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ በመሆኑና በፍ/ሀ/ቁ/ 3058/1/ የተመለከተው የ10 አመት ጊዜ ከማለፉ በፊት በመያዣ ንብረቱ ላይ እንቅስቃሴ የጀመረ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው። የአመልካች ዋነኛ አቤቱታ የመያዣው ውል ከተመዘገበ 10 አመት ስላለፈው በፍ/ሀ/ቁ 3058/1/ መሰረት መያዣው ቀሪ ነው የሚል ነው። ይህ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን ቅሬታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል። ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል።

አመልካች ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለወሰደው ብድር ቤታቸውን በመያዣ ሰጥተዋል። የመያዣ ውሉም የተመዘገበው በ1987 ዓ.ም. መሆኑን እንዲሁም ተበዳሪው ድርጅት ብድሩን መክፈል ባለመቻሉ ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም. ማስጠንቀቂያ መስጠቱን አመልካች አልካደም። አመልካች መያዣው ቀሪ ነው በማለት የሚከራከሩት የፍ/ሕ/ቁ 3058/1/ በመጥቀስ ነው። በመሆኑም ይህን ድንጋጌ መመልከት ያስፈልጋል። አመልካች የጠቀሱት ይህ ድንጋጌም እንደሚከተለው ይነበባል።

የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው።

በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ የመያዣ ውል ውጤት የሚኖረው መያዣው ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ እስከ 10 ዓመት ድረስ ነው። በመሆኑም በመያዣ ውሉ ምክንያት በሚገኙ ማናቸውም መብቶች መገልገል የሚቻለው ይኸው የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ይሆናል ማለት ነው። ይህ የጊዜ ዘመን ሲራዘም የሚችለው 10 ዓመቱ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስ አዲስ ምዝገባ ተከናውኖ ከሆነ ብቻ እንደሆነ ከፍ/ሕ/ቁ 3058/2/ እንገነዘባለን። በመሰረቱ ይህ ህግ አመልካች እንደሚሉት የይርጋ ድንጋጌ አይደለም። ይርጋ ማለት በህግ ተሰይቶ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቢኒላ በአንድ ጉዳይ ክስ ለማቅረብ የሚከለከልበት የህግ ፅንሰ ሃሳብ ነው። በመሆኑም ይርጋ አንድ ሰው በጉዳዩ ላይ መብት ያለው ቢሆንም እንኳን ይህንን መብቱን ለመጠየቅ የማይችልበትን ገደብ የሚመለከት ነው። ይህ ክልከላም ተፈጻሚ የሚሆነው ክስ ከቀረበ በኋላ ተከሳሹ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ የተከራከረ ከሆነ ነው። ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ከሆነ ቢኒላ ክስ አቅርቦ ተከሳሽ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን በመግለፅ ካልተቃወመ ክሱ ተቀባይነት አግኝቶ መታየት ይቀጥላል። የጊዜ ገደቡ ቦግለፉ ብቻ ፍ/ቤት የይርጋውን በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ክሱን ውድቅ ሊያደርግ አይችልም። የፍ/ሕ/ቁ/3058/1/ የሚያስቀምጠው የይርጋን ጽንሰ-ሐሳብ አይደለም። የተጠቀሰው አንቀፅ የሚናገረው በህጉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማለፉ የመያዣው ውሉን ቀሪ (lapse) የሚያደርገውና ከዚህ ጊዜ ቢኒላ መያዣ ውሉ ተጠቃሚ የሆነው ሰው በመያዣው ላይ ያለው መብት የሚያበቃበትን ሁኔታ ነው። የመያዣ ውሉ ከተመዘገበ ቢኒላ 10 ዓመት ሆኖት እንደሆነና እንዲታደስ ካልተጠየቀ ቢያቂ ባይኖርም አቃቤ መዝገቡ መያዣውን እራሱ ሊሰርዘው እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ 1632/2/ ተመልክቷል። በመሆኑም መያዣ ሰጪው 10 ዓመት በማለፉ መያዣው እንዲሰረዝ ጥያቄ ባያቀርብም መዝጋቢው አካል ራሱ ምዝገባውን ሰርዞ መያዣውን ቀሪ ሊያደርገው ይገባል።

በሌላ በኩል መያዣው ነሐሴ 17 ቀን 1987 ዓ.ም. የተመዘገበ ቢሆን በመያዣ የተያዘው ቤት አመልካች ክስ እስከመሰረቱበት ህዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ አለመሸጡን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል። አመልካችም ይህንኑ ጊዜ መሰረት አድርገው ነው መያዣው ቀሪ ነው ያሉ የሚከራከሩት። ተጠሪ በበኩሉ መያዣው ከተመዘገበ ቢኒላ ተበዳሪው እዳውን ባለመክፈሉ 10 ዓመቱ ሳያልፍ

ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም. ማስጠንቀቂያ በመስጠት የይርጋ ጊዜን ማቋረጥ የሚቻለው ለዋና እዳ እንጂ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አይደለም የሚል ነው። ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በፍ/ህ/ቁ 3058 ስር የተቀመጠው የጊዜ ገደብ የይርጋ ጊዜ ገደብ ባለመሆኑ ስለይርጋ ማቋረጫ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም። በሌላ በኩል ግን ባለገንዘቡ የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ 10 ዓመት ከማለፉ በፊት በመብቱ መገልገል ጀምሯል ሊባል የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ሊታይ ይገባል። በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ለሰጠው ብድር መያዣ ባንክ ብድር ካልተከፈለው የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ንብረቱን ለመሸጥና የባለቤትነት ስሙን ለግዢ ለማስተላለፍ እንደሚችል በቁጥር 3 ስር ተመልክቷል። በመሆኑም ባንኮች የመያዣ መብታቸውን መገልገል የሚጀምሩት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለመሆኑ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። በተያዘው ጉዳይ ቢሆን ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም. ማስጠንቀቂያ በመስጠት በመብቱ መገልገል ጀምሯል። መያዣው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው 10 ዓመት ሳያልፍ ነው። ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ቤቱን ሳይሸጥ የ10 ዓመቱ ጊዜ አልፎ ሊሆን ይችላል። የቤቱ ሽያጭ ሳይጠናቀቅ 10 ዓመቱ ማለፉ ብቻውን ግን መያዣውን ቀሪ አያደርገውም። ሊታይ የሚገባው ተጠሪ በመብቱ መገልገል የጀመረበት ጊዜ ነው። ከዚህ አኳያ ሲታይ ደግሞ መያዣው ቀሪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም። በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም።

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ በመ/ቁ 78317 ታህሳስ 09 ቀን 2000 ዓ.ም. እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 64469 ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንተዋል።

2. ውሳኔው ስለፀና ይህ ችሎት ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ትዕዛዙ ተነስቷል። ትዕዛዙ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ለመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ወ/ኅ

Federal Supreme Court Cassation Bench: File No. 44800

Justices: Menberetsehai Tadesse
Hirut Melese
Tafesse Yirga
Almaw Wole
Ali Mohammed

Petitioner: Ato Aburazak Hamid

Respondent: Commercial Bank of Ethiopia
October 5, 2002 E.C

Civil Code: application by the petitioner that there is a fundamental mistake of law in the application of Article 3058(1) of the Civil Code by the Federal First Instance Court and Federal High Court.

Held: Article 3058(1) does not provide a period of limitation. Creditors commence to exercise their rights as a mortgagor starting from the date of the issuance of default notice.

Summary of Judgment

The relief sought in this file is the cancellation of contract of mortgage. In his statement of claim presented to the Federal First Instance Court, the petitioner stated that Hamid and Family Agricultural Products Private Limited Company mortgaged the dwelling house located in Woreda 23, Kebele 12 to secure the payment of the loan that it took from the respondent. Moreover, Ato Hamid Isac also mortgaged two additional dwelling houses for to secure the payment of the same loan. Upon the failure of the petitioner to repay the loan, the respondent bank proceeded with the sale of the two houses mortgaged by Ato Hamid Isac and discharged the whole debt. However; the petitioner contended that the bank has failed to hand over the title deed of the house in spite of the fact that the debt has been reclaimed. The petitioner went on to argue that since ten years have lapsed after the making of the contract of mortgage, the obligations arising out of it cannot be exercised owing to lapse of period of limitation. The petitioner further pleaded the court to oblige the bank to

desist from activities aimed at the sale of his house, to hand over the title deed over the house and if the bank claims outstanding debt to present financial statement to that effect so that the petitioner can effect the payment of the debt, if any and to bring the mortgage to an end.

The court decided that the statement of claim is not acceptable since the entire debt has not yet been repaid and the respondent has commenced the process for the sale of the mortgage before the lapse of the ten years period of limitation provided under Article 3058(1) of the Civil Code . Following the appeal the petitioner took from this decision, the Federal High Court confirmed the decision of the Federal First Instance Court. This petition is presented to the Cassation Division on account of this decision. The principal argument of the petitioner is that the contract of mortgage had been extinguished as it has been more than ten years since its entry was made. The cassation division has examined the matter as follows.

The petitioner mortgaged his house for the debt that Hamid and Family Agricultural Products Private Limited Company took from the respondent. This contract of mortgage was registered in 1987 E.C. The respondent gave the Private Limited Company a default notice written on October 24, 1992 E.C for its failure to repay the debt. The petitioner did not contest these facts. The petitioner contention that the contract of mortgage is extinguished is based on Article 3058(1) of the Civil Code which provides that the 'registration of a mortgage shall be effective for ten years from the day when the entry was made'.

According to this provision, a mortgage shall produce legal effects for ten years since its entry was made. Therefore it would be possible to exercise all the rights that emanate from the contract of mortgage before the lapse of this period. It is possible to gather from the reading of Article 3058(2) that the period can be prolonged provided that a new entry is made with a view to renew the contract. However, this provision is not a rule on period of limitation as alleged by the petitioner. Period of limitation refers to a concept whereby it is prohibited to institute a legal action after the lapse of the period specified in the law. Consequently, it is a limitation prohibiting one from exercising rights even if one has certain rights. This prohibition

from instituting legal action takes effect if the defendant invokes lapse of period of limitation by way of preliminary objection. If the defendant fails to invoke this as a preliminary objection when the plaintiff brings legal action, then the matter would be a subject of judicial consideration. The court can not dispose the case by invoking lapse of period of limitation on its own motion. Article 3058(1) does not enunciate the concept of period of limitation. This provision submits that the lapse of the period specified therein would have the effect of extinguishing the contract and the rights thereof would come to an end. Article 1632(2) of the Civil Code calls upon the keeper of registers to cancel the contract of mortgage if it has been ten years since its entry has been made and no request has been to renew it. Thus, the keeper of registers may rescind the entry of the mortgage if it has been years since its entry was made whether or not the mortgagee as applied for such a cancellation.

The entry of the mortgage in the case at hand was made on August 17, 1987 E.C. The house mortgaged was not sold until the date the petitioner instituted the legal action i.e. November 12, 1999 E.C. the petitioner contends that the contract of mortgage is extinguished based on these dates. The respondent, on its part, contended that it has placed the debtor in default on October 24, 1992 E.C before the lapse of the period of limitation. Consequently, the respondent submitted that the period of limitation did not lapse. The petitioner did not deny the fact that he has been given the said default notice. However, his contention is based on the argument that the interruption of period of limitation by giving default notice applies to the principal obligation not to the ancillary obligation of the contract of mortgage. As stated above, since the period stated under Article 3058(1) is not a period of limitation, his arguments concerning interruption of period of limitation are not warranted. However, the issue as to when the creditor is said to have started availing itself of its rights under the contract after the date of entry of the contract of mortgage calls for scrutiny. The bank can proceed with the sale of the immovable mortgaged as a real security for the debt it furnished should the principal debtor fail to pay by giving a default notice of a month, pursuant to Article 3 of Proclamation 97/90. As a result, it is possible to understand from this provision that banks commence exercise of their rights as a mortgagor starting from the issuance of default

notice. In the case at hand, the respondent has already commenced exercise of its rights under the contract of mortgage by giving default notice on October 24, 1992 E.C. The default notice was served before the lapse of the entry of the contract of mortgage. Ten years have lapsed since the respondent served default notice without disposing the house. The mere fact that ten years period lapsed before the culmination of the sale of the house does not render the contract of mortgage of no effect. What matters most is the date the respondent commenced exercise of its rights under the contract. From this point of view, there is no legal basis for the contract of mortgage to be extinguished. Therefore, it is not possible to say that there is fundamental mistake of law in the decisions of the lower courts dismissing the statement of claim of the petitioner. The decisions of both the federal first Instance court and that of the federal high court are confirmed.

የአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት
ሰኔ 3 ቀን 1979 ዓ.ም.

ዳኞች ሀ.
ለ.
ሐ.
ዐቃቤ ሕግ መ.

ተከሳሽ፡- የመቶ አለቃ ሁንዴ ለሜቻ ከወህኒ ቤት ቀርቧል። ተከላካይ ጠበቃ አቶ ዮሴፍ ሙሉጌታ ቀረቡ። መዝገቡ ያደረው ለውሣኔ ስለሆነ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ዓቃቤ ሕግ በቁጥር 629/1754/ዘ 0/78 ጥር 15 ቀን 1978 ዓ.ም. በተጻፈ የክስ ማመልከቻ በተከሣሽ የመቶ አለቃ ሁንዴ ለሜቻ ላይ የመሠረተው ክስ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 523 የተመለከተወን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 23 ክልል ውስጥ ጥቅምት 3 ቀን 1979 ዓ.ም. ከጧቱ 4 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ መንስኤው ባልታወቀ ምክንያት ሟች ወ/ሮ ጥሩነሽ ግራባ የተባሉትን ሰው በፋስ መጥረቢያ ከራሣቸው ላይ አንድ ጊዜ መትቶ በመግደሉ ተከሷል የሚል ነው።

ተከሣሽ የካቲት 4 ቀን 1978 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እዚህ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ በንባብ ከሰማ በኋላ ቅጅው ደርሶት እምነት ክህደት ሲጠየቅ የለእምሮ ህመምተኛ ስለሆንኩ የእምነት ክህደት ቃል መስጠት አልችልም፤ ፍ/ቤቱ ወደ ህክምና ይላከኝ በማለት ስላመለከተ ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ተልኮ የለእምሮ ጤንነቱ እንዲመረመር ተደርጓል።

የአማኑኤል ሆስፒታልም በቁጥር አስ/1020/82/79 ጥቅምት 26 ቀን 1979 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ ተከሣሽ ሁንዴ ለሜቻ በአሁኑ ወቅት አእምሮው የተቃወሰ አለመሆኑንና ወንጀሉንም በፈጸሙበት ጊዜ እብደት እንዳልነበረው በማረጋገጥ ለፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ መሆኑን የሆስፒሉ ሕጋዊ የሕክምና ኮሚቴ እንደወሰነ ገልጿል።

ከዚህ በኋላ ተከሣሹ በተከላካዩ ጠበቃ በአቶ ዮሴፍ ሙሉጌታ አማካይነት እየተረዳ ለቀረበለት የእምነት ክህደት ጥያቄ ጥፋተኛ አይደለሁም ሲል ክዶ ተከራክሯል።
ዓቃቤ ሕግ እንደክሱ አቀራረብ የሚያስረዱ ምስክሮች ያሉት መሆኑን በመግለጽ እንዲቀርብለት አሳሳቦ ሁለት የሰው ምስክሮች 2 ገጽ የጽሁፍ ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል።
1ኛ/ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ወ/ሮ ናርዶስ ወልደሰንበት የሰጡት ቃል ተከሣሹን አውቀዋለሁ። የጋብቻ ዝምድና አለን። የባለቤቱ ወንድም የልጅ ልጅ ነው። የተከሰሰበትን አላውቅም። ተከሣሽ ከየት እንደሆነ አላውቅም መስከረም 30 ቀን 1978 ዓ.ም. ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ ወደ እኛ ቤት መጥቶ የትክክለኛ ሰው አነጋገር

አይናገርም፤ ሰውነቱንም ለመቆጣጠር አይችልም። ባዶ እጁን በመያዝ ከእኛ ቤት ተቀምጦ ሁኔታው ስላሰጋን እያባበልነው ከሰነበተ በኋላ ጥቅምት 3 ቀን 1979 ዓ.ም. ጨርሶ አእምሮውን ሳተና እየሮጠ በየሰው ቤት መግባት በየጫካው መሄድ ጀመረ። በዚህ ጊዜ እኔ እርሱን መያዝ አቅቶኝ ሰው ለእርዳታ እንዲመጣልኝ ጩኸት በማሰማት እርሱን በመከታተል ላይ ሣለሁ ልደርስበት አልቻልኩም። እርሱ እየሮጠ ሄደ። ጩኸት ሰምቼ ወደ ተጮኸበት ቦታ ስደርስ ሰዎች በብዛት ተሰብስበዋል። ተከሣሽ ከእኛ ቤት ሲወጣ ያልያዘውን መጥረቢያ በእጁ ይዞ ዘራፍ እኔ ማነኝ እያለ ሲፎክር አገኘሁት፤ ብለው የመሰከሩ ናቸው።

2ኛ/ የዓቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ታዬ በትሩ የመሰከረው ተከሣሽን አውቀዋለሁ፤ ከእርሱ ጋር ጸብም ሆነ ዝምድና የለኝም። የተከሰሰው ሰው በመጥረቢያ በመምታቱ ነው። ጥቅምት 3 ቀን 1979 ዓ.ም. ከጧቱ 4 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በከፍተኛ 15 ቀበሌ 23 ክልል 1ኛ/ እኔ 2ኛ/ ጀማነህ ኃይሌ እና 3ኛ/ ሰማ በየነ የተባልነው የአብዮት ጥበቃ አባላት በሮንድ ሥራ ላይ ተሰማርተን በመዘዋወር ላይ ሳለን አንዲት ስማቸውን የማላውቃቸው ሴት ወደ እኛ ዘንድ መጥተው አንድ ሰው በጩቤ ሰው ሊገድልብኝ ነውና እርዱኝ ባሉት መሠረት ከእሣቸው ጋር ሄደን ከአንድ ቤት አጠገብ ልንደርስ ስንል ብዙ ሰዎች ተሰብስበው አየን። ከዚያም ከእኔ ጋር የነበሩት ሁለት የአብዮት ጥበቃ አባላት ከሰዎች መካከል ገብተው እኔ ከመንገድ ላይ ሳለሁ ተከሣሽ ሰዎች ከከበቡት ቤት ውስጥ በእጁ መጥረቢያ ይዞ ወጥቶ "ይህ ወታደር ማንን ለመግደል ነው የመጣው።" በማለት ወደ እኔ በመጠጋቱ በመጥረቢያ ሊመታኝ ሲል በመሸሽ ወደ አንድ የእጥር በር ካለው ቤት እንደገባሁ ተከሣሹ ተከታትሎ መጥቶ በመጥረቢያ አጥሩን ከመታው በኋላ ከግቢው ውስጥ ገብቶ አንዲት ቆማ የነበረችውን ሴት "ኃይለሥላሴን የገደለው ማነው? ብሎ ጠይቋት "እኔ አላውቅም" ስትለው በመጥረቢያ ከጆሮ ግንዷ ላይ አንድ ጊዜ መትቷት ወደቀች። በዚህ ጊዜ እኔም ለሕይወቴ ስለፈራሁ በአጥሩ በኩል ዘልዬ ወደ ቀበሌው ጽ/ቤት ሄድኩ። ከዚያው እንዳለሁ አምቡላንስ መጥቶ የተመታችውን ሴት ወደ ሆስፒታል ወሰዷት በዚያኑ ዕለት የተመታችው ሴት ሞተች ማለትን ሰማሁ። ተከሣሹ በዕለቱ ሽሚዝ ብቻ ለብሷል። እኔ እየሮጥኩ የብረት አጥር ካለው ቤት ሰገባ ከተመታቸው ሴት ሌላ አልነበረም። እኔ እየሮጥኩ ስገባ ከግቢ ውስጥ የተመታችው ሴት ቆማ ነበር። ተከሣሹ ይዞት የነበረው መጥረቢያ እጀታው እንጨት ነበር። ተከሣሹ አልቦት የመናደድ ሁኔታ ይታይበት ነበር እኔ የደንብ ልብስ ለብሼ ነበር በማለት አስረድቷል።

ዓቃቤ ሕግ የሰው ምስክር ያበቃ መሆኑን በመግለጽ የሚች አስክሬን በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተመርምሮ በቁጥር 2898/44/78 ህዳር 2 ቀን 1978 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ሽኝነት ሁለት ገጽ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ትርጉም ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘ ሲሆን ፍሬ ሃሳቡም የራስ ቅሏ ከኋላ በኩልና በራሷ ጎን በኩል ያለው ስፌት ተላቋል። የቀኝ የራስ ጎንና የቀኝ ጆሮ ግንዷ አጥንት ተሰብሯል። የራስ ቅሏ መሠረተ አጥንት ተሰብሯል። በአንጎሏ ሽፋንና በሁለቱም ራሷ ጎን የተቋጠረ ደም ተገኝቷል። አንጎሏ ተሰርጉዶ ተቀጥቅጦአል። ለሞት

ያበቃትም 1ኛ አንጎሏ በመጎዳቱ። 2ኛ የራስ ቅሏ በመሰባበሩ 3ኛ ራሷ ላይ ጉዳት ስለደረሰባት መሆኑን የሚገልጽ ነው።

ዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ያበቃ መሆኑን ስለገለጸ ፍ/ቤቱ ክስና ማስረጃውን መርምሮ ተከሣሹ መከላከል የሚገባው መሆኑን ብይን ሰጥቷል።

ተከሣሽ በተከላካይ ጠበቃው አማካይነት የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ ያለው መሆኑን በመጥቀስ የሚከተለውን የመከላከያ ጭብጥ አስመዝግቧል።

1ኛ/ ተከሣሹ በውትድርና ሥራው ላይ ሣለ ጥሩ መኮንን እንደነበረና ከጊዜ በኋላ የአእምሮ ህመም አድሮበት በየጊዜው ይታመም እንደነበር ከዚያም እየተገደደ ወደ ሆስፒታል ይወሰድ የነበረ መሆኑን እንዲሁም ህመሙ በተነሳበት ጊዜ በንብረትና በሰው ላይ አደጋ ያደረሰ እንደነበረና ለማድረስም ይሞክር የነበረ መሆኑን።

2ኛ/ ተከሣሹ ህመሙ በሚነሳበት ጊዜ አእምሮውን መቆጣጠር የማይችል መሆኑንና በቁጥጥር ሥር እየዋለ ወደ ሆስፒታል ይገባ የነበረ መሆኑን እንዲሁም በንብረትና በግለሰብ ላይ አደጋ ያደርስ የነበረ ለመሆኑና በተለይም የተከሰሰበትን ወንጀል በፈጸመበት ሰሞን ቤተሰቦቹ አስረውት ሣለ የታሠረበትን ገመድ በጥሶ ከቤት በመውጣት ወንጀሉን የፈጸመ መሆኑን ያስረዳሉ የሚል ነው።

1ኛ/ የመከላከያ ምስክር ሻለቃ መኮንን ጥላሁን የመሰከረው ተከሣሹን አውቀዋለሁ። ጸብም ሆነ ዝምድና የለንም። ተከሣሽና እኔ የምንተዋወቀው ከ1977 ዓ.ም. እስከ 1978 ዓ.ም. ድረስ አብረን በውትድርና ሥራ በምንሠራበት ጊዜ ነው። ተከሣሽና እኔ አብረን በሠራንበት ጊዜ ውስጥ እርሱ የዕዝ ቁንጮ ተረኛ መኮንን ሆኖ ሲሠራ ምክንያቱን አላውቅም፤ የደንብ ልብሱን አውልቆ በመጣል ቱታ እየለበሰ ብዙ በመለፍለፍ ሰዎችን እየረበሸ የክበቡን መስተዋት ማለት የመስኮት መስተዋት በመስበርና የራሱን ሻንጣ ቀድዶ በመጣል እንዲሁም ከአሳራባች ክፍል የሚገኘውን የመገናኛ ሬዲዮ በማበላሸት በጥበቃ ሥር ለትንሽ ጊዜ አቆይተነው ነበር። ሆኖም ሁኔታው ሊሻሻል ስላልቻለ በቁጥጥር ሥር ለትንሽ ጊዜ አቆይተነው ነበር። ሆኖም ሁኔታው ሊሻሻል ስላልቻለ በቁጥጥር ሥር እንዳለ ዋናው መሥሪያ ቤት ወደሚገኝበት ደብረዘይት ላክነው። ተከሣሽ ከላይ የተገለጹትን ድርጊቶች የፈጸመው በአንድ ሰሞን ነበር። ተከሣሽ ይህን ሁሉ በሚፈጽምበት ጊዜ አእምሮው ትክክል እንዳልነበረ ሰው ሁኔታ ነው። ተከሣሹ ወደ ደብረዘይት የተላከው በጥር ወር 1977 ዓ.ም. ሲሆን በመጋቢት ወር 1977 ተመልሶ መጥቶ ለተወሰነ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ሲሠራ ከቆየ በኋላ በነሐሴ ወር 1977 ያው የተለመደው ህመሙ ተነሳበትና ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይፈጽም በማለት አሥረነው አንዳንድ ህክምና ሲደረግለት እንደቆየ ሰውነቱን መቆጣጠር ችሎ ስለነበር ዕረፍት ስጡኝ ብሎ ከእሥራቱ ፈትተነው በዓይነ ቁራኛ ይጠበቅ ነበር። እንዴት እንደጠፋ አይታወቅም፤ጠፍቶ ወደ ደብረዘይት ሄዶ ናሮ ለህክምና እንደተላከ በመቁጠር ደብዳቤ ጻፉለት ተብለን ቴሌግራም አስተላልፈናል፤ በማለት አስረድቷል።

2ኛ/ የመከላከያ ምስክር ወ/ሮ ብዙነሽ ገብረሕይወት የመሰከረችውን ተከሣሹን ለአንድ ቀን ብቻ አይቸዋለሁ። ከእርሱ ጋር ጸብም ሆነ ዝምድና የለንም። ቀኑንና ወሩን አላስታውስም፣ በግምት አንድ ዓመት ከስምንት ወር ይሆነዋል፤ ከምሠራበት መሥሪያ ቤት ቆይቼ ወደ ቤቴ እንደገባሁ ከውጭ እንጨት ትፈልጥ የነበረችው ልጄ ውብነሽ ማሞ የምትፈልገውን እንጨት በመተው መጣብኝ ብላ ወደ ቤት በመግባት በሩን ዘጋች። በዚህ ጊዜ ማንን ነው መጣብኝ የምትይው ስላት ቀደም ሲል ትንንሽ ከሆኑ የሠፈር ልጆች ጋር እያጨበጨበ ሲጫወት ያየሁትን ተከሣሽን የአባባ ገለታ ወንድም መሆኑን ገለጸችልኝ። ከዚያም ልጄ እንጨት ትፈልጥበት በነበረው መጥረቢያ ተከሣሹ የዘጋነውን በር መፍለጥ ጀመረ። ልጄም ኧረ በአባባ ገለታ "በኢየሱስ ክርስቶስ በይ" ብላኝ እኔም በኢየሱስ ክርስቶስ ብለው በሩን ከመፍለጥ አልታገሰም። በመካከሉ የአባባ ገለታ ባለቤት ወ/ሮ ናርዶስ የተባሉት መጥተው ምነው ልጄ የዘመድ ቤት እንዲህ ታደርጋለህ" ሲሉት መፍለጡን አቁሞ መጥረቢያውን ከትከሻው ላይ እንዳደረገ ሄደ። እኔና ልጄ በሩን በመክፈት ስንመለከት ተከሣሹ የመንግሥት ፈረስ የሚቀመጥበትን ቤት በር በመጥረቢያው ፈለጠውና በሩ ተከፈተ። ከዚያም ተከሣሽ ወደ በአታ ቤተክርስቲያን የሚያመራውን መንገድ ይዞ እንደ ሄደ ከፈረስ ቤቱ የነበሩት ሰዎች ተከሣሽ ሰው ገድሎ ሄደ እያሉ ሲጯጯሁ ሰማሁ። ተከሣሽን በዚያን ዕለት ያየሁት በበሩ ቀዳዳ ነው። አለባበሱ ደህና ነበር በማለት አስረድታለች።

3ኛ/ የመከላከያ ምስክር አቶ ይደግልኝ ገብረሚካኤል የመሰከረው ጥቅምት 3 ቀን 1978 ዓ.ም. ከጧቱ በግምት ከሰዓት እስከ አራት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ 15 ቀበሌ 23 ክልል ውስጥ ከልጆቼ ጋር ሆኜ ፀሐይ እየሞቅሁ ሰውነቴን ሳዝናና ተከሣሽ እጅ ጉርድ ነጭ ሸሚዝ ለብሶ ከእኔ ግቢ ውስጥ ሲገባ አይቼው ወደ እኔ ይመጣል ብዬ ስጠባበቀው ውሾቹ ባሉበት በኩል ቀጥታ ሄዶ ውሾቹን በማለፍ የስዕል ሥራ ከምሠራበት ክፍል ውስጥ ገባ። በዚህ ጊዜ እኔም በመቆጣት ተከሣሽ ወዳለበት ክፍል ውስጥ ገባሁና በመያዝ ወደ ውጭ ጠምዝዤ አስወጣሁት። ስመለከተው በእጁ የመጻፊያ እርሳስ ይዞ ወጋሁህ ሲለኝ በመካከሉ ውብዓለም እደግልኝ የተባለችው ልጄ ተከሣሹን "የአባባ ገለታ ዘመድ ነው። ዕብድ ነው የተባለው መቶ አለቃ ነው።" አለችኝ። በዚህ ጊዜ አባባ ገለታ ጎረቤት ስለነበሩ አይዞህ በማለት ተከሣሽን አቅፍ አድርጌ በማግባባት ወደ ውጭ ለማውጣት ስሞክር ተከሣሽ "ይኸው ሰይጣን" በማለት መሬቱን በድንጋይ እየደበደበ "ልቀቀኝ ልግደለው" ሲል ውሾቹ ይጮሁ ስለነበር "አሁንም ልቀቀኝ ሰይጣኑን ልግደለው" በማለት እስከ ውሾቹ አፍ ድረስ ተጠጋ። ይህ ሁሉ ሲሆን የአባባ ገለታ ባለቤት መጥተው ሁኔታውን ይመለከቱ ነበርና "እቤቱ ድረስ ወስደህ አባክህ አሰርልኝ" ብለውኝ ለመውሰድ ሞክሬ ከአቅሜ በላይ ስለሆነብኝ ለቀቁሁትና ከግቢዬ ወጥቶ ሄደ፡ በማለት አስረድቷል።

የተከሳሽ ጠበቃ ቀሪዎቹን የመከላከያ ምስክሮች አልፈልጋቸውም አሉ። በጽሁፍ ማስረጃ በኩል 1ኛ ሚያዝያ 30 ቀን 1979 በቁጥር 11/22/9279 ከአየር ኃይል ሆስፒታል የተጻፈው ደብዳቤ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡም የመለያ ቁጥር ኤ 09070 መቶ

አለቃ ሁንዴ ለሜቻ የአእምሮ መረበሽ ስለደረሰበት በ16/5/77 ከጅጅጋ ጣቢያ ከአንድ ጤና ረዳት ጋር ወደ አየር ኃይል ሆስፒል ተልኮ ነበር። ለሶስት ሣምንታት ያህል በሆስፒታላችን ሲረዳ ከቆየ በኋላ ለከፍተኛ ህክምና 07/6/77 ወደ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ተልኮ በአእምሮ እስፔሻሊስት ከታየ በኋላ ሐኪሙም የአእምሮ መረበሽ /ኒሮሲስ/ እንዳለበት አመልክተው መድኃኒትና የ15 ቀን እረፍት ተሰጥቶት ከተመለሰ በኋላ በማማስቱ ማለትም በ8/6/77 ከሆስፒታላችን በሙሉ ጤንነት መውጣቱን ከጤና ፋይሎች መረዳታችንን እንገልጻለን የሚል ነው።

2ኛው ግንቦት 4 ቀን 1979 በቁጥር 23/ሀ/2788/79 በአገር መከላከያ ሚኒስቴር የአየር ኃይል 1ኛው ሚሳይል ሬጅመንት ለፍ/ቤቱ የጻፈው ደብዳቤ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡም መኮንኑ ጅጅጋ በነበሩበት ጊዜ ከ1977 ጀምሮ አልፎ አልፎ ራሣቸውን ሲያማቸው እንደነበርና በዚሁ ምክንያት ሐኪም ቤት ሄዶ ከሰው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመቀነስ አንዳንድ ከሥነ ሥርዓት ውጭ የሆኑ ድርጊቶች መፈጸማቸውን፣ ከፈጸሙትም ውስጥ፣

1ኛ/ ፈቃድ ሳይሰጣቸው ከሥራቸው ላይ ጠፍተው መሄድ፣
2ኛ/ ቀይ ጨርቅ ከራሣቸው ላይ በመጠምጠም ብዛት ያላቸውን መጻሕፍት ተሸክመው መዞር፣
3ኛ/ ለሠራዊቱ አገልግሎት የሚውሉ ብርቅና ውድ ንብረቶችን መሰባበር፣
4ኛ/ ካምፕ ነዋሪ የሆኑትን አባሎች ሌሊት እንቅልፍ መንሳት፣
5ኛ/ ሲያደርጉ የነበሩት እንቅስቃሴ ከዕለት ዕለት እየባሰ በመሄዱ በቤት ውስጥ እንዲታሠሩ ተደርጎ የታሠሩበትን ገመድ በመበጣጠስ ከጅጅጋ ደብረዘይት ድረስ ጠፍተው መምጣታቸውን ጠቅሶ መኮንኑ የነበሩበት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤታችን በቴሌግራም ቁጥር 23/ቀ/0974/79 አረጋግጦልናል። እኛም መኮንኑ እዚህ ከደረሱ በኋላ አስፈላጊውን የጤንነት ምርመራ እንዲያደርግላቸው በደብዳቤ ቁጥር 23/ሀ/143/78 መሠረት መስከረም 13 ቀን 1978 ወደ አየር ኃይል ህክምና ክፍል ልከናቸዋል። የሕክምና ክፍሉም ከ15/1/78 ጀምሮ የሁለት ሣምንት የበሽታ ዕረፍት ስጥቷቸው በዚሁ በተሰጣቸው የሐኪም እረፍት ተጠቅመው ከቤተሰባቸው ጋር በመኖር ላይ እንዳሉ በ3/2/78 የሰው መግደል ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው መታሠራቸውን እናውቃለን የሚል ነው።

ተከሣሹ በተከላካይ ጠበቃው በአቶ ዮሴፍ ሙሉጌታ እየተረዳ ጠቅላላ የመከላከያ ማስረጃ ያበቃ መሆኑን ስላረጋገጠ ግራ ቀኙ ወገኖች የፍርድ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል።

ይሁንና ዓቃቤ ሕጉም ሆነ ተከሣሽ የፍርድ ሃሳባቸውን አላቀረቡም። በወ/መ/ሕግ/ሥ/ሥ/ ቁጥር 148 መሠረት የሚደረገው የመጨረሻ ንግግር የግራ

ቀኑ ተከራካሪ ወገኖች መብት እንጂ ግዴታ ባለመሆኑ ለማቅረብ እንዲፈልጉ ተቀጥሮ ታልፏል።

ፍ/ቤቱ የክሱን ፍሬ ነገር ከህግና የመከላከያ ማስረጃው ይዘት ጋር በማገናዘብ አንድ በአንድ መርምሯል።

ተከሣሹ የመቶ አለቃ ሁንዴ ለሜቻ መንስኤው በውል ተለይቶ ባልታወቀ ምክንያት ሚች ወ/ሮ ጥሩነሽ ግራባን በፋስ መጥረቢያ አንድ ጊዜ ከራሷ ላይ መትቶ ገድሏል በመባል በቀረበበት ክስ ክዶ የተከራከረ ቢሆንም ሁለት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቀርበው አድራጎቱን በመዘርዘር መስክረውበታል።

የሚች ሕይወት ያለፈው በደረሰባት ምት ምክንያት መሆኑን ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል የተሰጠው የአስክሬን ምርመራ ውጤት አረጋግጧል።

ተከሣሹ በበኩሉ በተከላካይ ጠበቃው አማካይነት እየተረዳ 3 የመከላከያ ምሥክሮች አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ሁለት ገጽ የጽሁፍ ማስረጃም አያይዟል። የመከላከያ ማስረጃው ይዘት በጥቅል ሲጤን ተከሣሹ አሁን የተከሰሰበትን ሰው የመግደል ወንጀል በአጋጣሚው የአእምሮ መታወክ ህመም የተነሳ የባህርይ ለውጥ ማሳየቱንና የማሕበራዊ ግንኙነቱም እየተበላሸ መሄዱን፣ እንዲሁም ይህን ወንጀል ከመፈጸሙ ቀደም ሲል ጤነኛ አእምሮ አለው የሚሰኝ ሰው ሊያደርገው የማይገባውን ልዩ ልዩ ድርጊት ይፈጽም የነበረ መሆኑን የሚጠቁም ነው።

ተከሣሹ እዚህ ፍ/ቤት የካቲት 4 ቀን 1978 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቀርቦ በተጠየቀበት ወቅት የአእምሮ በሽተኛ መሆኑን በመግለጽ የህክምና እርዳታ እንዲደረግለት ጠይቆ ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ሄዶ እንዲመረመር የተደረገ ሲሆን የአማኑኤል ሆስፒታልም በቁጥር አስ/1ውቤ/82/79 ጥቅምት 26 ቀን 1979 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ተከሣሹ ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ እብደት ያልነበረውና ምርመራውንም ባደረገበት ወቅት አእምሮው ያልተቃወሰ ጤነኛ መሆኑን በመግለጽ ለፈጸመው ወንጀል በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል መሆኑን አረጋግጧል።

እዚህ ላይ ተገናዝቦ መታየት የሚገባው ነጥብ ስለተከሣሹ የአእምሮ ጤንነት ጉዳይ ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባፈራው ሣይንሳዊ የህክምና ዘዴ በመጠቀም በሳል የሕክምና ባለሙያዎች የሰጡት ማረጋገጫ ወይስ በአካባቢ ሁኔታ የተነገረው የምሥክርነት ቃል ነው የሚለው ነው።

የድርጊቱን አፈጻጸም ሁኔታ ለማጣራትና የተከሣሽን የወንጀል አድራጎት ለማረጋገጥ ከተሰበሰበው የዓይንና የአካባቢ የሕግና የመከላከያ ማስረጃ አኳያ ተከሣሹ የአእምሮ መታወክ ህመም ይታይበት እንደነበረ ጠቋሚ ሁኔታዎች መኖራቸው ግልጽ ቢሆንም የአማኑኤል ሆስፒል ሕጋዊ የህክምና ኮሚቴ ግን ተከሣሹ ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ እብደት ያልነበረበትና በአሁኑ ወቅትም የአእምሮ መታወክ ህመም የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ለፈጸመው ወንጀል

በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚገባው መሆኑን በማረጋገጡ ፍ/ቤቱ ማስረጃነቱን አምኖ እንዲቀበለው አድርጎታል። ምክንያቱም ተከሣሹ ወንጀሉን ከመፈጸሙ በፊትም ሆነ በኋላ ያሳየው የነበረው ባሕርይ ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው የሚያደርገውን ዓይነት ነው ተብሎ በአካባቢ ሁኔታ የተጠቆመውን አጠራጣሪ ነጥብ ለማጣራት ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሕግ ቁጥር 51 መሠረት የሕክምና ምርመራ እንዲደረግ አዝዞ የተገኘው ማረጋገጫ ተከሳሽ ጤነኛ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በአጠቃላይ ተከሣሹን በቀረበበት ሰው የመግደል ወንጀል ክስ ክዶ የተከራከረ ቢሆንም ባቀረበው የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረበት ከመሆኑም በላይ በአቀረበው የመከላከያ ማስረጃ አልተደገፈም። ምንም እንኳን ተከሣሹ የአእምሮ መታወክ ህመም ያለበት መሆኑን ይሠራበት ከነበረው የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ በተጻፈለት ደብዳቤና በአቀረበው የሰው ማስረጃ ለማስረዳት ቢሞክርም የአእምሮ ጤንነትን በተመለከተ በቂ የህክምና ምርመራ አድርጎ ማረጋገጫ ከሰጠው የአማኑኤል ሆስፒታል የተሰጠው ምስክርነት የተከሣሹን ጤናማነት የሚያመለክት በመሆኑ ለፈጸመው ወንጀል በኃላፊነት ከመጠየቅ የሚያድንበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም።

ስለዚህ ተከሳሽ የመቶ አለቃ ሁንዴ ለሜቻ የተመሠረተበትን ሰው የመግደል ወንጀል የተጠናቀረውንም የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃ ከአማኑኤል ሆፒታል በተሰጠው ምስክርነት መሠረት ለፈጸመው ድርጊት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚገባው መሆኑን ስለአረጋገጠ ለክሱ በተጠቀሰው የወ/መ/ሕግ ቁጥር 523 መሠረት ጥፋተኛ ነው ብለናል።

ስለቅጣቱ ዓቃቤ ሕግ ያሳሰበው ስለ ተከሣሹ የቀድሞ የሕይወት ታሪክ የሚያቀርበው ሪከርድ ስለሌለ ጥፋተኛ ነው በተባለበት ሕግ መሠረት ተመጣጣኝ ቅጣት ይወሰንበት ብሏል።

የተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ያሳሰቡት ተከሣሹ ደካማ እናትና አባቱን ከመርዳቱም በላይ ደካማ ዘመዶችንም የሚረዳ ባለትዳር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ይህንኑ ሁሉ በመመልከት ከፍተኛ አስተያየት አድርጎና በውትድርና 11 ዓመታት ያገለገለውን ተመልክቶ ዝቅተኛ ቅጣት ይወሰንልኝ ብሏል።

ዓቃቤ ሕጉና የተከሣሽ ተከላካይ ጠበቃ ያቀረቡትን የቅጣት ሃሣብ አገናዝበን የታሠረው አንድ ዓመት ከ6 ወር ከአንድ ቀን የታሠረውን ለቅጣቱ በቂ አድርገን ወስነናል።

ተከሣሹ ከእሥራቱ እንዲፈታ ለአ.አ. ወህኒ ቤት ይጻፍ የይግባኝ መብት የተጠበቀ ነው።

የዳኞች ፊርማ፡- ሀ፣ ለ፣ ሐ፣

Addis Ababa High Court
Sene 3, 1979 E.C.
Judges: Unidentified
Prosecutor : Unidentified
Defendant: Lieutenant Hunde Lemecha represented by Defense Counsel Ato Yoseph Mulugeta

Summary of the Judgment

The defendant is charged with under Article 523 of the 1957 Penal Code[529] for killing Wro. Tirunesh Garba with an axe on Tikimt 3, 1979. He was sent to a mental hospital for examination and the medical report submitted confirmed that the defendant had no mental disturbance or insanity at the time of committing the crime.
The defendant pleaded not guilty. The prosecution called the following witnesses:

1. Wro. Nardos W/Senbet testified that the defendant is her relative. The witness testified that on Tikimt 3, 1979 the defendant came to her house at 12:00 p.m., run amok and entered different houses in the neighborhood. She tried to stop the defendant but failed to do so. While running after the defendant, she saw many individuals gathered at a place and some were crying. She arrived at the specific spot and saw the defendant holding an axe which he didn't have while he was with her a while ago. She heard him asking the crowed who they think he was.

2. Ato Taye Betru, a neighborhood guard on patrol at the relevant time, testified that a woman seeking help approached him and told him that a man was about to chop another individual. He went to the spot with his colleagues and saw the defendant holding an axe. The defendant then approached him and asked him who he came to kill. When the defendant came after him he fled the scene and went in to a nearby house. The defendant then sort of knocked on the fence of the house he entered with his axe and asked the woman he found in the premise 'who killed Emperor Haile Selassie?'. She responded that she did not know the killer and he struck her around

[529] The defendant was charged under the Penal Code of 1957 which is repealed by the Criminal Code of 2004.

her ear with his axe. The victim was taken to a hospital and died on the same day. The witness testified that the defendant was sweating and looked angry.

The prosecutor submitted a post mortem examination medical report which stated that the victim died as a result of the blow that she received from the defendant.

The defense on its part called the following witnesses:

1. Major Mekonnen Tilahun told the court that the defendant was his colleague. The witness testified that he had observed the defendant taking off his military uniform and walking around in track suit, talking a lot and disturbing others, and breaking the windows of the military meeting hall. The witness further made the following testimony. The defendant was put under detention for the above acts. Since his situation could not improve, the defendant was eventually remanded to the Army Head Quarters. Though he rejoined the army after sometime, he relapsed into his previous behavior and received treatment while under detention. The defendant was then given sick leave when he fled to Debre Zeit.

2. Wro. Bizunesh G/Hiwot , a resident of the neighborhood, testified that the defendant came to her house and picked an axe left idle in the premise and started to hit the gate of her fence and could not stop his act even when implored by her. He then left the house upon a plea from one of his relatives and then went to a nearby government barn and started to axe the door. She then saw him walking in the direction of the Ba'eta Church and eventually heard people raising hue and cry and shouting that he has killed a person.

3. Ato Yidegilign G/Michael, also a resident in the neighborhood, testified that the defendant came to his house and threatened to stab him with a pencil and that while he was pushing him out, he started to hit the ground yelling to be left alone. The witness testified that he drove the defendant out of his house by twisting his arm.

The defense also adduced the following written pieces of evidence:

1. A letter written by the Air Force Hospital, which states that the defendant was suffering from mental disturbance and was treated at the hospital for three weeks. The letter states that the defendant was sent to the Army Hospital in Addis for further treatment. The letter further states that the defendant was diagnosed with neurosis at the Army Hospital and fully recovered upon leaving the hospital.

2. Another letter written by a Division in the Ministry of Defense of which the defendant was a member states that the defendant, while serving in Jijiga, used to suffer from occasional headache, deterioration of personality and poor social relations. The letter also confirms that the defendant was admitted to hospital and has committed the following acts: abandoned his duty without permission, broke valuable properties that belonged to the army, disturbed camp residents at night, and eventually went to Debre Zeit without obtaining leave.

The Court pointed out that main issue in the case is whether it is the certified medical evidence or circumstantial evidences that should tip the balance of admissibility. Though it was proved by circumstantial evidence gathered from the scene of the crime that the defendant was suffering from mental disturbance, the medical evidence proves that he committed the crime while in a normal state of mind. The Court has accepted the certified medical evidence from the Amanuel Hospital as the most reliable. The prosecution has also presented evidence adduced to the Court and the testimony of witnesses which were not rebutted by the defendant. Therefore, the Court found the defendant guilty of the charge brought against him under Article 523 of the 1957 Penal Code. After weighing the aggravating and mitigating and circumstances adduced by the prosecution and defense, the court pronounced the following sentence.

In principle, penalty should be fixed based on the prior history of a defendant, taking into account the reason that prompted the act, and the seriousness of the offence. Since the prosecution has not submitted any evidence that shows that the defendant is a recidivist,

the Court has drawn a conclusion that the defendant has no crime record. Moreover, the Court noted that though it is medically proved that the defendant was sane at the time of committing the crime, it is hard to accept that the defendant was normal when he committed the crime against a person whom he has never met. Thus, the Court noted that for this reason it was difficult to apply Arts.48-51[530] of the Code.

The Court after examining the defendant's past military service and other mitigating circumstances adduced by the defense and noting that the defendant's state of mental health prior to and while committing the crime indicate that he was suffering from a undetected health problem which could not be diagnosed through medical examinations, and in light of the overall objectives of the law, sentenced him to a year and thirty one days imprisonment.

[530] These are provisions that deal with the standards of the defense of insanity and procedures to be followed in case when insanity is raised as a defense.

የመሬት ይዞታ መብትና በመሬቱ ላይ የተሠራ ቤት ባለቤትነት ጥያቄ: በፍርድ ላይ የቀረበ ትችት

ሞላ መንግሥቱ*

መግቢያ

በዚህ ርዕስ የሚተቹት ሁለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ውሳኔዎች ናቸው። ሁለቱን ውሳኔዎች በአንድ ርዕሰ ስር ለመተቸት የተፈለገውም አንድም ፍርዶቹ ተመሳሳይነት ስላላቸው ነው። ሁለተኛም ፍ/ቤቱ በተመሳሳይ ጉዳዮች የሚሰጣቸው የተለያዩ ውሳኔዎች የተጣጣሙ መሆን አለመሆንናቸውን ለማመልከት ሲሆን ሶስተኛም በውሳኔዎቹ የሚታዩትን ችግሮች ተደጋጋሚ መሆን አለመሆን ለማሳየት ነው።

በትችቱ የመሬት መብት የይዞታ መብት ሲሆን በመሬቱ ላይ የሚሠራው ቤት መብት ግን የባለቤትነት መብት መሆኑ መብቶቹን ከመወሰን አንፃር የፈጠረውን መሳከርና የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች በእነዚህ መብቶች ላይ ያላቸው ተፈፃሚነት ከሕገ መንግስቱና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጐች ድንጋጌዎች ጋር እንዴት ተጣጥመው መተግበር እንዳለባቸው ከፍርድ ቤቱ ውሳኔዎች አንፃር የጉዳዮቹን ዝርዝር ለማየት ይሞከራል።

I. ውሳኔ አንድ[531]

የአቶ አድነው አወቀ ይዞታ በሆነው በአዲስ አበባ የሚገኝ መሬት ላይ ቁጥር 560(ሀ) እና 560(ለ) የሆኑ ቤቶች ነበሩ። ባቤት ቁጥር 560(ሀ) አቶ አድነው አወቀ ከነቤተሰቦቻቸው የሚኖሩ ሲሆን በቤት ቁጥር 560(ለ) ደግሞ አቶ ገዛኸኝ አወቀ ይኖሩ ነበር።

የአቶ አድነው አወቀን መሞት ተከትሎ የሚች ባለቤት የነበሩት ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝና ልጆቻቸው ገነት አድነውና ደሣለኝ አድነው በጋራ በመሆን ቁጥሩ 560(ለ) የሆነውን ቤታችንን በኃይል ገብቶ በመያዝ እየተጠቀመበት ስለሚገኝ ቤቱን እንዲለቅልን ይወሰንልን በማለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአቶ ገዛኸኝ አድነው ላይ ክስ ያቀርባሉ። ተከሣሹ በበኩላቸው ክስ የቀረበበትን ቤት የሠራሁት ራሴ ስለሆንኩ ከሣሾች ምንም ዓይነት መብት የላቸውም፤ የቤቱ ባለቤትም እኔ እንጅ እነሱ አይደሉም። ስለዚህም ክሱ ውድቅ ተደርጐ በነፃ ልሰናበት በማለት ተከራከሩ።

ፍ/ቤቱ የከሣሽና የተከሳሽን የጽሑፍና የቃል ክርክር ከመረመረ በኋላ:-

1) ቁጥር 560(ለ) የሆነው ቤት ባለቤት ከሣሾች ናቸው ወይስ ተከሣሽ?

---

*ሌክቸረር፣ሕግ ት/ቤት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

[531]በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 05950 በ9/3/98 ዓ.ም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሳኔ

2) ባለቤቱ ተከሣሽ ናቸው ከተባለ በማን ይዞታ ላይ ነው ቤቱን የሠሩት? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ መርምሮ ውሳኔ[532] ሰጥቶባቸዋል። በውሳኔውም ቤቱን የሠራው ተከሣሽ መሆኑ ስለተረጋገጠ የቤቱ ባለቤትም እሱ ነው ካለ በኋላ ቤቱን የሠራውም የከሣሾች አውራሽ በሆኑት በሟቹ በአቶ አድነው አወቀ ይዞታ ላይ በእሳቸው ፈቃድ መሆኑን ማረጋገጡን አብራርቷል። ፍ/ቤቱ በመቀጠልም ከሣሾች ቤቱ የተሠራበትን ዋጋ ከፍለው ቤቱን ከተከሣሽ መረከብ የሚችሉ መሆኑን ከጠቀሰ በኋላ ሆኖም ተከሣሽ ቤቱን የሠራው ቦታው የከሣሾች አውራሽ ይዞታ መሆኑን እያወቀ ስለሆነ ከሣሾች መክፈል የሚገባቸው በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1180 በተደነገገው መሠረት ቤቱ የተሠራበትን ዋጋ 1/4 ብቻ ነው በማለት ወስኗል።

ተከሣሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ መልስ ሰጭን አስቀርቦ ግራቀኙን ክክራክረ በኋላ ይግባኙን ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል።[533] የስር ተከሣሹ በመቀጠልም የይግባኝ ሰሚውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ዘርዝሮ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታውን አቀረበ።

በዚህ አቤቱታውም፦

1. ከሣሾች በቤት ቁጥር 560(ለ) ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን ሳያረጋግጡ በከሣሽነት እንዲከራከሩ ፍ/ቤቱ በመፍቀድ ክርክሩ እንዲቀጥል ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፤
2. ክርክሩ የተነሳበት ቤት የተሠራበት ቦታ የአቶ አድነው አወቀ ይዞታ ነው ተብሎ መወሰኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1140 ትርጉምን ያልተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ፤
3. ክርክር የተነሳበት ቤት የተሠራበት ቦታ የአንደኛ ከሣሽ ባለቤትና የሌሎች ከሣሾች አውራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሬት የመንግሥት ነው ተብሎ የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ሊሻር ይገባዋል በማለት ጠይቋል።

የሰበር መልስ ሰጭዎችም ባቀረቡት መልስ፦

1. ክርክር የተነሳበት ቤት የተሠራው በአቶ አድነው አወቀ ይዞታ ቦታ ላይ መሆኑ በፍ/ቤቱ ስለተረጋገጠና ተከሣሽም በቦታው ላይ ቤቱን እንድሠራ አቶ አድነው አወቀ ፈቅደውልኛል በማለት ከሚጠቀምበት በሰተቀር በስጦታ የተሰጠው ለመሆኑ ወይም ቦታው የራሱ ለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ ባለመኖሩ፤

---

[532] ፍ/ቤቱ ሁለተኛውን ጭብጥ መመርመሩ አስፈላጊ የሚሆነው ቤቱን የሠራው በራሱ መሬት ላይ ከሆነ የቤቱ ባለሐብትነቱ የማይካ መሆኑንና ቤቱ የተሠራው በሌላ ሰው ይዞታ መሬት ላይ ከሆነ ግን የቤቱ ባለሐብትነት ባለይዞታው ቤቱ ሲሠራ ባኑት ተቃውሞ ወይም ባሳዩት ዝምታ ወይም በሰጡት ፈቃድ ላይ ተመሥርቶ የሚለያይ መሆኑን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

[533] በመዝገብ ቁጥር 43119 ህዳር 9 ቀን 1999ዓ.ም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ

2. ተከሣሽ በክርክሩ ላይ በፍ/ቤት ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስ ቤቱን ሠራሁ የሚልበት ቦታ የአቶ አድነው አወቀ መሆኑን አረጋግጦ ያስረዳ በመሆኑ፣
3. የቤት ቁጥር 560(ለ) የተሠራበት ቦታ ይዞታ የአቶ አድነው አወቀ መሆኑ ባቀረብነው ማስረጃ በፍ/ቤቱ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ.
4. ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ውሳኔውን ተቀብሎ ያፀደቀው ምንም ዓይነት የሕግ ስህተት የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ ስለሆነ፣

ውሳኔው የሕግ ስህተት አለበት የሚባልበት ምንም ምክንያት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል። የሰበር ሰሚው ፍ/ቤትም የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ "የሰበር አመልካች ክስ የቀረበበትን ቤት ለከሣሾች ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም" የሚል ጭብጥ በመያዝ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል።[534]

የሰበር ችሎቱ ውሳኔ፣

የተከበረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት "በፍትሐብሔር ሕጉ ስለንብረት በጠቅላላው በሚደነግገው ሶስተኛ መጽሐፍ ሥር በአንቀጽ 1178(1) ባለመሬቱ በግልጽ እየተቃወመው ማንም ሰው በሌላ ሰው መሬት ላይ ሕንፃ የሠራ እንደሆነ በሕንፃው ላይ አንዳችም መብት ሊኖረው እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን ባለመሬቱ ሳይቃወም በመሬቱ ላይ ሕንፃ የሠራ ሰው የዚሁ ሕንፃ ባለሀብት ሊሆን እንደሚችል ቀጥሎ በሚገኘው በቁጥር 1179 (1) ላይ ተመልክቷል። እንዲህ በሆነ ጊዜም ባለመሬቱ ከባለ ሕንፃው ጋር የተስማሙበትን ግምት በመክፈል ወይም በግምቱ ያልተስማማ እንደሆነ በቁጥር 1180 በተመለከተው መሠረት የሕንፃውን ግምት በመክፈል ሕንፃውን ማስለቀቅ እንደሚችል ተደንግጓል" ካለ በኋላ በመቀጠል፡-

> "ሕጉ በዚህ መልኩ የተቀረፀ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች ደግሞ አባትና አውራሽ የሆኑት አቶ አድነው አወቀ በነበራቸው መሬት ላይ አመልካች ቤት እንዲሠሩ ፈቅደውላቸው ቤቱን የሠሩ መሆኑን የፌ/መ/ደ/ ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ አስፍሯል።
> ከላይ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 1179(2) መሠረት በሌላ ሰው መሬት ላይ ቤት (ሕንፃ) የሠራ ሰው የሕንፃውን ግምት ተቀብሎ ሕንፃውን ለባለመሬቱ ለማስረከብ የሚገደደው ባለመሬቱ ሳይቃወም ሕንፃውን የሠራ በሚሆንበት ጊዜ ነው። ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የሠራው የአንደኛ ተጠሪ ባለቤትና የቀሪዎቹ ተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት ሟች አቶ አድነው አወቀ ሳይቃወሙ በቀሩበት ሁኔታ ሳይሆን ይልቁንም ፈቃዳቸውን ሰጥተዋል በተባለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ ሕጉ በወጣበት ዘመን

---

[534] በሰበር መዝገብ ቁጥር ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ

ግለሰቦች በመሬት ባለቤትነት ረገድ መብት የነበራቸው ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገመንግስት መሬት በግል ባለቤትነት መያዙ ቀርቶ የመንግስትና የሕዝብ ሀብት እንዲሆን የተደረገ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች የመሬቱ ባለቤት ስለሆኑ አመልካች በመሬቱ ላይ የሠራውን ቤት የዋጋ ግምት 1/4 ከተጠሪዎች ተቀብለው ቤቱን ያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ በዚህ ረገድ ከነበረው ሕግም ሆነ ከሕገመንግስታችን ጋር የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል" የሚለውን ምክንያት ከሰጠ በኋላ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ውሳኔውም፦

1. "የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ሕ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. "አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለተጠሪዎች ሊያስረክብ አይገባም፡፡" የሚል ነው፡፡

II. ውሳኔ ሁለት[535]

አቶ ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኮል በምዕራብ ጉጃም ዞን በመርጠ ለማርያም ከተማ ቤት ሠርተው በጋብቻ ሲኖሩ ከቁዩ በኋላ ህፃን ዘላለም ተመስገንን ወልደው አቶ ተመስገን ዳኘ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የሟች ሚስት የነበሩት ወ/ሮ እባቡ ቸኮል የሟች አባትና እናት የሆኑት ቄስ ገበዝ ዳኘ ካሳና ወ/ሮ ምትኬ አየለ ሟች በመርጠ ለማርያም ከተማ የሠራውን ቤትና ሌሎች የቤት ዕቃዎች በመያዝ ስለከለከሉኝ ቤቱንና ንብረቱን ያስረክቡኝ በማለት በራሳቸውና በህፃን ልጃቸው ስም ለምዕራብ ጉጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ አቀረቡ፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው ቤቱን የሠራነው ራሳችን ስንሆን የተሠራውም የአንደኛው ተጠሪ ይዞታ በሆነ ቦታ ላይ ነው፡፡ በአመልካች የተዘረዘረው የቤት ዕቃም የለብንም በማለት ተከራክረው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ከሣሽም ቤቱን የሠሩት ሟች አቶ ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኮል መሆናቸውን ያስረዱልኛል ያሉዋቸውን ምስክሮች አቅርበው ያሰሙ ሲሆን ተጠሪዎችም በበኩላቸው ቤቱን የሠሩት እነሱ መሆናቸውንና ቤቱ የተሠራውም በነሱ ይዞታ መሬት ላይ መሆኑን ያስረዱልናል የሚሏቸውን ምስክሮች አቅርበው አስምተዋል፡፡ የመሬቱ ይዞታ የነሱ መሆኑን ለማሳየትም ከመርጠ ለማርያም ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት የተላከ የጽሑፍ ማስረጃና አንደኛው ተጠሪ የከተማ ቦታ ኪራይ የከፈሉበትን ደረሰኝ አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተና ያቀረቡትን ማስረጃ ከሰማ በኋላ እስከ 1998 ዓ.ም የመሬቱን ግብር የከፈለው አንደኛው ተጠሪ

---

[535] በሰበር መዝገብ ቁጥር 44221 መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ

መሆኑን የመርጠ ለማርያም ከተማ ማዘጋጃ ቤት የገለጸ ሲሆን ከሣሽ ያቀረበችው ማስረጃ ግን የሰው ምስክር ነው። የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ደግሞ በሰው ማስረጃ ማስረዳት አግባብነት ያለው ባለመሆኑ ወ/ሮ እባቡ ቸኩልና ህፃን ዘላለም ተመስገን በቤቱ ላይ መብት የላቸውም የቤቱን ዕቃ በተመለከተ ግን ተጠሪዎች ለአመልካች በዓይነት ወይም ብር 3500.00(ሶስት ሽህ አምስት መቶ) ይክፈሉ በማለት ወሰነ።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቀረበች። ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም ተጠሪን አስቀርቦ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የቦታው ባለይዞታዎች ተጠሪዎች ቢሆኑም ቤቱን የሠሩት በተጠሪዎች ፈቃድ አቶ ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኩል መሆናቸው በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ የቤቱ ባለሀብቶች ወ/ሮ እባቡ ቸኩልና ህፃን ዘላለም ናቸው በማለት ወሰነ።

ተጠሪዎችም በበኩላቸው የይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለው በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቀረቡ። የክልሉ ሰበር ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አቶ ተመስገን ዳኘ ቤት የሠራው አንደኛው ተጠሪ የይዞታ ቦታቸውን ስለሰጡት ነው የተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ስምምነት በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723 የተደነገገውን ማሟላት የሚገባው ሆኖ ስለ አመልካቾች ይህን ፎርም ማሟላታቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም። በሌላ በኩል ተጠሪዎች ግን በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1195(1) በተደነገገው መሠረት ያስረዱ ሲሆን አመልካቾች ይህን ማስረጃ ለማፍረስ ያቀረቡት የሰው ምስክር በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቤቱ የአመልካቾች ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ የቤቱ ባለቤቶች ተጠሪዎች ናቸው በማለት ወሰነ።

አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ ተጠሪ ልጃቸው አቶ ተመስገን ዳኘ በይዞታ መሬታቸው ላይ ቤት እንዲሠራ የፈቀዱትና የተስማሙት በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723 በተደነገገው መሠረት አይደለም፤ ከዚህም በተጨማሪ ቤቱን የሠሩት ሟች ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኩል መሆናቸውን በሰው ምስክር ማስረዳታቸው ተገቢነት የለውም በማለት የቤቱን ባለቤትነት ለተጠሪዎች እንዲሰጥ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቀረቡ።

ተጠሪዎችም በበኩላቸው አንደኛ ተጠሪ ለሟች ተመስገን ዳኘ ክርክር የተነሳበትን ቤት እንዲሠራ ቦታ በስጦታ የሰጡ መሆናቸው በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723 ድንጋጌ መሠረት መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በከሣሾች በኩል አልቀረበም። ከዚህም በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ ባዶ ቦታ የመንግሥት በመሆኑ ስጦታ ተሰጥቷል ቢባል እንኳ ፈራሽ ነው በማለት ተከራክረዋል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ "ክርክር የተነሳበት ቤት ባለሀብት ማን ነው?" የሚለውን ጭብጥ በመያዝ አመልካችና ተጠሪዎች ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች ተቀባይነት አግባብ ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ውሳኔ ሰጥቷል።

የሰበር ችሎቱ ውሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት ተጠሪዎች በሚመለከተው የመንግሥት አካል በሕጋዊ መንገድ የቤት መሥሪያ ቦታ የተሰጣቸው መሆኑን የመርጠ ሰማርያም ከተማ ማዘጋጃ ቤት በፃፈው ደብዳቤና አንደኛው ተጠሪ ባቀረቡዋቸው የቦታ ግብር ደረሰኞች ተገጋግጧል። ሆኖም ተጠሪዎች ያቀረቡዋቸው እነዚህ የጽሑፍ ማስረጃዎች በፌዴራል ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) መሠረት ባለሀብት ከሆነው መንግሥትና ሕዝብ የኪራይ ክፍያ እየከፈሉ ቦታውን ለቤት መሥሪያነት፣ እንዲጠቀሙበት በይዞታነት የተሰጣቸው መሆኑንና ባለይዞታዎችም በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 40 (7) መሠረት መሬቱን የመጠቀም፣ በመሬቱ ላይ ቋሚ ማሻሻያ ለማድረግ፣ የማይንቀሳቀስ ሐብት ለማፍራትና በሚያፈሩት ሐብት ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ያላቸው መሆኑን የሚያስረዱና በአጠቃላይም በመሬቱ ላይ የባለይዞታነትና የመጠቀም መብት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው ካለ በኋላ እነዚህ በተጠሪዎች የቀረቡ ሰነዶች ተጠሪዎች በመሬቱ ላይ ያላቸውን የይዞታ መብት የሚያረጋግጡ እንጂ ተጠሪዎች በተሰጣቸው ቦታ ላይ የተሠራው ቤት የእነሱ መሆኑን የሚያረጋግጡ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት አይደሉም በማለት አብራርቷል።

በዚህ ማብራሪያ ላይ በመመሥረትም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪዎች ያቀረቡት ሰነድ በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1195(1) መሠረት የቤቱ ባለሀብት መሆናቸውን በአጥጋቢ ሁኔታ ያስረዳል በማለት የሰጠው ውሳኔ የመሬት ይዞታና ተጠቃሚነትን በማስረዳትና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን በማስረዳት መካከል ያለውን ልዩነት ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተችቷል።

ሰበር ችሎቱ በመቀጠልም ተጠሪዎች ቤቱ የተሠራበት መሬት ባለይዞታ መሆናቸው ተረጋግጧል። ሆኖም አንድ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው በይዞታው ላይ ሌላ ሰው ቤት እንዲሠራ የፈቀደ እንደሆነና ፈቃድ የተሰጠው ሰውም በሌላ ሰው የይዞታ መሬት ላይ ባገኘው ፈቃድ መሠረት ቤት የሠራ እንደሆነ የቤቱ ባለሀብት በባለይዞታው ፈቃድና ስምምነት ቤቱን (ሕንፃውን) የሠራው ሰው እንደሆነ በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179 (1) ተደንግጓል። በዚህ ጉዳይ የመሬቱ ባለይዞታዎች ተጠሪዎች ቢሆኑም አንደኛው ተጠሪ ሚች ልጃቸው ተመስገን ዳኘና ባለቤቱ ወ/ሮ እሳቡ ቸኮል በይዞታ መሬታቸው ላይ ቤት እንዲሠሩ በሰጡት ፈቃድና ስምምነት መሠረት ክርክር የተነሳበትን ቤት የሠሩ መሆኑን በሰው ምስክር አስረድተዋል በማለት አብራርቷል። በማያያዝም አንድ ሰው የአንድ ንብረት ባለሀብት የሚሆነው በገንዘቡ፣ በጉልበቱ ወይም በፈጠራ ችሎታው ያፈራው መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 40 (2)

የተደነገገ ሲሆን ተጠሪዎች ግን የመሬቱ ባለይዞታ ከመሆናቸው በስተቀር ቤቱን በገንዘባቸው ወይም በጉልበታቸው የሠሩት ለመሆኑ አላስረዱም ብሏል።

በዚህም መሠረት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ ተጠሪ ሚች ልጃቸው ተመስገን ዳኘ በይዞታ ቦታቸው ላይ ቤት እንዲሠራ መስማማታቸውን የሚያረጋግጥ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው ወይም በፍ/ቤት መዝገብ ሹም ፊት የተደረገና በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723(1) መሠረት የተደረገ ውል አልቀረበም በማለት የሰጠው ትርጉም ስህተት ያለበት ነው። ምክንያቱም አ/ድ ሰው በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179(1) መሠረት ባለ ይዞታው ሳይቃወም ወይም በባለይዞታው ፈቃድና ስምምነት የሌላ ሰው ይዞታ በሆነ መሬት ላይ ቤት የገነባ መሆኑን በማናቸውም ተአማኒነትና ክብደት ባለው ማስረጃ ለማስረዳት ይችላል በማለት አብራርቷል።
ከላይ የተነሱትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግም ሰበር ችሎቱ በማጠቃለያው የቦታው ባለይዞታዎች ተጠሪዎች መሆናቸው ለሰር ፍ/ቤት በቀረበው ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ቤቱን የሠሩት ደግሞ በተጠሪዎቹ ፈቃድና ስምምነት ሚች አቶ ተመስገን ዳኘና ባለቤቱ ወ/ሮ እባቡ ቸኮል መሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል ካለ በኋላ በዚህም ምክንያት በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179(1) መሠረት የቤቱ ባለሀብቶች ሚች አቶ ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኮል ናቸው። ይህም በመሆኑ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ከላይ የተገለፁትን የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የቤቱ ባለቤት የመሬቱ ባለይዞታዎች የሆኑት ተጠሪዎች ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሯል፤ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል በማለት ወስነ።

III. ትችት፣
1/ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርበው ውሳኔ የተሰጠባቸው ሁለቱም ጉዳዮች የመሬቱ ባለመብትነት የአንድ ሰው ሆኖ በመሬቱ ላይ የተገነባውን ቤት የሠራው ግን በመሬቱ ላይ መብት ያልነበረው ሌላ ሰው በሚሆንበት ጊዜ የቤቱ ባለቤት የሚሆነው ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ መልስ የሚመለከቱ ናቸው። ይህ ማለት ደግሞ ሁለት የተለያዩ መሬትን የሚመለከቱ መብቶች ተገናኝተው አንድ ንብረት እንዲፈራ በሚያደርጉበት ጊዜ የባለቤትነት ጥያቄው የሚፈታው በምን ሁኔታ ነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ እንደማለት ነው።

የሰበር ችሎቱ ውሳኔ በሰጠባቸው እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ቤቶች የተሠሩት የሌላ ሰው ይዞታ በሆነ መሬት ላይ የመሬቱ ይዞታ መብት ባልነበራቸው ሰዎች እንደሆነ በበቂ ሁኔታ መረጋገጡን ከችሎቱ ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል። ችሎቱ ይህን ካረጋገጠ በኋላ ቀጥሎ በጥልቀት የመረመረው የሌላ ሰው ይዞታ በሆነ መሬት ላይ ቤቶች የተሠሩት ባለይዞታዎች ፈቅደው ነው ወይስ ሳይፈቅዱ የሚለውን ጥያቄ ነው። ይህን ጥያቄ ለመመለስ ጉዳዩን ለመመርመር ትኩረት የሰጠበት ምክንያት ደግሞ የጥያቄው መልስ አንዱ ወይም ሌላው መሆን የቤቱ ባለቤትነት ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ወይም ሌላው በመሆን እንዲወሰን ለማድረግ

በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ በግልጽ የተደነገገ መሆኑን በውል በመገንዘብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ደግሞ በሌላ ሰው መሬት ላይ ቤት በሚሠራበት ጊዜ የቤቱ ባለቤት ማን እንደሆነ ለመወሰን የሚያስችሉ ሁለት ሁኔታዎችን በግልጽ አስቀምጧል። እነዚህም አንደኛ የመሬቱ ባለቤት ቤቱ በመሬቱ ላይ እንዳይሠራ እየተቃወመ ከተሠራ የቤቱ ባለቤት የመሬቱ ባለቤት ይሆናል።[536]

ሁለተኛ የመሬቱ ባለቤት ቤቱ በመሬቱ ላይ ሲሠራ ተቃውሞ ሳያነሳ ከተሠራ የቤቱ ባለቤት ቤቱን የሠራው ሰው ይሆናል[537] የሚሉ ናቸው። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚኖርብን በይዞታ መሬት ላይ ሌላ ሰው ቤት ሲሠራ ተቃውሞ አለማንሳትና በይዞታ መሬት ላይ ሌላ ሰው ቤት እንዲሠራ መፍቀድ የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ነው። ከዚህም በተጨማሪ መጤን ያለበት ጉዳይ በመሬቱ ባለይዞታ ፈቃድ አንድ ሰው ቤት በሚሠራበት ጊዜ የቤቱ ባለቤት ማን ይሆናል የሚለውን ጉዳይ የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ከላይ በተመለከትናቸው አንቀጾች ያልደነገገ መሆኑን ነው።

ሕጉ ይህን ያልደነገገበት ምክንያት ደግሞ የድንጋጌዎቹ ዓላማ በባለ መሬቱና ቤቱን በሠራው ሰው መካከል ግልጽ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ ለሚፈጠረው የንብረት መብት አሻሚነት መፍትሄ መስጠት በመሆኑ ነው። ለምን ቢባል የመሬቱ ባለይዞታ ፈቅዶ ቤቱ ከተሠራና በስምምነቱ ባለይዞታው በቤቱ ላይ መብት እንደሚኖረው ካልገለፀ የቤቱ ባለቤት ቤቱን የሠራው ሰው እንዲሆን የተስማማ በመሆኑ የቤቱን ባለቤትነት ለመወሰን ወሳኙ ስምምነታቸው ስለሆነ የሕጉን ጣልቃገብነት የሚጠይቅ ጉዳይ ባለመኖሩ ነው። እዚህም ላይ መገንዘብ ያለብን ባለመሬቱ ሳይቃወም አንድ ሰው በሌላ ሰው ይዞታ መሬት ላይ ቤት ሲሠራም ሆነ በመሬቱ ባለይዞታ ስምምነት ቤት ሲሠራ በሁለቱም ሁኔታዎች የቤቱ ባለቤት የሚሆነው ቤቱን የሠራው ሰው ነው ያልን ቢሆንም በመካከላቸው መሠረታዊ የመብት ልዩነት ያለ መሆኑንም ጭምር ነው ምክንያቱም ባለይዞታው ሳይቃወም ቤቱ በተሠራ ጊዜ የሠራው ሰው የቤቱ ባለቤት ቢሆንም የመሬቱ

---

[536] አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሕግም የመሬት ባለቤትነት ባይኖርም የመሬት ባለይዞታው ይዞታውን ያለመነጠቅ መብቱ የተጠበቀ በመሆኑ እንዲይሠራ እየተቃወመ በይዞታው ላይ ሌላ ሰው ቤት ከሠራ የቤቱ ባለቤት እሱ ይሆናል። ምክንያቱም በመሬቱ ላይ ቤቱ ከተሠራ በኋላም የመሬት ባለይዞታነቱ እንደተጠበቀ የሚቀጥል በመሆኑ ነው።

[537] የመሬቱ ባለይዞታ ተቃውሞ ሳያነሳ በሌላ ሰው መሬት ላይ ቤት ሲሠራበት የሚችለው ባለይዞታው የቤቱን መሠራት እያወቀ ወይም ሳያውቅ ሊሆን ይችላል። በሰው ይዞታ ላይ ቤቱን የሠራው ሰውም ቤቱን የሠራው የመሬቱ ይዞታ የሌላ ሰው መሆኑን እያወቀ ወይም ሳያውቅ መብት ያለው መስሎት ሊሆን ይችላል። እነዚህን ሁኔታዎች በማገናዘብም ሕጉ ቤቱ የተሠራው የመሬቱ ባለይዞታ ሳይቃወም ከሆነ የመሬቱ ይዞታ በባለይዞታው እጅ ይቆያል፤ የቤቱ ባለቤትነት ግን የሠራው ሰው ይሆናል በማለት ሁለቱም መብቶች ተጣጥመው እንደሚቆዩ በሚያሳይ ሁኔታ ከደነገገ በኋላ የመሬት ይዞታውና የቤቱ ባለቤትነት ተጣጥመው መቀጠል ካልቻሉ ግን ቤቱን የሠራው ሰው ለቤቱ መሥሪያ ያወጣውን ወጭ ተክሶ የመሬት ባለይዞታው በመሬቱ ላይ ያለውን መብት የቤቱን ባለቤትነት ጨምሮ በተሟላ ሁኔታ እንዲገለገልበት በማስቻል ይደነግጋል።

ባለይዞታ በፈለገ ጊዜ በሕጉ መሠረት የቤቱን ዋጋ በመክፈል የቤቱ ባለቤት መሆን የሚችል ሲሆን[538] በባለይዞታው ፈቃድ ቤት ከተሠራ ግን ቤቱን የሠራው ሰው የቤት ባለቤትነት መብት በማንኛውም ጊዜ በመሬቱ ባለይዞታ ሊነካ የማይችል በመሆኑ ነው።[539]

የሰበር ችሎቱ በቀረቡለት ጉዳዮች የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረቡትን ማስረጃዎች ተመልክቶ አመልካቾች በሌላ ሰው ይዞታ መሬት ላይ ቤት የሠሩት በባለይዞታዎች ፈቃድ መሆኑ መረጋገጡን በውሳኔው ገልጿል። ችሎቱ ከቀረቡት ክርክሮችና ማስረጃዎች ያረጋገጠው ይህ ከሆነ ቀጥሎ የምንመለከተው በጉዳዮቹ ላይ የተሰጡት ውሳኔዎችና ለውሳኔዎቹ የተሰጡት ምክንያቶች አግባብ ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች አንፃር ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ነው።

የሰበር ችሎቱ እነ ወ/ሮ ዳላሽ ባይነሰኝና አቶ ገዛኸኝ አድነው ተከራካሪ በሆኑበት በመጀመሪያው ጉዳይ ተከሳሹ አቶ ገዛኸኝ አድነው የቤቱ ባለቤት ናቸው ቤቱንም የመሬቱ ባለይዞታዎች ለሆኑት ከሳሾች ለእነ ወ/ሮ ዳላሽ ሊመልሱ አይገባም በማለት የወሰነው፦

> በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1179(2) በተደነገገው መሠረት በሌላ ሰው መሬት ላይ ቤት የሠራ ሰው የሕንፃውን ግምት ተቀብሎ ሕንፃውን ለባለመሬቱ ለማስረከብ የሚገደደው ባለመሬቱ ሳይቃወም ሕንፃውን የሠራ በሚሆንበት ጊዜ ነው። በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ቤቱን የሠራው የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የሌሎች ተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት ሟች አቶ አድነው አወቀ ሳይቃወሙ በቀሩበት ሁኔታ ሳይሆን ይልቁንም ፈቃዳቸውን ሰጥተዋል በተባለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ ሕጉ በወጣበት ዘመን ግለሰቦቹ በመሬት ባለቤትነት ረገድ መብት የነበራቸው ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገመንግሥት መሬት በግል ባለቤትነት መያዙ ቀርቶ የመንግሥትና የሕዝብ የተደረገ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች የመሬቱ ባለቤት ስለሆኑ አመልካች በመሬቱ ላይ የሠራውን ቤት የዋጋ ግምቱን 1/4 ከተጠሪዎች ተቀብለው ቤቱን ያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ በዚህ ረገድ ከነበረው ሕግም ሆነ ከሕገመንግሥታችን ጋር የተጣጣመ ሆኖ

---

[538] በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ቤት የሠራው ሰው በመሬቱ ላይ ምንም መብት እንደሌለው እያወቀ ከሠራው ጥፋተኛ ቢሆንም የመሬቱ ባለይዞታም የቤቱን መሠራት ካልተቃወመ ለተፈፀመው ጥፋት አስተዋጽኦ አድርጓል። ስለዚህም ሕጉ የመሬት ባልይዞታው ባለመቃወሙ የቤቱን ባለቤትነና ለሠራው ሰው የሰጠ ሲሆን ቤቱን የሠራው ሰውም በመሬቱ ላይ መብት እንደሌለው እያወቀ ቤቱን ስለሠራው የቤቱ ዋጋ 1/4 ብቻ ተከፍሎት ባለሀብትነቱን እንዲለቅ በመወሰን አስታራቂ በሆነ ሁኔታ ደንግጓል።

[539] አንድ የመሬቱ ባለይዞታ በይዞታው ላይ ሌላ ሰው ቤት እንዲሠራ ከፈቀደ በመሬቱ ላይ ያለው መብት ለሌላ ሰው እንዲተላለፍ ተስማምቷል ማለት ስለሆነ በተሠራው ቤት ላይ ምንም ዓይነት መብት ሊኖረው አይችልም።

አልተገኘም። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል የሚል ምክንያት በመስጠት ነው።
ችሎቱም ከላይ በትክክል እንዳተተውም የሰበር አመልካቹ ቤቱን ሠሩ የተባለው በመሬቱ ባለይዞታ ፈቃድ እንጅ በዝምታ ድርጊቱን ሳይቃወሙ በቀሩበት ሁኔታ አይደለም። ፍ/ቤቱ ይህን እንደ መነሻ መጥቀሱ ደግሞ ሳይቃወሙ መቅረትና ፈቃድ መስጠት ውጤታቸው የተለያየ መሆኑን ለማመልከትና ቤቱ የተሠራው የመሬቱ ባለይዞታ ሳይቃወም በቀረበት ሁኔታ ቢሆን ኖሮ እንደነገሩ ሁኔታ የቤቱን ሙሉ ዋጋ ወይም የዋጋውን 1/4 ከፍሎ ለመውሰድ ሕጉ ይፈቅድለታል የሚለውን መቀበሉን ለመገመት ያስችላል። ይህ ደግሞ ከሕጉ ጋር የሚጣጣም ውሳኔ ነው።

በዚህ መነሻነትም ችሎቱ ለውሳኔው መሠረት አድርጉ የጠቀሰው የመሬቱ ባለይዛታ ፈቅደው ቤቱ መሠራቱንና በአሁኑ ጊዜ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት ነው የሚሉትን ሁለት ምክንያቶች ነው።በእርግጥም የመሬት ባለይዞታው ፈቅዶለት አንድ ሰው ቤት ከሠራ የመሬቱ ባለይዞታ ቤቱ እንዲመለስለት ለመጠየቅ አይችልም በማለት ችሎቱ በአንደኛ ምክንያትነት ያስቀመጠው ከሕጉ ጋር የሚጣጣም ነው። ምክንያቱም ብበታች ፍ/ቤት የተጠቀሰው የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179 የመሬቱ ባለይዞታ ተቃውሞ ሳያነሳ ቤቱ በተሠራበት ጊዜ የሚነሳውን የቤት ባለቤትነት ጥያቄ የሚመለከት እንጅ ባለይዞታው ፈቅዶ ቤት በሚሠራበት ጊዜ የሚነሳ የቤት ይገባኛል ጥያቄን የሚመለከት ድንጋጌ ባለመሆኑ ነው።

ይሁን እንጅ የመሬቱ ባለይዞታዎች በይዞታቸው ላይ የተሠራውን ቤት ለማስመለስ መብት የማይኖራቸው በአሁኑ ጊዜ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት ስለሆነ ነው በማለት ችሎቱ በሁለተኛ ምክንያትነት የጠቀሰው ነጥብ ግን በተለያዩ ምክንያቶች ትክክል ነው ለማለት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም አንደኛ የመሬት ባለይዞታው ፈቅዶ በመሬቱ ላይ ቤት ከተሠራ ቤቱ ይመለስልኝ ብሎ መጠየቅ የማይችል ለመሆኑ ፈቃዱን መስጠቱ ብቻ በቂ ነው። ፈቃድ ሰጥቶ በይዞታ መሬት ላይ ቤት እንዲሠራ ማድረግ ሳይቃወሙ ከተሠራበት ሁኔታ የሚለይ በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179 ስር የሚወድቅም አይደለም የሚለው ምክንያት በቂ ሆኖ ሳለ አጠቃላይ የሆነ የሕገመንግሥት ድንጋጌ በተጨማሪ ምክንያትነት መጥቀሱ አስፈላጊ መስሎ አይታይም። ሁለተኛም ሁለቱ ምክንያቶች ተደበላልቀው መቅረባቸው ችሎቱ ለውሳኔው የሰጠውን ምክንያት በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ በቀላሉ ተረድቶ ከውሳኔው ትምህርት ለማግኘት አስቸጋሪ አድርጉታል። በሶስተኛ ደረጃም የመሬት ባለቤትነት የመንግሥትና የህዝብ ሀብት መሆን ባለይዞታዎች በባዶ መሬታቸው ላይ ምንም መብት የላቸውም ማለትም አይደለም።

ባለይዞታው ከባለቤት በተለየ ቦታውን ማድረግ የማይችለው ነገር መሸጥ ነው።በአሁኑ ሁኔታም የመሬቱ ባለይዞታ እየተቃወመ በመሬቱ ላይ ሌላ ሰው ቤት ቢሠራበት በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1178 መሠረት የቤቱ ባለቤት እሱ ይሆናል። እንዲሁም በይዞታ መሬቱ ላይ ሌላ ሰው ቤት ሲሠራ ሳይቃወም

በቀረበትም ሁኔታ እንደዚሁ በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179(2) በተደነገገው መሠረት እንደነገሩ ሁኔታ ቤቱ የተሠራበትን ዋጋ ወይም 1/4ኛውን ከፍሎ ቤቱን የማስመለስ መብት አለው። ምክንያቱም የመሬት ባለቤትነትም ሆነ የመሬት ይዞታ መብት ሁለቱም የንብረት መብቶች በመሆናቸው ነው።

በኢትዮጵያ ሕጐች መሠረት መሬትን በተመለከተ የይዞታ መብትና የባለቤትነት መብት ያላቸው መሠረታዊ ልዩነትም መሸጥ የመቻልና ያለመቻል ጉዳይ ነው። የፍትሐብሔር ሕጉም መተርጐም ያለበት በአሁኑ ጊዜ የመሬት ይዞታ እንጂ ባለቤትነት ስለሌለ ድንጋጌው አግባብነት የለውም በሚል ሳይሆን እንደ አግባቡ (Mutatis mutandis) ለይዞታም ተፈፃሚነት እንዳለው ተደርጐ ነው።

ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ችሎቱ የመሬቱ ባለይዞታ ቤቱ ሊመለስለት የማይገባው የመሬት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ እንጅ የሱ ባለመሆኑም ጭምር ነው በማለት የሰጠው ምክንያት በአንድ በኩልም ትክክል ያልሆነ በሌላ በኩልም በተጠቀሰበት ሁኔታ እንኳ ግልጽ ያልሆነና የሚያምታታ ነው። ስለዚህም የሰበር ችሎቱ የበታች ፍ/ቤት ውሳኔ "ከነበረው ሕግ (ከፍ/ብ/ሕጉ) ጋር የተጣጣመ አይደለም" በማለት የሰጠው ምክንያት ትክክል ሆኖ ሳለ "ከሕገመንግሥታችን ጋርም የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም" በማለት የሰጠው ትችት ግን ግልጽ ያልሆነ በቂ ምክንያት ያልተሰጠበትና የተሳሳተ መስሎ ይታየኛል።
2/ የሰበር ችሎቱ እነ ወ/ሮ እባቡ ደሴና ቂሰ ገበዝ ዳኘ ካሣ ተከራካሪ በሆኑበት ሁለተኛው ጉዳይም የቤቱ ባለቤቶች ቤቱን የሠሩት ሚች አቶ ተመስገን ዳኘና ባለቤታቸው የነበሩት ወ/ሮ እባቡ ቸኮል ናቸው በማለት የወሰነው፡-

> የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው በይዞታው ላይ ሌላ ሰው ቤት እንዲሠራ የፈቀደ እንደሆነና አንድ ሰው በሌላ ሰው ይዞታ ላይ በባለ ይዞታው ፈቃድ ቤት የሠራ መሆኑ ከተረጋገጠ የቤቱ ባለሐብት በባለይዞታው ፈቃድና ስምምነት ሕንፃውን የሠራው ሰው እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179(2) ተደንግጓል

በማለት ካተተ በኋላ የመሬቱ ባለይዞታዎች ተጠሪዎች ቢሆኑም በይዞታ መሬታቸው ላይ አመልካቾች ቤት እንዲሠሩበት በሠጡት ፈቃድና ስምምነት መሠረት ቤቱን የሠሩት አቶ ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኮል መሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል የሚል ማብራሪያ በመስጠት ነው። ከዚህ በመቀጠልም አንድ ሰው የአንድ ንብረት ባለሐብት የሚሆነው በገንዘብ በጉልበቱ ወይም በፈጠራ ችሎታው ያፈራው መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 40(2) ተደንግጓል። ተጠሪዎች ደግሞ የመሬቱ ሕጋዊ ባለይዞትዎች ከመሆናቸው በስተቀር ቤቱን በገንዘባቸው ወይም በጉልበታቸው የሠሩት መሆኑን አላስረዱም በማለት አትቷል። በዚህ ላይ በመመሥረትም፡-

> የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ ተጠሪ ሚች ልጃቸው ተመስገን ዳኘ በቦታው ላይ ቤት እንዲሠሩ የተስማሙ ለመሆናቸው ውል ለመዋዋል ስልጣን ባለው ወይም በፍ/ቤት መዝገብ ሹም ፊት የተደረገና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723(1) መሠረት የተደረገ ውል አልቀረበም

በማለት የሰጠው ትርጉም ስህተት ያለበት ነው። ምክንያቱም በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1179(1) መሠረት አንድ ሰው ባለይዞታው ሳይቃወም ወይም በባለይዞታው ፈቃድና ስምምነት በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ቤት የገነባ መሆኑን በማናቸውም ተዓማኒነትና ክብደት ባለው ማስረጃ ማስረዳት የሚችል በመሆኑ ነው በማለት የውሳኔውን ምክንያት አብራርቷል።

ሰበር ችሎቱ በማጠቃለያውም ክርክር የተነሳበትን ቤት በተጠሪዎች ቦታ ላይ በተጠሪዎች ፈቃድና ስምምነት የሠሩት ሟች ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኮል መሆናቸው ለሰር ፍ/ቤት በቀረበ ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1179(1) መሠረት የቤቱ ባለሐብቶች ሟች ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኮል ናቸው በማለት ደምድሟል።

የሰበር ችሎቱ የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ ለመሻር የሰጣቸው ምክንያቶች ሶስት ናቸው። እነርሱም፦

1. አንድ ሰው በሌላ ሰው ይዞታ መሬት ላይ በባለ ይዞታው ፈቃድ ቤት የሠራ እንደሆነ በባለይዞታው ፈቃድ መሥራቱን በማናቸውም ተአማኒነትና ክብደት ባለው ማስረጃ ማስረዳት ይችላል።
2. አንድ ሰው በሌላ ሰው ይዞታ መሬት ላይ በባለ ይዞታው ፈቃድ ቤት የሠራ እንደሆነ የቤቱ ባለቤት ቤቱን የሠራው ሰው እንደሚሆን በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ ር 1179(1) ተደንግጓል፣
3. አንድ ሰው የአንድ ንብረት ባለሐብት የሚሆነው በገንዘቡ፣ በጉልበቱ ወይም በፈጠራ ችሎታው ያፈራው ሲሆን በመሆኑና የመሬቱ ባለይዞታዎች ደግሞ ቤቱን በገንዘባቸው ወይም በጉልበታቸው ሥላልሠሩት ባለቤት ሊሆኑ አይችሉም የሚሉ ናቸው።

በእርግጥም በይዞታ መሬት ላይ ሌላ ሰው ቤት እንዲሠራ መፍቀድ የይዞታ መብትን ለማስተላለፍ የተደረገ ሙሉ ስምምነት ሳይሆን ቤቱ እንዲሠራ ብቻ መፍቀድ በመሆኑ ችሎቱም እንዳለው በማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ማስረዳት kፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723(1) ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ አይሆንም። ስለዚህም ችሎቱ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰጠው ምክንያትም ሆነ የሰጠው ውሳኔ ትክክል ይመስለኛል።

በባለይዞታው ፈቃድ የተሠራ ቤት ባለሐብት ቤቱን የሠራው ሰው እንደሚሆን በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179(1) ተደንግጓል በማለት ችሎቱ የጠቀሰው ግን በአንድ በኩል በባለይዞታው ተቃውሞ ሳይቀርብ ቤት መሥራትንና በባለይዞታው ፈቃድ ቤት መሥራትን አንድ አድርጐ መውሰድ ሲሆን በሌላ በኩልም አንቀጹ የማይለውን እንደሚል አድርጐ በመውሰድ ሌላ ሕግ እንደማውጣት ይሆናል። ምክንያቱም አንቀጽ 1179(1) የሚደነግገው የመሬቱ ባለይዞታ ሳይቃወም ሌላ ሰው በመሬቱ ላይ ቤት በሚሠራበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ እንጅ ባለይዞታው ፈቃዱን በሰጠበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ አይደለም። ከዚህም በተጨማሪ ችሎቱ ቀደም ብሎ በተመለከትነው በእነ ወ/ሮ ዳሳሽና በአቶ ገዛኸኝ አድነው መካከል በተካሄደው ክርክር በሰጠው ውሳኔ አንቀጽ 1179(1) በባለይዞታው ፈቃድ ቤት በሚሠራበት

ጊዜ ያለውን ሁኔታ የሚመለከት አይደለም በማለት ከሰጠው ምክንያት ጋርም የሚቃረን ይሆናል። ስለዚህም ችሎቱ የቤቱ ባለቤቶች ቤቱን የሠሩት አቶ ተመስገን ዳኘና ወ/ሮ እባቡ ቸኮል እንደሆኑ መወሰኑ ትክክል ቢሆንም ለዚህ ውሳኔ አንዱ ምክንያት የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1179(1) ይህንን የሚደነግግ በመሆኑ ነው ማለቱ ግን የተሳሳተ ነው። ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ቤቱን የሠሩት ሰዎች የቤቱ ባለሐብቶች የሚሆኑት በአንቀጽ 1179(1) መሠረት ሳይሆን የመሬቱ ባለይዞታ በይዞታቸው ላይ ቤት እንዲሠራ የሰጡት ፈቃድ ቤቱን የሠራው ሰው የቤቱ ባለቤት እንዲሆን መስማማታቸውን የሚያረጋግጥ በመሆኑ ነው።
ችሎቱ በሶስተኛ ደረጃ የመሬት ባለይዞታዎች በመሬታቸው ላይ የተሠራው ቤት ባለሐብቶች የማይሆኑት በፌዴራል ሕገመንግሥት በተደነገገው መሠረት ቤቱን በገንዘባቸው ወይም በጉልበታቸው የሠሩት ባለመሆናቸው ነው በማለት የሰጠው ምክንያት የመሬት ይዞታ መብት ራሱን የቻለ የንብረት መብት መሆኑን የዘነጋ ትችት ነው። ምክንያቱም የመሬት ይዞታ መብት አለመነካት ወይም ከይዞታ አለመፈናቀል መብት በኢትዮጵያ ሕግ የተከበረ ከመሆኑም በላይ በአንድ ሰው ይዞታ ላይ ባለይዞታው እየተቃወመ በሌላ ሰው ቤት ቢሠራ በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1178 ቡተደነገገው መሠረት የመሬቱ ባለይዞታ የቤቱ ባለቤት የሚሆን መሆኑን የሚሸር ሕግ ስለሌለ ነው።

ስለዚህም የሰበር ችሎቱ አንድ የመሬት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ የተሠራውን ቤት ራሱ በገንዘቡ ወይም በጉልበቱ ካልሠራው የቤቱ ባለሐብት ሊሆን ስለማይችል ተጠሪዎች ቂስ ገበዝ ዳኘ ካሣና ወ/ሮ ምትኬ አየለ የቤቱ ባለሐብት ሊሆኑ አይችሉም በማለት በተጨማሪ ምክንያትነት የጠቀሰው አንድም ለጉዳዩ አግባብ የሌለው ሁለተኛም የተሳሳተ ምክንያት ሆኖ ታይቶኛል፡

ማጠቃለያ

የተከበረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በዚህ ትችት በተመለከትናቸው ሁለት ጉዳዮች የተነተናቸው ምክንያቶች አንዳንዶቹ ተገቢ የሆኑና የሰጣቸው ውሳኔዎችም ትክክል

ቢሆኑም፡-

1. አንድ የመሬት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ሌላ ሰው ቤት እንዲሠራ ፈቃዱን ሰጥቶ ቤቱ በተሠራበት ጊዜና ተቃውሞ ሳያነሳ በተሠራበት ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነውን የሕግ ድንጋጌ በተመለከተ ያለው አቋም ግልጽነት እንደሌለውና አንድ ወጥ እንዲልሆነ ተመልክተናል።
2. አንድ ሰው በባዶ መሬቱ ላይ መብት ሊኖረው የሚችለው የመሬት ባለቤትነት ባለበት ሁኔታ እንጅ መሬት የመንግሥትና የህዝብ ሐብት በሆነበት እንደኢትዮጵያ ባለ ሁኔታ የመሬት ባለይዞታዎች በይዞታቸው ላይ ሌላ ሰው ቤት ቢሠራ እነሱ ሳይቃወሙ በተሠራው ቤት ላይ ምንም መብት አይኖራቸውም የሚል በቂ የሕግ ድጋፍ የሌለው አቋም እንዲሰው ተገንዝበናል።

በአንድ ሰው የመሬት ይዞታ ላይ ባለይዞታው ሳይቃወም ሌላ ሰው ቤት በሚሠራበት ጊዜ የቤቱ ባለቤትነት መወሰን ያለበት መሬት የግል በነበረበት ጊዜ በወጣው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ብቻ ሳይሆን "በገንዘብ ወይም በጉልበት ያልተፈራ ንብረት ባለሐብት መሆን አይቻልም" በሚለው የፌዴራል ሕገመንግሥቱ ድንጋጌ መሠረትም ነው የሚል በአጠቃላይ የተደነገገውን ለዝርዝር ጉዳይ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚሞክርና የመሬት ይዞታ መብትን አሳንሶ የሚያይ እምነት ያለው መሆኑን ተረድተናል።

አሁን ባለው የኢትዮጵያ የንብረት መብት ሕግ የመሬት ይዞታ መብትና የቤት ባለቤትነት መብት መሠረታዊ ልዩነት የይዞታ መብቱ በሽያጭ የማይተላለፍ መሆኑና የቤት ባለቤትነት መብት ግን በሽያጭ የሚተላለፍ መሆኑ ሆኖ ሳለ ችሎቱ ሁለቱን መብቶች እጅግ በማይገናኝ ሁኔታ የተለያዩ መሆናቸውን እንደሚያምን በሚያሳይ ሁኔታ በውሳኔው ማመልከቱን ተገንዝበናል።

ሦስተኛ ወገን መያዣው የኔ ነው በማለት በፍ/ቤት ክስ ሲያቀርብ መያዣው የመያዣ ሰጭው መሆኑን መያዣ ተቀባዩ ማስረዳት አለበት? የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 51001 በሰጠው ፍርድ ላይ የተሰጠ አስተያየት

ንጋቱ ተስፋዬ

መግቢያ

ተንቀሳቃሽ ንብረትን የሚመለከት የመያዣ ውል የሚተዳደረው በፍትሐ ብሔር ሕግ ከቁጥር 2825 እስከ 2874 ባሉት ድንጋጌዎች ነው። የመያዣ ውል ማለት አንድ ባለዕዳ ለባለገንዘቡ የገባውን ግዴታ እንደሚፈጽም ዋስትና እንዲሆን መያዣ ተብሎ የሚጠራውን ዕቃ ለባለገንዘቡ ለመስጠት የሚገደድበት ውል ነው።[540] በመያዣነት የሚሰጠው አንድ ተንቀሳቃሽ ንብረት ወይም በጠቅላላው ዕቃ ተብለው የሚጠሩ ተንቀሳቃሽ ነገሮች ወይም ተንቀሳቃሽ ንብረትን የሚመለከት የገንዘብ መብት ወይም ሌላ መብት ሊሆን ይችላል።[541] የመያዣው ውል ከአምስት መቶ ብር በላይ የሆነ ግዴታን የሚመለከት ከሆነ ውሉ በጽሑፍ ካልተደረገ አይጸናም።[542] እንዲሁም፣ ዋስትና የተሰጠበት ግዴታ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን በመያዣ ውሉ ካልተጠቀሰ ውሉ ፈራሽ ይሆናል።[543]

መያዣ ተቀባዩ ሊከፈለው የሚገባው ገንዘብ በሙሉ እስኪከፈለው ድረስ መያዣውን በራሱ ይዞታና ቁጥጥር ሥር አድርጎ የማቆየት መብት አለው።[544] የመያዣው ውል ለሦስተኛ ወገኖች መቃወሚያ እንዲሆን መያዣው በባለገንዘቡ ወይም ተዋዋዮቹ በመረጡት ሦስተኛ ሰው እጅ መቀመጥ ይኖርበታል።[545] በሕግ ተገልጾ ካልተፈቀደ በስተቀር የዕዳው መያዣ የሆነው ንብረት ከባለዕዳው እጅ ሳይወጣ በመያዣ እንደተሰጠ ሊቆጠር ስለማይችል መያዣው በባለዕዳው እጅ ይሆናል የሚል የመያዣ ውልም አይጸናም።[546] ሆኖም፣ ንብረቱ በባለዕዳው እጅ ቢሆንም መያዣ ተቀባዩ በንብረቱ ለማዘዝ የሚያስችሉና የንብረቱን ባለቤትነት

የጽሑፉ አቅራቢ የስቪሊንያ ባንክ የሕግ ማኅበረ ሲሆኑ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1972 የሕግ ባችለር ድግሪ (LLB)፣ ከዩሰ ዩኒቨርሲቲ በ1976 የሕግ ማስተርስ ድግሪ (LLM) ተቀብለዋል። ለበርካታ ዓመታትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስና በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ መምህርነት ሰንሰግለዋል።

[540] *የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2825። እንግሊዝኛው A contract of pledge is a contract whereby a debtor undertakes to deliver a thing, called the pledge, to his creditor as security for the performance of an obligation ይላል።* (**ማሳሰቢያ**፣ *ተለይቶ ካልተገለፀ በቀር፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ቁጥሮች በ1952 የወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ናቸው።*)

[541] ቁጥር 2829(1)። *እንግሊዝኛው The pledge may consist of a chattel, a totality of effects, a claim or another right relating to movable property ይላል።*

[542] ቁጥር 2828(2)

[543] ቁጥር 2828(1)

[544] ቁጥር 2846

[545] ቁጥር 2852 ስና 2831

[546] ቁጥር 2832(2)። በሸቀጥ መያዣነት ብድር ሲሰጥ ስበጻሪውና የሸቀጡ ባለቤት የመጋዘኑን ቁልፍ በጋራ የሚቆጣጠሩበት (dual control) ስሥራር ከሕጉ ጋር ስደስማማም። ምን ጊዜም ቢሆን መያዣው በባለገንዘቡ ወይም በሦስተኛ ሰው እጅ መሆን ስበበት።

የሚያሳዩ ሰነዶች በእጁ ካደረገ ንብረቱን በእጁ እንዳደረገ ይቆጠራል::[547] መያዣው በመያዣ ተቀባዩ ወይም መያዣ ሰጭውና መያዣ ተቀባዩ በመረጡት ሦስተኛ ሰው እጅ የሚገኝ ከሆነ መያዣ ተቀባዩ ከንብረቱ ሽያጭ ዋጋ ላይ ከሌሎች ባለገንዘቦች ቀድሞ የመቀበል መብት አለው::[548]

በመያዣ የተሰጠው ዕቃ የኔ ነው የሚል ሦስተኛ ወገን ሲነሳ ባለገንዘቡ መያዣውን የተቀበለው የባለቤትነት መብት ከሌለው ሰው ላይ ቢሆንም እንኳ የመያዣው ውል በሚሰጠው መብት ሊሠራበት እንደሚችል በሕግ ተደንግጓል::[549] መያዣ ተቀባዩ በዕቃው ላይ ያለውን የመያዣ መብት የሚያጣው መያዣ ሰጭው ዕቃውን በመያዣ ለመስጠት መብት እንደሌለው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲኖርበት መያዣውን በግዴለሽነት የተቀበለ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው::[550] ዕቃው የኔ ነው ባዩ ይህን ማስረዳት ካልቻለ ዕቃውን ከመያዣ ተቀባዩ ሊወስድ የሚችለው ዕቃው በመያዣ የተሰጠበትን ዕዳ ለባለገንዘቡ በመክፈል ብቻ ነው::[551]

የሚንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከተው የመያዣ ሕግ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ ቁጥሌን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም በሰ/መ/ቁ. 51001 ፍርድ የሰጠበትን ጉዳይ እናያለን:: በዚህ መዝገብ አመልካቹ አቢሲንያ ባንክ አ.ማ. ሲሆን፣[552] ተጠሪው አቶ ዘውዱ ነጋ ነበሩ:: ጉዳዩ በተጀመረበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት ተጠሪው ሲሆኑ፣ ተከሳሹ ፐርፍ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር (ከዚህ በኋላ ባጭሩ "ፐርፍ" የሚባለው) ነበር::

1. ፐርፍ ሰሊጥ እየገዛና ኢያስበጠረ ወደ ውጭ የሚልክ የንግድ ማኅበር ነው:: ፐርፍ ለዚህ ንግዱ ገንዘብ ስለአስፈለገው አመልካች ሰሊጥ በዋስትና እየያዘ ሳልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ብድር (credit facility) እንዲፈቅድለት ስለአመለከተ ጥቅምት 14 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገ ውል 2,500,000.00 ብር ብድር ተፈቀደለት:: ፐርፍ በዚህ ገንዘብ ለተወሰነ ጊዜ ከሠራ በኋላ የብድሩ መጠን ከፍ እንዲልለት አመለከተና መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገ ውል 500,000.00 ብር ተጨምሮለት የብድሩ መጠን ወደ 3,000,000.00 ብር ከፍ አለ:: በዚህ ገንዘብ እየሠራ ቆይቶ ጥሩ ውጤት ስለአገኘና የንግዱ መጠን እየጨመረ ስለሄደ ሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገ ሦስተኛ ውል 2,000,000.00 ብር ተጨምሮለት የብድሩ መጠን ወደ 5,000,000.00 ከፍ አለ:: ፐርፍ በዚህ

---

[547] ቁጥር 2830:: በመንገሥት ስካሰ የሚመዘገቡ ስንደ ሞተር ተሽከርካሪ ያሱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (ሲብሬ) ያሳቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች መደም ዕቃዎች በመጋዘን ሰመቀመጣቸው መደም በመርከብ ሰመጫናቸው መደም በጉዞ ላይ ሰመሆናቸው የሚገዉዜና በሰነዱ ጀርባ ላይ ሰመያዣ ተቀባዩ ስንዲሰጡ የተጻፈባቸው (endorse የተደረጉ) ስንደ warehouse certificates, bill of lading, or way bill የመሳሰሱ ሰነዶችን ስበዳሪው ከተቀበሰ ዕቃዎች በስበዳሪው ይዞታ ሥር ስንዳሆኑ ይቆጠራሱ:: ሞተር ተሽከርካሪዎችን በሚመሰክት ግን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (Title deed) ከመቀበሰ በተጨማሪ የመያዣ ውሱ በሚመሰክተው የመንገድ ትራንስፖርት መሥሪያ ቤት ስንዲመዘገብ ያስፈሰጋሱ::

[548] ቁጥር 2852(1) ስና 2857

[549] ቁጥር 2843:: የስንግዚዝኛው ቅጅ *The pledgee may exercise the right deriving from the contract of pledge notwithstanding that the pledge has been delivered to him by a person who was not authorized to dispose of it.* ይሳል::

[550] ቁጥር 2844(1)

[551] ቁጥር 2844(2)

[552] ዘክፍተኛው ፍ/ቤትና በመቀሳያ ፍ/ቤተ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ስቢሲንያ ባንክ በቅደም ተከተሱ የመቃወም ዕመዉልካች ስና ይግባኝ ባይ ሆኖ ተከራክሯል::

በተፈቀደለት ገንዘብ ሰሊጥ እየገዛና እያስበጠረ ወደ ውጭ በመላክ ጠቀም ያለ የውጭ ምንዛሪ አስገኝ። የሚቀርብለት የግዥ ጥያቄ እየበዛ ስለሄደም ተጨማሪ ብድር እንዲሰጠው አመልክቶ የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ/ም በተደረገ ውል 3,000,000 00 ብር ተጨምሮለት ጠቅላላው የብድር መጠን ወደ 8,000,000.00 ብር አደገ። ከላይ በተጠቀሱት አራቱም የብድር ውሎች ውስጥ ለተፈቀደው ብድር መያዣ የሚሆነው ሰሊጥ ዓይነትና ብዛት ተገልጿል።

1.1. መያዣ የሆነው ሰሊጥ ተበጥሮ ወደ ውጭ እስኪላክ ድረስ የሚቀመጠው ቃሊቲ አካባቢ በሚገኝ በናይል ቡና ላኪ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር (ከዚህ በኋላ ባጭሩ "አስቀማጩ" በሚባለው) መጋዘን ውስጥ ነበር። ሰሊጡ በዚህ መጋዘን እንዲቀመጥ አመልካች፣ ፐርፍ እና አስቀማጩ ጎዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም. የሦስትዮሽ ውል ተዋውለዋል።[553] በዚህ የሦስትዮሽ ውል፣

- ፐርፍ የሚገዛውን ሰሊጥ በአስቀማጩ መጋዘን ለማስቀመጥና ከአመልካች ለሚወሰደው ብድር በመያዣ ለመስጠት፤ እንዲሁም የመጋዘን ኪራይ ለአስቀማጩ ለመክፈልና ሰሊጡን አስበጥሮ ወደ ውጭ በሚልክበት ጊዜ የሰሊጡን ዋጋ በቅድሚያ ለአመልካች ለመክፈል ተስማምቷል።

- አስቀማጩም ፐርፍ ወደ መጋዘኑ ያስገባውን ሰሊጥ ብዛትና ዋጋ ገልጾ አመልካች ሳይፈቅድ ሰሊጡ ከመጋዘኑ እንደማይወጣ በማረጋገጥ ለአመልካች በጽሑፍ ሊያሳወቅና ሰሊጡን በጥሩ ሁኔታ ሊይዝ ተስማምቷል።

- አመልካች ደግሞ ሰሊጡ በተቀመጠበት መጋዘን የራሱን ተቆጣጣሪ ሠራተኛ መድቦ የሰሊጡን ጥራት፣ አቀማመጥና አያያዝ ሊቆጣጠር፤ ሰሊጡ የተገዛበትን ዋጋ ሰባ በመቶ ወደ ፐርፍ ሂሳብ ገቢ ሊያደርግ እና ፐርፍ ወደ ውጭ የሚልከውን ሰሊጥ ዋጋ በቅድሚያ ሲከፍል ሰሊጡ ለውጭ ገበያ እንዲጫን ሊፈቅድ ተስማምቷል።

የብድሩ ገንዘብ ለፐርፍ የሚለቀቀው ሰሊጡ በመጋዘን ለመግባቱ ከአስቀማጩ ማረጋገጫ ሲቀርብ ነበር።

1.2. ተዋዋዮቹ ከላይ በተገለጸው የሦስትዮሽ ስምምነት መሠረት ከጥቅምት 1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2001 ዓ.ም ድረስ ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ ተጠሪ ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ/ም በፐርፍ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ ምክንያት ችግር በመፈጠሩ ሥራው ሊቋረጥ ችሏል። ተጠሪ በመሠረቱት ክስ ፐርፍ በአደራ እንዲያስቀምጥ የሰጡትን ግምቱ ብር 2,934,183.00 የሆነ 2,257.064 ኩንታል የሁመራ ሰሊጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ ስለአልሆነ ሰሊጡን እንዲያስረክብ እንዲወሰንና ጉዳዩ እስኪወሰን ድረስ ሰሊጡ እንዳይሸጥና ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው አመለከቱ። ፍ/ቤቱም በአስቀማጩ መጋዘን የተቀመጠ ሰሊጥ ካለ በማንኛውም ሁኔታ ለሦስተኛ ወገን ሳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ ሰጠ።[554]

---

[553] ይህ ውል የተደረገው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2831 በሚፈቀደው መሠረት ነው።

[554] የኦ/መ/ቁ. 72845ን ይመልከቱ። ፐርፍ ጠቅላላ መጋዙ ብር 8,175,653.68 የሆነውን 5,766.14 ኩንታል የሁመራ ሰሊጥ ወደ አስቀማጩ መጋዘን ያስገባው ከየካቲት 7/2000 እስከ ግንቦት 19/2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ

1.3. አስቀማጩ ይህ የእግድ ትዕዛዝ ሲደርሰው ጉዳዩን ወዲያውኑ ለአመልካች አሳወቀ:: አመልካችም ከስ የቀረበበትን 2,257.064 ኩንታል የሁመራ ሰሊጥ ጨምሮ TCF በአስቀማጩ መጋዘን ያከማቸውን 5,766.14 ኩንታል ሰሊጥ ለTCF ለሰጠው 8 ሚሊዮን ብር ብድር በመያዣ የያዘውና የቅድሚያ መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ ሰሊጡን ሸጦ ለብድሩ መክፈያ ለማዋል እግዱ እንዲነሳለት ኅዳር 17 ቀን 2001 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ጠየቀ:: ፍ/ቤቱም ማመልከቻውን ተቀብሎ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጡበት ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን ሊሰማ ቀጠሮ ያዘ::

1.4. አመልካች ባቀረበው ማመልከቻ ላይ ተጠሪ ኅዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በሰጡት አስተያየት፣

- *አመልካች ከTCF ጋር ባደረጋቸው አራት የብድር ውሎች ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘው ሰሊጥ ብዛት በብድር ውሎቹ ውስጥ መገለጹን፤*
- *አመልካችና TCF የተዋዋሉት የመጨረሻው የብድር ውል የተደረገው የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑንና ለዚህ ብድር አመልካች በመያዣ የያዘው ጠቅላላ ዋጋው ብር 4,300,000.00 የሆነ በተለያዩ ጊዜያት ለመበጠር ወደ አስቀማጩ መጋዘን የሚገባ የሁመራና የወለጋ የሰሊጥ ምርት መሆኑ በውሉ ውስጥ መገለጹን፤*
- *ተጠሪ ለTCF ሰሊጡን በአደራ የሰጡት ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ሲሆን፤ ይህም አመልካች በተለያዩ ጊዜያት ለመበጠር ወደ አስቀማጩ መጋዘን የሚገባ የሁመራና የወለጋ የሰሊጥ ምርት በዋስትና ይዞ ለTCF ብድር ከሰጠ ከሦስት ወር በኋላ በመሆኑ የእነሳቸው ሰሊጥ የብድሩ መያዣ ነው ሊባል እንደማይችል፤*
- *ኅዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም አመልካች፣ TCF እና አስቀማጩ የተዋዋሉት የሦስትዮሽ ውል የብድሩ መያዣ የሆነው ሰሊጥ በ3ኛ ወገን እጅ እንዲቀመጥና የንብረቱን አጠባበቅ ለመወሰን በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2831 መሠረት የተደረገ መሆኑን፤*
- *TCF በተለያዩ ጊዜያት ለአመልካች የጻፋቸው ደብዳቤዎች የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም ከተደረገው የብድር ውል በኋላ የተጻፉና TCF በአስቀማጩ መጋዘን ያስገባውን ሰሊጥ እየገለጸ ብድሩ እንዲለቀቅለት የጻፋቸው ደብዳቤዎች[555] አራቱንም የብድር ውሎች ከመግለጽ በስተቀር የትኛው*

ውስጥ ሲሆን፣ ከዚሁ ሰሊጥ ውስጥ የተጠሪ ነው የተባለው 2,318 ኪሻ ወይም 2,257.064 ኩንታል የሁመራ ሰሊጥ ነው:: ተጠሪ የእኔ ነው ያሉት ሰሊጥ የተገዛበት ጠቅላላ ዋጋ ብር 4,288,421.60 ሲሆን፣ የእዚሁ ዋጋ 70 በመቶ 3,001,895.12 ነው:: ነገር ግን ከዚሁ ከስ ጋር በተያያዘ ተጠሪ የእኔ ነው ያሉበትን 3,121.17 ኩንታል ሰሊጥም ፍ/ቤቱ ለዳግባብ ለሰጠገደው የአመልካች መያዣ የሆነው ሰሊጥ ይዘ ጸሐፍ ለስከተጠናቀቀበት ሚያዝያ 2002 ዓ.ም ድረስ እንዳይነገደ ደገኖበ:: ከTCF ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰሎች ወገኖችም በTCF ላይ ለሰለሰፈረዱ ሰሊጡ ተሸጦ ይከፈሉን በማለት ይከራከራሉ::

[555] *ለአስቀማጩ ግንቦት 15 እና 16 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር ናበዳ/7048/2000፣ ናበዳ/7067/2000፣ ናበዳ/7068/2000 እና ናበዳ/7069/2000 በጻፋቸው አራት ደብዳቤዎች TCF 2,318 ኪሻ ወይም 225,706.4 ኪሎ ግራም የሁመራ ሰሊጥ በመጋዘኑ ውስጥ ያስገባ መሆኑን ገልጿል:: TCFም ግንቦት 15 እና 19 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፋቸው አራት ደብዳቤዎች ለአስቀማጩ ለረጋገጠ የገለበውን ሰሊጥ ለተፈቀደለት ብድር በመያዣ መስጠቱን ጠቅሶ ጥቅምት 14/1998፣ መጋቢት 30/1998/ ሰኔ 6/1999 እና የካቲት 7/2000 በተፈረሙት በሸቀጥ መያዣነት በተፈቀዱት የብድር ውሎች መሠረት ሰሊጡ የተገዛበት ዋጋ 70% የሆነው ገንዘብ ቁጥሩ C/A 077 በሆነው ተንቀሳቃሽ ሂሳቡ እንዲገባለት ጠይቆ ገቢ ተደርጎለታል::*

ሰሊጥ ለየትኛው ብድር መያዣነት እንደተሰጠ ስለማይገልጹ የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ እንዲሆን አመለከቱ።

1.5. ከላይ የተገለጸው ክርክር ከተደረገ በኋላ ተጠሪና ፐርፍ ታኅሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት አድርገው ስምምነቱን ፍ/ቤቱ እንዲመዘግብላቸው ጠየቁ።[556] ፍ/ቤቱም ታህሣሥ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ስምምነቱን መዝግቦ ተጠሪና ፐርፍ በስምምነቱ መሠረት ይፈጽሙ። ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ፐርፍ በአስተግዳሮ መጋዘን ባስገባው ሰሊጥ ላይ ፍ/ቤቱ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል በማለት መዝገቡን ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት መለሰው። ፍ/ቤቱ አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ በሚመለከት ምንም ያለው ነገር የለም።

1.6. እንዲሁም፣ ተጠሪ የእርቅ ስምምነቱ ለአስቀግዳ እንዲደርሰውና በትዕዛዙ መሠረት እንዲፈጽም እንዲታዘዝ ታህሣሥ 17 ቀን 2001 ዓ.ም አመልክተው ፍ/ቤቱ በዚሁ ቀን በዋለው ችሎት የተዘጋውን መዝገብ አስቀርቦ አስቀግዳ በስምምነቱ መሠረት ሰሊጡን ለተጠሪ እንዲያስረክብ የእርቅ ስምምነቱ ይድረሰው በማለት ትዕዛዝ ሰጠ።

1.7. አመልካች ይህን እንዳወቀ ክርክር የተነሳበትን ሰሊጥ ለሰጠው ብድር በመያዣ ስለያዘውና የቅድሚያ መብት ስለአለው ፐርፍ ሰሊጡን ለተጠሪ ለማስረከብ ያደረገው ስምምነት የአመልካችን የመያዣ መብት ስለሚጎዳ ተፈጻሚ እንዳይሆን፤ ፐርፍና አስቀግዳ ሰሊጡን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተሰጠው ትዕዛዝም እንዲታገድለት ጥር 22 ቀን 2001 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ለፍ/ቤቱ አመለከተ። *ፍ/ቤቱም ተጠሪ ክሱ በመሠረቱበት ብር 2,934,183.00 ላይ ጸንጎት ከፍለህ አቤቱታው ለግራ ቀኙ ደርሷቸው ተዚጋጅተው ይቅረቡ፤ ታህሣሥ 15 እና 17 ቀን 2001 ዓ.ም ፍ/ቤቱ የሰጣቸው ትዕዛዞች ታግደዋል* በማለት ጥር 27 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጠ።[557]

1.8.አመልካች በትዕዛዙ መሠረት ጸንጎት ከፍሎ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ካየ በኋላ፣ የናይል ቡና ላኪ ኃ/የተ/የግ/ማ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተከሳሹ ከመጋቢት 7 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ሰሊፕ በመጋዘኑ ማራገፉን፤ ሁሉም ሰሊጦች ስመቃወም አመልካች በሥስትዮሽ ስምምነት መሠረት ሪፖርት መደረጋቸውንና ከዚህ ውጭ ስመቃወም አመልካች ሳይገስጽ በተከሳሹ አማካይነት የተቀመጠ ሰሊፕ የለም ሲል አረጋግጧል። በመቃወም አመልካች የብድር ገንዘቡን ስተከሳሽ የሚሰቀው ይህ ሪፖርት ሲደርሰው በመሆኑ በመጋዘኑ ውስጥ ያሉ ሰሊጦች መያዣው ዋጋ የሚኖረው መያዣ ተቀባዩ በእጁ እድርጎ ሲያዝበት ነው በማለ ተክራከረዋል። በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2831 መሠረት የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በሦስተኛ ወገን እንዲቀመጥ ሲደረግ እንደሚችል የሚደነግግ በመሆኑ ተከሳሽ፣ በመቃወም አመልካችና ናይል ቡና ላኪ ያደረጉት የሦስትዮሽ ስምምነት ይህን የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ከሳሽ ያቀረቡት ክርክር በሕጉ የተደገፈ አይደለም። ከሳሽና ተከሳሽ ያደረጉት

---

[555] ተጠሪ እና ፐርፍ ታኅሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት ፐርፍ 2,257.064 ኩንታል የዘሙቱ ሰሊጥ ከተጠሪ በእዳቸ መቀበሱንና በእስተግዳ መጋዘን ማስቀመጡን፤ ይህን ሰሊጥ ጥር 30 ቀን 2001 ዓ.ም በተጠሪ ስማስረከብና ተጠሪ ሰእርክረ ያመጡትን መጭ ስመክፈል ተስማምቶ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 276 መሠረት የግዳገል ስምምነት ማድረጋቸውን ይገልጻል።

ስምምነት ተፈጻሚ ሲሆን የሚችለው ተከሳሹ በመቃወም አመልካች ያልተያዘ ሰሊጥ በመጋዘን ሲያስገቡ ወይም የብድር ዕዳችውን ከፍለው ሰሊጡን ሲያስለቅቁ ብቻ ነው:: በመሆኑም በስምምነቱ መሠረት የማይፈፀም ቢሆን የሚነሳው የአፈጻጸም ጉዳይ ነው:: ይህም የአፈጻጸም መዝገብ ተከፍት ከሚታይ በስተቀር በዚህ ደረጃ የሚስተናገድ አይሆንም:: ፍ/ቤቱ ታህሣሥ 17 ቀን 2001 ዓ/.ም ገሬ ቀን በስምምነቱ መሠረት እንዲፈጽሙ የሰጠው ትዕዛዝ መታየት የሚገባው ከዚህ አንጻር ነው:: በመሆኑም በመቃወም አመልካች የእርቅ ስምምነቱ ይሠረዝልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበለም:: እንዲሁም የእርቅ ስምምነቱ የመቃወም አመልካችን መብት ያጣብባል ተብሎ የቀረበውን አቤቱታ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም:: ፍ/ቤቱ ጥር 27 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጠውን እገድ እንስቷል፣" በማለት ሚያዝያ 2 ቀን 2001 ዓ.ም መዝገቡን ዘግቷል::[558]

2. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በዋስትና በያዘው ሰሊጥ ላይ ተጠሪና ፒርፍ ያደረጉትን የእርቅ ስምምነት ፍ/ቤቱ መዝግቦ ሰሊጡ በእርቅ ስምምነቱ መሠረት ለተጠሪ እንዲሰጥ ማዘዙ የአመልካችን የመያዣ መብት ስለሚያሳጣ፣ እንዲሁም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ዳኝነት የከፈለበት አቤቱታ በአፈጻጸም ከሚታይ በስተቀር በዚህ ደረጃ የሚስተናገድ አይደለም ተብሉ ውድቅ መደረጉ አግባብ ስለአልሆነ እንዲሻርለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቀረበ::[559]

ይግባኙን የሰማው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለእያንዳንዱ ብድር የተደረገ የሰሊጥ ብዛትና ዓይነት በእያንዳንዱ የብድር ውል እየተጠቀሰ ስለተቀመጠ ኅዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው የሶስትዮሽ ውል ድግግሞሽ ነው::[560] ይግባኝ ባይ አስቀድሞ የሰጠው ብድር በሚገባ ሁኔታ ገቢ ሳይደረግለት ሌላ ብድር ደርቦ መስጠት የለበትም::[561] አከራካሪው ሰሊጥ ወደ መጋዘን የገባው ከግንቦት 13 እስከ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን፣ ይግባኝ ባይና ተከሳሹ ያደረጉት የመጨረሻ የብድር ውል የተደረገው የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ነው:: ብድሩ የተሰጠው ሰሊጡ ወደ መጋዘኑ ከመግባቱ በፊት በመሆኑ በብድር ውሉቹ ላይ የተጠቀሰው መያዣ ከአከራካሪው ሰሊጥ ጋር

---

[558] *የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 72845ን ይመልከቱ::*

[559] *ተጠሪም የአስቀማጩ መጋዘን ብዙ ምርት ስለተከማቸበትና አመልካች በሰሊጡ ላይ ምልክት አድርጎ በራሱ ቁጥጥር ሥር ስለአላደረገ መያዣዬ ነው ማለት ስለማይችል፣ ፍ/ቤቱ ሰሊጡ የአመልካች መያዣ ነው ማለት ይቻላል ያለው አግባብ ስለሆነ ይህ አቤቱታ ይታረምልኝ በማለት መስቀልኛ ይግባኝ አቅርቧል::*

[560] *ጠቅላይ ፍ/ቤት ለእያንዳንዱ ብድር መያዣ የሆነው ሰሊጥ ብዛትና ዓይነት በእያንዳንዱ የብድር ውል በመገለጹ ኅዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው የሦስትዮሽ ውል ድግግሞሽ ነው በማለት የገለፀው ስምምነቶችን በአግባቡ ባለማጤን ነው:: የሦስትዮሽ ውሉ ዓላማ መያዣው በ3ኛ ሰው እጅ እንዲቀመጥ ለማድረግ ነው:: የብድር ውሎቹ ዓላማ ደግሞ ለፒርፍ ብድር ለመፍቀድና የብድሩ መያዣ ምን እንደሆነ በትክክል ለማመልከት ነው:: በብድር ውሎቹም ውስጥ ለፒርፍ የተፈቀደው የብድር መጠንና የብድሩ መያዣም ፒርፍ ወደፊት በአስቀማጩ መጋዘን የሚያስገባው የጠለጋና የሁመራ ሰሊጥ ምርት መሆኑ በትክክል ተገልጿል::*

[561] *ጠቅላይ ፍ/ቤት "ይግባኝ ባይ አስቀድሞ የሰጠው ብድር ገቢ ሳይደረግለት ሌላ ብድር መስጠት የለበትም" ያለው አግባብ ነው:: አመልካች ባንክ እንደመሆኑ መጠን ብድር መስጠት የቀን ተቀን ሥራው ነው:: የንግድ ሥራው ለምን ነው ብሎ እስካመነ ድረስ መያዣ በመቀበል ወይም ያለመያዣ ብድር ሊሰጥ ይችላል:: ፍ/ቤቱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ተዋዋዮቹ ባደረጉት"ውልና በሕጉ መሠረት ውሳኔ መስጠት ነበረበት እንጂ፣ በአበዳሪና በተበዳሪ የንግድ ግንኙነት ጣልቃ በመግባት በፊት የሰጠሽውን ብድር ሳይከፍልህ ሌላ ተጨማሪ ብድር መስጠት የለብህም ማለት አይገባውም::*

ግንኙነት የለውም።[562] የብድር ውሉቹ ሰሊጡን በመያዣነት ያልጠቀሱት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2828(1) የተደረገ መያዣ አይደለም ብለናል በማለት ተጠሪና ፐርፍ ባደረጉት ስምምነት መሠረት እንዲፈፀም ውሳኔ ሰጥቷል።

3. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቤቱታ አቀረበ። በአቤቱታውም፣

   - የብድሩ መያዣ በ3ኛ ሰው እጅ እንዲቀመጥ ኅዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም በፐርፍ፣ በአስቀማጩና በአመልካች መካከል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2831(1) መሠረት የሦስትዮሽ ውል መደረጉን፤ በዚህ የሦስትዮሽ ውል መሠረት አመልካች ከፐርፍ ጋር የብድር ውሎች በመዋዋል በአስቀማጩ መጋዘን የሚቀመጠውን ሰሊጥ በዋስትና እየያዘ ከሰሊጡ ጠቅላላ ዋጋ ሰባ በመቶውን ለፐርፍ ሲያበድር መቆየቱንና ይህም ብድር 8 ሚሊዮን ብር መድረሱን፤
   - አመልካች የፈቀደው ብድር በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል (Term loan) ሳይሆን እንደ ኦቨርድራፍት ብድር ባልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የብድር ሂሳብ (credit facility) መሆኑን፤
   - ፐርፍ ሰሊጡ ለብድሩ መያዣ ሆኖ በአስቀማጩ መጋዘን እንዲቆይ መስማማቱን፤ አስቀማጩም ሰሊጡን በመጋዘኑ ለማስቀመጥና ያለአመልካች ፈቃድ ላለመልቀቅ ተስማምቶ በዚሁ መሠረት ሲፈጽም መቆየቱን፤
   - ፐርፍ ሰሊጡን ከመጋዘን አውጥቶ መውሰድ የሚችለው የተበደረውን ገንዘብ በመክፈል መሆኑን፤ ፐርፍ ዕዳውን ባይከፍል አመልካች የ15 ቀን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሰሊጡን ለመሸጥ የሚችል መሆኑ በውሉ መገለጹን፤

562 ሰ/ፍ/ቤቱ ይህን ያለው ፐርፍና አመልካች ያደረጓቸውን የብድርና የመያዣ ውሎች በአግባቡ ከመረ ሳይሆን የመጨረሻው የብድር ውል የተደረገበትን ቀንና ሰሊጡ ወደ መጋዘን የገባባቸውን ቀናት በማነጻጸር ብቻ ነው። ፐርፍ በንግዱ ስለተሰማራና ከውጭ አገር በርካታ የገዥ ጥያቄዎች ስለቀረቡለት የተፈቀደለት የብድር መጠን የቀረበበትን የገዥ ጥያቄ ለማሟላት ስለማያስችለው የብድሩ መጠን ከፍ እንዲልለት አመልካች የብድሩን ጣሪያ ወደ 8 ሚሊዮን ብር ከፍ ለማድረግ የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም ተጨማሪ የብድር ውል ተፈርሟል። በዚህም የብድር ውሎች ውስጥ የብድሩ መያዣ ፐርፍ በአስቀማጩ መጋዘን የሚያስቀምጠው መጠኑ የተወሰነ የመጠንና የሁመራ ሰሊጥ መሆኑ በግልጽ ተጠቅሷል። አመልካች ለፐርፍ የ8 ሚሊዮን ብር የብድር ጣሪያ የፈቀደለት የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገው ውል ብቻ ሳይሆን ቀደም ብለው በተደረጉት ሦስት ውሎች ጭምር ነው። የፐርፍ ሥራ ባደገ ቁጥር አመልካች የብድሩን ጣሪያ ከፍ ሲያደርግለት ቆይቷል። አመልካች ለፐርፍ የፈቀደው እንደ ኦቨርድራፍት ብድር ባልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የብድር ፋሲሊቲ እንጂ በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ብድር (Term loan) አይደለም። በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ብድር ቢሆን ተከፍሎ ሲያልቅ ውሉ ቀሪ ይሆናል። ይህኛው ግን ባልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ፋሲሊቲ በመሆኑ ፐርፍ የተፈቀደለትን ጣሪያ ሳያልፍ ከብድር ሂሳቡ ገንዘብ እያወጣ ሰሊጥ ሲገዛና ሲያበጥር ወደ ውጭ ሊልክ ይችላል። ገንዘብ የተለቀቀለትም በውሉ ላይ የተጠቀሰውን የሁመራ ሰሊጥ በአስቀማጩ መጋዘን ያስገባ በመሆኑ አስቀማጩ በሦስትዮሽ ውሉ መሠረት ለአመልካች በጽሑፍ እየገለፀ ፐርፍም ሰሊጡ የተገዛበት ዋጋ ሰባ በመቶ ወደ ሂሳቡ ገቢ እንዲደረግለት በጽሑፍ እየጠየቀ ነው። የመጨረሻው ውል የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም ቢደረግም፣ ፐርፍ በጥር ወር 2000 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የተፈቀደለትን ገንዘብ ከፍሎ በመጋዘን በመያዣ ሰጥቶት የነበረውን ሰሊጥ በሙሉ ወደ ውጭ ለመላክ ከየካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በመጋዘን ገብቶ የተከማቸውን ሰሊጥ በዋስትና በመያዝ ለፐርፍ ገንዘብ የተለቀቀለት ከየካቲት 19 እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ለመረዳት በተከታታይ ሳያገናዝብ የብድሩ ገንዘብ ለፐርፍ የተለቀቀውና አመልካችም መያዣውን የተቀበለው የመጨረሻው ብድር ውል በተፈረመበት ቀን እንደሆነ በመቁጠር ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ሰጥቷል።

- ለብድሩ በዋስትና ተይዞ በአስቀማጩ መጋዘን ተከማችቶ የሚገኘው የፐርፍ ሰሊጥ ክርክር የቀረበበትን ጨምሮ 6228 ኬሻ ወይም 5766.144 ኩንታል መሆኑን፤
- መያዣ የተሰጠበት የገንዘብ መጠን እና የብድሮቹ መያዣ ፐርፍ በአስቀማጩ መጋዘን የሚያስገባው የወለጋና የሁመራ ሰሊጥ መሆኑ በአያንዳንዱ የብድር ውል ውስጥ ስለመያዣ በሚለው አንቀጽ ሥር ተገልጸ እያለ ይግባኝ ሰሚው ጠ/ፍ/ቤት የብድሩን መያዣ በሦስተኛ ሰው ዘንድ ለማስቀመጥ የተደረገው የሰስትዮሽ ውል የፍ/ህግ ቁጥር 2828(1)ን ድንጋጌ እያሟላም፤ ሰሊጡ የብድሩ መያዣ መሆኑም በብድር ውሎቹ አልተጠቀሰም ማለቱ አግባብ አለመሆኑን፤
- አስቀማጩ እስከ ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ፐርፍ ወደ መጋዘኑ ያስገባው የሰሊጥ ምርት በሦስትዮሽ ውሉ መሠረት መሆኑን እና ለአመልካች ሳይገለጽ የተቀመጠ ሰሊጥ የሌለ መሆኑን ለፍ/ቤቱ በጻፈው ደብዳቤ ገልጾ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይህን ትቶ የብድር ውሎቹ ሰሊጡን በመያዣነት ያልጠቀሱት በመሆኑ የብድሩ መያዣ አይደለም በማለት ተጠሪና ፐርፍ ባደረጉት ስምምነት መሠረት እንዲፈፀም የወሰነው ሰሊጥን እንደሚመዘንብና የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥበት ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመቁጠር መሆኑን በመግለጽ ውሣኔው ተሽሮ ክርክር የተነሳበት ሰሊጥ አመልካች በመያዣ የያዘው ነው እንዲባልለት አመልክቷል።

ይሁን እንጂ፣ የሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ እንዲህ በማለት ውድቅ አድርጎታል፤

> ለክርክሩ መነሻ በሆነው ሰሊጥ ላይ አመልካች መብት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ ከማየት በፊት *ከመሠረቱ ሰሊጡ የማን ንብረት ነው?* የሚለውን ጥያቄ መመለሱ አግባብ ይሆናል። ሰሊጡ የማን ነው? በሚለው ነጥብ ላይ በዝርዝር ክርክር የተደረገው በፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሲሆን፣ በዚህ ሂደትም ፍ/ቤቱ ሰሊጡ በተጠሪ ስም ከጎንደር ተጭኖ ወደ አዲስ አበባ መምጣቱንና የሥር ተከሳሽ ተቀብሎ በናይል ቡና ላኪ ኃ.የተ.የግል ማህበር መጋዘን ውስጥ ማስቀመጡን አረጋግጧል። ... ተጠሪ ሰሊጡን ወደ አዲስ አበባ ያመጣው ለመሸጥ እንደሆነ፣ ነገር ግን የገበያ ዋጋ ስለዋዠቀበት የተሻለ ገበያ እስኪያገኝ ድረስ በአደራ እንዲቀመጥለት ማድረጉን ፍ/ቤቱ ማጣራቱን በውሳኔው ላይ ገልጿል። ፍ/ቤቱ እነዚህን ማስረጃዎች ከመረመረ እና ከግራ ቀኙ ወገኖች የቀረበውን ክርክር አገናዝቦ ከመዘነ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሰሊጥ የተጠሪ ንብረት ነው ወደሚለው መደምደሚያ ደርሷል። እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሰሊጥ የተጠሪ ንብረት ስለመሆኑ በሕግና በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበውን ክርክር የመመርመር ሥልጣን ባለው ጠ/ፍ/ቤት ተረጋግጧል። አመልካች የመያዣ ውል ያደረገው ከተጠሪ ጋር አይደለም። የመያዣ ውል አደረግሁ የሚለው ከሥር ተከሳሽ ፐርፍ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ጋር ሆኖ መሠረቱም በየጊዜው ተሰጡ የተባሉት ብድሮች እንደሆኑ በክርክሩ ገልጾታል። *አመልካች በሰሊጡ ላይ መብት አለኝ የሚለው የመያዣ ውሉን መሠረት በማድረግ እስከሆነ ድረስ ሰሊጡ የመያዣ ሰጪው ንብረት መሆኑን ሊያስረዳ ይገባል።* እንደምናየው ግን የመያዣ ውል ማድረጉን

ከማሳየት አልፎ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሰሊጥ የመያዣ ሰጭው ንብረት መሆኑን ሲያስረዳ እንዳልቻለ ጠ/ፍ/ቤቱ አረጋግጦአል። በመሆኑም ለክርክሩ አልባት ለመስጠት መታየት ያለበት ሰሊጡ የማን ንብረት ነው ለሚለው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ እንጂ አመልካች ከሥር ተከሳሽ ጋር የመያዣ ውል አድርጓል ወይስ አላደረገም የሚለው አይደለም። ... የቀረበው የሰበር አቤቱታ በሕግ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት መኖሩን የሚያሳይ ባለመሆኑ የሰበር ችሎቱ የሚያርመው አይሆንም።

4. የሰበር ችሎት ከላይ የተገለፀውን ለማለት ያስቻለውን የሕግ ድንጋጌ አልጠቀሰም። ተንቀሳቃሽ ዕቃን ስለያዘ ባለገንዘብ መብትና ግዴታ በሚደነግገው ንዑስ ክፍል ስር የተጻፈው የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2843 የሚደነግገው የሰበር ችሎት ከፊረደው በተለየ ነው። እንዲህ ይላል፤

ቁ. 2843 - መያዣው የኔ ነው ስለሚል ሦስተኛ ወገን

መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ይህን መያዣ የተቀበለው የባለቤትነት መብት ከሌለው ሰው ላይም ቢሆን እንኳ የመያዣው ውል በሚሰጠው መብት ሊሠራበት ይችላል።

4.1. የሰሊጥ፣ የኑግ፣ የተልባ እና የሱፍ ምርቶች የቅባት እህል ምርቶች ናቸው። በተለይ የሰሊጥና የኑግ ምርቶች እስከሚበጠሩና ከተበጠሩም በኋላ ወደ ውጭ እስኪላኩ ድረስ በኬሻ እየተደረጉ በመጋዘን ይቀመጣሉ። እነዚህ ምርቶች ለንግድ ዓላማ በመኪና ተጭነው ሲጓጓዙና በመጋዘን ሲከማቹ የሰሊጡን ባለቤት የሚያውቁት አጓጓዡ እና በመጋዘን አስቀማጩ ብቻ ናቸው። ባንኮች እነዚህን የሀገር ምርቶች በመጋዘን እንደተቀመጡ በዋስትና በመያዝ ለነጋዴዎች ገንዘብ ያበድራሉ። በዋስትና በሚይዙበት ጊዜም ለምርቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ አይጠይቁም። ቢጠይቁም ሊቀርብላቸው አይችልም። ምክንያቱም እንዲህ ላለው ተንቀሳቃሽ ንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት የሚሰጥ አካል የለም። በሕጉ መሠረት እንዲህ ያለውን ተንቀሳቀቃሽ ንብረት በእጁ የያዘው ሰው የንብረቱ ባለቤት እንደሆነ ይገመታል።[563]

4.2. በሰ/መ/ቁ. 51001 በተጠቀሰው ጉዳይ ፐርፍ ከዚህ በፊት ሲያደርግ እንደቆየው የሁመራ ሰሊጥ በአስቀማጩ መጋዘን አስገብቶ ከአመልካች ለሚወስደው ብድር በመያዣ ሰጥቷል። አስቀማጩም ፐርፍ 6=228 ኬሻ ወይም 5=766.14 ኩንታል የሁመራ ሰሊጥ በመጋዘኑ ማስገባቱንና አመልካች ካልፈቀደ በቀር ሰሊጡ ከመጋዘኑ እንደማይወጣ በማረጋገጥ ለአመልካች በደብዳቤ ገልጿል።[564] በዚህ መሠረት አመልካች ሰሊጡን በዋስትና በመያዝ ሰሊጡ የተገዛበትን ዋጋ ሰባ በመቶ በብድር ውሉ መሠረት ለፐርፍ ለቆለታል።

---

563 ቁጥር 1193(1)

564 ፐርፍ ከየካቲት 19 ቀን 2000 ስሰከ ፖንቦተ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ባሱተ ሦስተ ወራት ሙለጥ ለአመልካች በጻፋቸው 13 ደብዳቤዎች በአስቀማጩ መጋዘን 5,766.14 ኩንታል ሰሊጥ በብር 8,175,653.68 ገዝቶ ማስቀመጡን ገልጾ በብድር ውሉቹ መሠረት የሰሊጡ ዋጋ ሰባ በመቶ ብር 5,722,957.58 ወደ ሂሳቡ ገቢ እንዲደረግለት ጠይቆ ገቢ ተደርጎለታል። ከዚህ ሰሊጥ ሙለጥ ተመሪ የስኔ ነው ያሉተ 2,257.064 ኩንታል ሲሆን፣ ፐርፍ ይህን ሰሊጥ በብር 4,288,421.60 የገዛው መሆኑን ገልጾ የዚህ ሰባ በመቶ ብር 3,001,895.12 በሂሳቡ ገቢ እንዲደረግለት ጠይቆ ገቢ ተደርጎለታል።

4.3. ፐርፍ የተጠቀሰውን ሰሊጥ በመያዣ ለጥቶ ከአመልካች ብድር ከወሰደ በኋላ ብድሩን ሳይከፍል በአደራ የተቀበልኩት ነው በማለት የእርቅ ስምምነት እንዲያደርግና ሰሊጡን ለተጠሪ እንዲያስረክብ ሕግ አይፈቅድለትም::[565] ጉዳዩን በየደረጃው ያዩት ፍ/ቤቶች ግን የመያዣ ሕጉ የሚለውን ወደ ጎን በመተው ፐርፍና ተጠሪ ባደረጉት የእርቅ ስምምነት መሰረት ተጠሪ ሰሊጡን እንዲወስዱ ፈርደውላቸዋል::[566] እነዚህ ፍርዶች ሕጉን መሠረት ያደረጉ አይደሉም::

4.4. አመልካች ሰሊጡን በመያዣ በተቀበለበት ጊዜ ሰሊጡ የተጠሪ ንብረት መሆኑን አያውቅም:: ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታም አልነበረም:: ተጠሪም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2844(1) በሚደነግገው መሠረት አመልካች ሰሊጡን ከፐርፍ ላይ በመያዣ የተቀበለው ፐርፍ የሰሊጡ ባለቤት አለመሆኑን እያወቀ ነው በማለት ያስረዱት ነገር የለም:: ይህን ነጥብ ተጠሪ ባላስረዱበት ሁኔታ ሰሊጡን ከአመልካች ተረክበው መውሰድ የሚችሉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2844(2) መሠረት ሰሊጡ መያዣ የሆነበትን ዕዳ ለአመልካች ከፍለው መሆን ነበረበት::

4.5. የባለቤትነት ማረጋገጫ የማይቀርብበትን ተንቀሳቃሽ ንብረት በእጁ የያዘው ሰው ባለቤት መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለ ከዚህ ሰው ጋር የመያዣም ሆነ የግዥ ውል በመዋዋል ንብረቱን በእጅ ማድረግ ይቻላል:: ሻጩ ወይም በመያዣ የሰጠው ሰው በዕቃው ላይ መብት እንደሌለው ዘግይቶ ቢታወቅ በገዥው ወይም በመያዣ ተቀባዩ ላይ መቃወሚያ ሊሆንበትና በንብረቱ ላይ ያለውን መብት ሊያሳጣው አይችልም::[567] በዚህ ጉዳይ ሰሊጡን በአስቀማጩ መጋዘን አስገብቶ ያስረከበው ፐርፍ ነው:: አስቀማጩና አመልካቹ የሰሊጡ ባለቤት ፐርፍ ነው ብለው በቅን ልቦና ለመገመት በቂ ምክንያት አላቸው:: ፐርፍ ከዚህ በፊትም ሰሊጥ እየገዛና እያስበጠረ ወደ ውጭ ሲልክ የቆየ ነጋዴ መሆኑን አስቀማጩም አመልካችም ያውቃሉ:: ከማወቅም አልፈው ገንዘብ በማበጠርና በማበደር አብረው ሲሠሩ ቆይተዋል:: ሁኔታው ይህ ለመሆኑ ከበቂ በላይ ማስረጃ ቀርቦ እያለ የሰበር ችሎት አመልካች የመያዣ መብቱን ለማስከበር ሰሊጡ የመያዣ ሰጭው (የፐርፍ) መሆኑን ማስረዳት አለበት በማለት የወሰነው አላግባብ ነው::

4.6. አመልካች ሰሊጡ የፐርፍ አለመሆኑን እያወቀ በመያዣ ለመቀበሉ ተጠሪ አላስረዱም:: መያዣ ሰጭው በዕቃው ላይ መብት የሌለው መሆኑን መያዣ ተቀባዩ ያውቅ እንደነበር ዕቃው የኔ ነው ባዩ በማስረጃ ካላረጋገጠ በቀር መያዣ ተቀባዩ የመያዣው ውል በሚሰጠው መብት ሊሠራበት እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2844(1) እና 2843 በግልጽ ይናገራሉ:: ንብረቱ የሌላ ሰው መሆኑን መያዣ ተቀባዩ ያውቃል ወይም ማወቅ ነበረበት ሊባል የሚችለው ንብረቱ በመንግሥት አካል የሚመዘገብና የባለቤትነት ማረጋገጫ የሚሰጥበት ቢሆን ነበር:: ለምሳሌ ተሽከርካሪ ወይም ስም የተጻፈበት አክሲዮን ቢሆን፣ መያዣ ተቀባዩ የንብረቱን ባለቤትነት ማረጋገጫ በማየት ባለቤቱን ሊያውቅ ስለሚችል ይህን ሳያደርግ የሌላ ሰው ንብረት ይዞ ከተገኘ የመያዣ ውሉ ውድቅ ሆኖ የንብረቱ ባለቤት የተያዘውን ዕቃ መልሶ ለመውሰድ

---

[565] *ቁጥር 2843*

[566] *ቁጥር 2843 እና 2844*

[567] *ሶፐር 1161፣ 1162፣ 1163(2)፣ 2843 እና 2844(1)ን ይመልከቱ::*

ይችላል::[568] ንብረቱ የእኔ ነው የሚለው ሦስተኛ ወገን ይህን ሁኔታ ማስረዳት ካልቻለ ግን መያዣ ተቀባዩ የመያዣው ውል በሚሰጠው መብት እንዲሠራበት ሕግ ፈቅዶለታል:: ሁኔታው ከላይ እንደተገለፀው ሆኖ ሳለ የይግባኝ ሰሚው ችሎት የፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት እንዲታረምለት አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ፍበሕግ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት መኖሩን የሚያሳይ ባለመሆኑ የሰበር ችሎቱ የሚያርመው አይሆንምን ተብሎ ውድቅ መደረጉ እጅግ የሚያስገርም ነው::

[568] ቁፐር 2844::

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ
መንበረፀሐይ ታደሰ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
አልማው ወሌ

አመልካች፣ አቢሲንያ ባንክ - መርዓዊ ታደሰ ቀረበ።
ተጠሪ፣ ዘውዱ ነጋ ከጠበቃው ደሳለኝ አለሙ ክብረት ጋር ቀረበ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ነጥብ ተጠሪ ንብረቱ ነው በማለት ክስ የመሠረተበት ሰሊጥ አመልካች ከሌላ ሰው ጋር ባደረገው ስምምነት በመያዣ የያዘው የመያዣ ሰጪው ንብረት ነው ወይንስ የተጠሪው ንብረት የሚለው ነው። ክርክሩ ከፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ ተከሳሽ ደግሞ ፐርፍ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ የሚባል ኩባንያ ነው። ተጠሪ ክስ ሊመሰርት የቻለው በአደራ ያስቀመጥኩትን 2,257,064 ኩንታል ነጭ የሁመራ ሰሊጥ ያልመለሰልኝ በመሆኑ በፍርድ ኃይል ተገዶ ይመለስልኝ በማለት ነው። ክሱን በተመለከተም ሰሊጡ እንዲታገድ ጥያቄ በመቅረቡ ፍ/ቤቱ ሰሊጡ በሚገኝበት በናይል ቡና ላኪ ኃ.የተ.የግ.ማ. መጋዘን እንዳለ ተከብሮ እንዲቆይ ትዕዛዝ ሰጥቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ክርክሩ ከመወሰኑ በፊት ከሳሽና ተከሳሽ ጉዳዩን በእርቅ ጨርሰው ስለመጡ ይህንኑ ለፍ/ቤቱ አቅርበው በስምምነቱ መሠረት እንዲፈፀም ትዕዛዝ አሰጥተዋል። ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረውን የእግድ ትዕዛዝም ፍ/ቤቱ አንስቶአል። አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባው ከዚህ በኋላ ነው።

ከመዝገቡ እንዳየነው አመልካች መቃወሚያ ያቀረበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ ዳኝነት የጠየቀውም ከሣሽና ተከሣሽ ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በመያዣ የያዝኩትን ሰሊጥ የሚመለከት በመሆኑ ይጎዳኛል፣ ይሰረዝልኝ በማለት ነው። ፍ/ቤቱ የሁሉንም ወገኖች ሃሳብ ከተቀበለ በኋላ፣ የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶአል። በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ተካሂዶአል። በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሰሊጥ አመልካች ለሥር ተከሳሽ ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘው አይደለም። ሰሊጡ የሥር ተከሳሽ በአደራ ያስቀመጠው የተጠሪ ንብረት በመሆኑ በተጠሪ እና በሥር ተከሳሽ መካከል ታህሳስ 14 ቀን 2001 ዓ.ም. የተደረገው የእርቅ ስምምነት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማፅደቁ ተገቢ ነው። በመሆኑም በስምምነቱ መሠረት ይፈጸም በማለት ወስኗል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው።

በበኩላችንም አመልካች ታህሳስ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። በመቀጠልም

አከራካሪ የሆነውን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።
ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው በተጠሪ እና በሥር ተከሳሽ መካከል የተፈጠረው ግንኙነት የተመሠረተው ግንቦት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. በፊአሙት የአደራ ውል ላይ ነው። የአደራ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ማለትም ከግንቦት 13 እስከ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ በነበሩት ቀናት ውስጥ ሰሊጡ ወደ መጋዘኑ ስለ መግባቱም በፊደራል ጠ/ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በማስረጃ የተረጋገጠ ስመሆኑ በውሳኔው ላይ ተመልክቶአል። ተጠሪ በአደራ አስቀማጩ ላይ ክስ የመሠረተው ሰሊጡን ሊመልስልኝ አልቻሰም በማለት ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ ሰሊጡ በመያዣ የያዝኩት ነው። ለተጠሪ ሲሰጥ አይገባም የሚል መከራከሪያ ይዞ ነው ወደ ክርክሩ የገባው። የመያዣ ውሉ ተደረገ የተባለው በአመልካች እና በሥር ተከሳሽ (ሰሊጡን በአደራ አስቀምጦአል ተብሎ በተከሰሰው) መካከል እንደሆነም አላከራከረም። በመሆኑም ለክርክሩ መነሻ በሆነው ሰሊጥ ላይ አመልካች መብት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ ከማየት በፊት ከመሠረቱ ሰሊጡ የማን ንብረት ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለሱ አግባብ ይሆናል።

የአመልካች ክርክር በዋነኛነት የተመሰረተው የሥር ተከሳሽ በናይል ቡና ላኪ ኃ.የተ.የግ. ማህበር መጋዘን በተለያዩ ጊዜያት የሚያስገባውን ሰሊጥ በመያዣነት ለመያዝ ጎዳር 13 ቀን 98 ዓ.ም. በተደረገው የሶስትዮሽ ውል አለኝ በሚለው ላይ ነው። ለክርክሩ መነሻ የሆነው መጠኑ በትክክል የተገለፀው ሰሊጥ በእርግጥ እና በተሰየ ሁኔታ በመያዣ ለመያዙ የሚያስረዳለት ሌላ ማስረጃ ግን አላቀረበም። ሰሊጡ የማን ነው? በሚለው ነጥብ ላይ በዝርዝር ክርክር የተደረገው በፊደራል ጠ/ፍ/ቤት ሲሆን፣ በዚህ ሂደትም ፍ/ቤቱ ሰሊጡ በተጠሪ ስም ከጎንደር ተጭኖ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ በቀጥታ ለሥር ተከሳስም ተቀብሎ በናይል ቡና ላኪ ኃ.የተ.የግል ማህበር መጋዘን ውስጥ በማስቀመጡና፣ ለዚህም ግንቦት 8 ቀን 2000 ዓ.ም. የተጻፈ ቁጥር 0119 እና 0001 የሆኑ ግንቦት 9 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፈ ቁጥሩ 0116 የሆነ ግንቦት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፈ ቁጥሩ 0117 የሆነ፣ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፉ ቁጥር 0118 እና 0119 የሆኑ እና ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፈ ቁጥር 0120 የሆነ የማስጫኛ ሰነዶች በአስረጂነት መቅረባቸውን አረጋግጠዋል። የማስጫኛ ሰነዶች የመኪናው ታርጋ (ሠሌዳ) ቁጥር፣ የሹፌሩ ስም እና ስልክ ቁጥር፣ የጭነቱን ልክ፣ ወዘተ በዝርዝር የያዙ እንደሆኑም ጠ/ፍ/ቤት አረጋግጦአል። ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ሰሊጡን ወደ አዲስ አበባ ያመጣው ለመሸጥ እንደሆነ፣ ነገር ግን በጊዜው የገበያ ዋጋ ስለ ዋገርቀበት የተሻለ ገበያ እስኪያገኝ ድረስ ብአደራ እንዲቀመጥለት ማድረጉን ፍ/ቤቱ ማጣራቱን በውሳኔው ላይ ተገልፏል። ፍ/ቤቱ እንዚህን ማስረጃዎች ከመረመረ እና ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አገናዝቦ ከመዘነ በኋላም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሰሊጥ የተጠሪ ንብረት ነው ወደሚለው መደምደሚያ ደርሶአል።

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሰሊጡ የተጠሪ ንብረት ስለመሆኑ በሕግና በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበውን ክርክር የመመርመር ስልጣን ባለው ጠ/ፍ/ቤት ተረጋግጦአል። አመልካች የመያዣ ውል ያደረገው ከተጠሪ ጋር አይደለም። የመያዣ ውል አደረግሁ የሚለው ከሥር ተከሳሽ ፐርፍ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ጋር ሆኖ መሠረቱም በየጊዜው ተሰጡ የተባሉት ብድሮች እንደሆኑ በክርክሩ ገልያታል። በሰሊጡ ላይ መብት አለኝ የሚለው የመያዣ ውሉን መሠረት በማድረግ እስከሆነ ድረስ ሰሊጡ የመያዣ ሰጪው ንብረት መሆኑን ሊያስረዳ ይገባል። እንደምናየው ግን የመያዣ ውል ማድረጉን ከማሳየት አልፎ

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሰሊጥ የመያዣ ሰጭው ንብረት መሆኑን ሊያስረዳ እንዴልቻለ ጠ/ፍ/ቤቱ አረጋግጦአል። በመሆኑም ለክርክሩ አልባት ለመስጠት መታየት ያለበት ሰሊጡ የማን ንብረት ነው ለሚለው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ እንጂ አመልካች ከሥር ተከሳሽ ጋር የመያዣ ውል አድርጎአል ወይስ አላደረገም የሚለው አይደለም። በመጨረሻም በማስረጃ ተረጋግጦ በተደረሰው የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ የቀረበው የሰበር አቤቱታ በሕግ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖሩን የሚያሳይ ባለመሆኑ የሰበር ችሎቱ የሚያርመው አይሆንም (የኢፌዲሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 ይመለከተዋል።

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 46144 ታህሳስ 1 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል።
2. አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል።
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች ይቻቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

ት ዕ ዛ ዝ

ታህሳስ 4 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቶአል። ለሚመለከተው ይፃፍ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

Effect of Non-Renewal of Registration of a Contract of Mortgage under the Ethiopian Civil Code: A Case Comment

Aschalew Ashagre*

I. Introduction

In almost all jurisdictions, there are important security devices which are meant to secure the due performance of an obligation in general and contractual obligation in particular.[569] Mortgage is one of such security devices which is widely practiced in the world. According to Black's Law Dictionary, 'mortgage is a conveyance of title to property that is given as a security for the payment of a debt or the performance of a duty and that will become void [extinguished] upon payment or performance according to the stipulated terms'.[570] However, as we can easily observe, this definition cannot as such enable us to distinguish mortgage from other security devices particularly from that of pledge[571] as the definition does not tell us about properties which are brought under the ambit of mortgage.

Mortgage is established where a specific immovable property is made for the payment of money or the performance of an obligation. [572] Thus, mortgage, as a security device, pertains to an immovable property. The Ethiopian Civil Code (hereinafter Code) does not define mortgage although it has made it clear that a mortgage may charge an immovable only.[573]

---

* LL.B, LL.M, Lecturer in Law, Consultant and Attorney-at-Law.

569 The term security devices encompass devises such as pledge, surety, lien, financial guarantee bond and the like, see for instance, Arkun Kimer Sen and Jitendra Kumar Mitra, Commercial Law Including Company Law, 21st ed., the World Press Private Limited, Calcutta, 1998 at. 402-409. See also M. Planiol, Treatise on the Civil Law, Translated by the Louisiana State Institute, 11th ed., Vol. 2, No. 2, 1939. In Ethiopia, too, surety has been dealt with Art. 1920-1951, and pledge has been regulated by Arts. 2825-2873 of the 1960 Civil Code of the Empire of Ethiopia while lien is essentially created by virtue of the law and found scattered in the Civil Code.

570 Bryan A. Garner, (Editor-in-Chief), Black's Law Dictionary, 8th ed., 2004, at 1031.

571 There are essential differences between mortgage and pledge with regard to formation, and the respective rights and duties of the parties involved, the consequences that each security device produce.

572 Arkumen Sen and Jitendra Kumar Mitra, Supra note, 1, at 402. Besides, mortgage is defined as "dead pledge". See Corpus Juris Secundum: A Complete Restatement of the Entire American Law, Vol. 58, at 23.

573 Civil Code of the Empire of Ethiopia (Civil Code), proclamation No. 165, 1960, Art. 3047.

However, the Code has also provided that a mortgage may charge certain kinds of movables where it is clearly provided by law.[574]

As far as the establishment of mortgage is concerned, the Code has incorporated three ways. These are: 1) Legal mortgage; 2) Judicial mortgage; and 3) Contractual mortgage.[575] Concerning the first, Article 3042 of the Code states that whosoever sells an immovable shall have a legal mortgage on such immovable as a security for the payment of the agreed price and for the performance of any other obligation laid down in the contract of sale. From this provision, it is possible to gather that the mortgage created by virtue of the law is an accessory obligation whose creation and existence hinges upon the creation and existence of the principal obligation - the contract of sale. In addition to this, a legal mortgage is created in favor of a co-partitioner of an immovable property.[576] In this case, too, for a legal mortgage to come into being, there must be a contract of partition of an immovable property. The second type of mortgage is judicial mortgage where a court or an arbitration tribunal may secure execution of its judgments, orders or awards by granting one party a mortgage on one or more immovables the property of the other party. This also indicates that mortgage is an accessory obligation for it is created by the court or an arbitral tribunal which entertains a case involving a principal obligation.

The other point worth considering in this introductory part, is the requirements that need to be satisfied for the establishment of a valid mortgage. In this regard, Article 3045 of the Code stipulates that the contract or other agreement creating mortgage shall be of no effect unless it is made in writing. Sub-article 2 of the same article adds that it shall be of no effect unless it specifies in Ethiopian currency the amount of the claim secured by mortgage.

Article 3045(1) reaffirmed what Article 1725 of the Code has stated that writing is a validity requirement to establish a contract of mortgage. In

---

574 In Ethiopia, as a matter of exception; mortgage may be established on movable properties where such is specifically provided by law.

575 Civil Code, Supra note 5, Art. 3041.

576 Id, See Art. 3043 which stipulates that a co-partitioner shall have a legal mortgage on the immovable allotted to his co-particioners in accordance with the act of partition. Such mortgage shall secure the payment of any compensation in cash that may be due to him or such other compensation as may be due by the co-partitioner where he is dispossessed of any property allotted to him.

addition to the requirement of writing, the Code has provided another stringent requirement - the contract of mortgage shall be of no effect unless the amount of claim secured by the mortgage is specified in Ethiopian currency. Furthermore, there is also another stiff requirement that needs to be satisfied so that a valid mortgage will be established. This is registration of mortgage. In this regardd, Article 3052 of the Code declares that a mortgage, however created,[577] shall not produce any legal effect except from the day when it is entered in the register of immovable property at the place where the immovable mortgage is situate.[578]

To sum up, no valid mortgage can be established in Ethiopia unless the following elements are cumulatively satisfied. These are:

1. Mortgage must be made in writing;
2. The amount secured by the mortgage should be specified in Ethiopian currency (Birr).
